

«መንግስታችን እያለማ ያለው ስንዴ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም መመገብ ይችላል»

- አቶ በንቲ ፉፋ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት የቦርድ አባል

ገጽ 6

የግለሰቡ እና የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ክርክር እስከ ሰበር

ገጽ 10


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 056 ጥቅምት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# «የሰላም ስምምነቱ በሁሉም ዜጎች ተሳትፎ ኢትዮጵያን ከፍ ለማድረግ ዕድል ይፈጥራል»

## - አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፣ "የሰላም ስምምነቱ በሁሉም ዜጎች ተሳትፎ ኢትዮጵያን ከፍ ለማድረግ ዕድል ይፈጠራል ሲሉ የሰላም አማራጭ አቢይ ኮሚቴ አባልና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ተናገሩ። ለተግባራዊነቱ ሁሉም ዜጋ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

የሰላም አማራጭ አቢይ ኮሚቴ አባላት የስምምነቱን አጠቃላይ ሂደትና ቀጣይ ሥራዎችን በሚመለከት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተገኙበት ለሁለቱ ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎች፣ ለክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ ለከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችና ለብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ትናንት ገለጻ አድርገዋል።

የኮሚቴው አባልና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ የደህንነት አማካሪ ሚኒስትር አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን እንዳሉት፣የሰላም ስምምነቱ በዋናነት የኢትዮጵያን ዘላቂ

«የሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ከስምምነቱ ማግስት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦንድ ሽያጭ በዓለም ደረጃ በፍጥነት ጨምሯል

## - የወደሙ አካባቢዎችን መልሶ የመገንባቱ ሂደት ለኢኮኖሚ እድገት ዕድል ይፈጥራል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል ከተደረገው የሰላም ስምምነት ጋር ተያይዞ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የኢትዮጵያ 'ዩሮ ቦንድ' ገዢ ኢንቨስተሮች ቁጥር በአንዴ በዓለም ደረጃ መጨመሩን የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ አመለከቱ።

በጦርነት የወደሙ አካባቢዎችን ለመገንባት የሚፈሰው መዋዕለ ንዋይ በተገቢው ከተተገበረ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርም አክለው ገልጸዋል።

አቶ ዘመዴነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ የኢንቨስተሮች ፍሰትን ለመጨመር ከዓለም ኢንቨስተሮች የተበደረችው የአንድ ቢሊዮን ዶላር 'ዩሮ ቦንድ' በጦርነቱ ምክንያት ኢንቨስተሮች ወደ አገሪቱ የመሄድ ፍላጎት በማጣታቸው የቦንዱ ዋጋ በዓለም ገበያ በጣም ወርዶ ነበር። ነገር ግን ከስምምነቱ ማግስት ጀምሮ ዋጋው በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል።

ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ ያውም አብዛኞቹ በአምራች እድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች የሚገኙባት ሀገር በመሆኗ እና በአየር ንብረቷ በዓለም ኢንቨስተሮች ዘንድ ተመራጭ በመሆኗ ለኢንቨስተሮች ተመራጭ ሀገር ናት ያሉት አቶ ዘመዴነህ፣ የሰላም እጦቱ በኢንቨስተሮች ፍሰት ላይ ያስከተለው ጥቁር ጠባሳ እንዳለ ሆኖ በኢንቨተሮች ፍሰት ጥሩ ውጤት ካስመዘገቡ አገሮች ተርታ መሰለፍ

ከስምምነቱ ማግስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሴ

አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ






# ሰቆጣ ከተማ በመጪዎቹ ሁለት ቀናት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ታገኛለች

## - በሁመራ የኤሌክትሪክ መስመር ጥገና እየተካሄደ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ሰቆጣ ከተማ በጦርነቱ ምክንያት በደረሰ ጉዳት ተቋርጦባት የነበረውን የኤሌክትሪክ አገልግሎት በሁለት ቀናት ውስጥ እንድታገኝ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ። በሁመራና አካባቢው የሚገኙ ዜጎች የኤሌክትሪክ

ሰቆጣ ከተማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች በርካታ የስራ እድሎችን እየፈጠሩ ነው

ገጽ 4

ዜና

# በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያተኮረው ዓለም አቀፍ ወርክሾፕ በአዲስ አበባ ተካሄደ

**ኢያሱ መሰለ**

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን የተደገፈው "ሁለተኛው ዙር ዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃና ደህንነት እና አፍሪካ" የተሰኘ ወርክሾፕ በአዲስ አበባ ከተማ ተካሄደ።

የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ከሪጅናል ሴንተር ፎር ማፒንግ ኦፍ ሪሶርስስ ፎር ዴቨሎፕመንት (RCMRD) ጋር በመተባበር ያዘጋጁት ይህ ወርክ ሾፕ የአካባቢ ጥበቃና ደህንነትን አስመልክቶ አፍሪካ ስለነደፈችው እቅድና መከተል ስላለባት አዋጭ መንገድ እንዲሁም ሀገራት እርስ በእርሳቸው ሊኖራቸው ስለሚገባው አጋርነትና ፍላጎት ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ነው።

በመርሐ ግብሩ ላይ የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ዳይሬክተርን በመወከል ንግግር ያደረጉት ቱሉ በሻ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በአህጉሩ በምስራቅ አፍሪካና በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃና ደህንነት ችግር እያጋጠመ ነው። ወርክሾፑ የልምድ ልውውጥ የተካሄደበትና የጋራ መግባባት የተደረሰበት ነው።

የቀጣናው ሀገራት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ወሳኝ ጉዳዮች በመለየት መረጃን መሠረት ያደረገ ፖሊሲ በማውጣትና ትክክለኛ ውሳኔ በማስተላለፍ የመሬትን የውሃ ሀብትና አካባቢን ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል ያሉት ዶክተር ቱሉ፤ ስለተፈጥሮ ሃብትና ስለአካባቢ ሁኔታ የጂኦስፓሻል መረጃዎችን በመጠቀም ሀገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ እድገትን ማረጋገጥ እንደሚቻል ተናግረዋል።

የRCMRD ተወካይ ኢኑሲ ዋንጓዊ በበኩላቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ ለመንከባከብ እና ጥቅም ላይ ለማዋል በቂ መረጃ ሊኖር ይገባል። ድርጅቱ ከኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ጋር በትብብር መሥራቱ የአገሪቱን አካባቢያዊ፣ መልክዓ ምድራዊና ተፈጥሯዊ ሃብት በተመለከተ በቂ መረጃ ስላለው ነው።

ተቋሙ በሚሰጣቸው መረጃዎች አማካኝነት መንግሥት የፖለሲ ማሻሻያዎችን የማድረግ እድል እንደሚያገኝም ተናግረዋል።

የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተፈጥሮ ሀብትን በምን አግባብ መጠቀም እንደሚገባ የሚለውን መረጃ መለዋወጥ ያስፈልጋል ያሉት ተወካይዋ፤ በቀጣናው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን በመለየት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተፈጥሮ ሀብቱን እንዴት መጠቀም እንዳለበት አስቀድሞ መወያየት ክፍተትን ይሞላል ብለዋል።

የደኖች መመናመን የሚያስከትለውን የድርቅና የጎርፍ አደጋ ለመቀነስ የጂኦስፓሻል መረጃዎችን መሠረት አድርጎ መሥራት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

RCMRD ከአፍሪካ ኅብረት ጋር በገባው ስምምነት መሠረት ከደቡብና ምስራቅ አፍሪካ 20 ሀገራትን በማስተሳሰር በአካባቢና ደህንነት ጥበቃ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ላይ የተሠማራ ድርጅት ነው።

በወርክሾፑ ላይ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ሙያተኞች መሳተፋቸውን ለማወቅ ተችሏል።

# በክልሉ በመማሪያ ተፋሰሶች ፕሮጀክት ከአራት ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆነዋል

**አዲሱ ገረመው**


አርሶአደር ጥላሁን ገላዬ


አቶ ወሮታ አበራ



ፈለገ ሕይወት፡- በአማራ ክልል በአምስት የመማሪያ ተፋሰሶች ፕሮጀክት ከአራት ሺህ በላይ አርሶ አደሮች በተፈጥሮ ሀብት ልማት ተጠቃሚ መሆናቸው ተገለጸ።

በውሃና መሬት ሀብት ማዕከል በክልል ደረጃ የቀድሞ የመማሪያ ተፋሰሶች አስተባባሪ የነበሩና በአሁን ወቅት በቁንዝላ የተቀናጀ ፕሮጀክት ቴክኒካል አሲስታንት የሆኑት አቶ ወሮታ አበራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፣ የጣናና አባይን ተፋሰስ መሠረት አድርገው ባሉ አምስት የመማሪያ ተፋሰሶች በልማት ቡድን የተደራጁ አራት ሺህ 626 አርሶ አደሮች የመሬትን ምርታማነት በማሻሻል በተፈጥሮ ሀብት ልማት ተጠቃሚዎች ሆነዋል።

እንደ አቶ ወሮታው ገለጻ፣ የውሃና መሬት ሀብት ማዕከል ተግባራዊ ባደረገው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ፕሮጀክት በአማራ ክልል በሜጫ፣ ደንበጫ፣ ይልማና ዴንሳ፣ ባህር ዳር ዙሪያና ደሴ ዙሪያ ወረዳዎች በሚገኙ የመማሪያ ተፋሰሶች የተራቆተውን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ መልሶ እንዲያገግም በማድረግ ማልማት ተችሏል።

ፕሮጀክቱ የአፈር ጥበቃ ሥራን መሠረት በማድረግ በጥናት ላይ ተመሥርቶ ለኅብረተሰቡ ተገቢው የሆነ ሙያዊ እገዛን በማድረግ በርካታ ተግባራት እንዲከናወን ያስቻለ መሆኑን ጠቅሰዋል። በተፈጥሮ ሀብት ልማት የአርሶ አደሩን ገቢ በማሳደግና ኢኮኖሚውን በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ሚናን ተጫውቷል ብለዋል።

አቶ ወሮታው እንደሚሉት፣ በመማሪያ ተፋሰሶቹ የአካባቢውን የውሃ እጥረት በማሻሻል ለሰውና እንስሳት መጠጥ የሚውል ውሃን በበቂ ሁኔታ እንዲዳረስ ሆኗል።

በአካባቢው ላለው ማኅበረሰብና በየደረጃው ላለው የመንግሥት አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቶ የግብርና ሥራው ውጤታማ እንዲሆን መደረጉንም ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ በአምስቱ ተፋሰሶች ላይ ባሉት ሦስት ሺህ 790 ሄክታር መሬት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ ሦስት ሺህ 456 የእርሻ ማሳ ላይ የተፈጥሮ ሀብት ልማት መከናወኑን ገልጸዋል። ከዚህ ውስጥ 238 ሄክታር የተራቆቱ መሬቶችን በማልማት ሕዝቡ ተጠቃሚ መሆን እንደቻለና የውሃ ማስረግ፣ የደን ልማትና የፍራፍሬ ልማት ሥራዎች ውጤት ሊያመጡ በሚችሉ ስልቶች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

ከዚህም በሻገር በጓሮ ልማት፣ በእንስሳት እርባታና መሰል የግብርና ሥራዎች ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ መሆኑን አንስተዋል።

በአሁን ወቅት የመማሪያ ተፋሰስ ቁጥር እየጨመረ መሆኑን፣ ይህም የተጀመረው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ውጤታማና ዘላቂ መሆኑን በየአካባቢው ያሉ አርሶ አደሮች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተናግረዋል።

በምዕራብ ጐጃም ዞን ደቡብ ሜጫ ወረዳ ፈለገ ሕይወት ቀበሌ ነዋሪ አርሶ አደር ጥላሁን ገላዬ እንደተናገሩት ከዚህ ቀደም በአካባቢው የነበረው የተራቆተው የመሬት ገጽታ ተለውጦ ተፈጥሯዊ ሚዛኑ ተስተካክሏል። የአረንጓዴ ሽፋንም ጨምሯል። ይህ የሆነው አርሶ አደሩ በአፈር ጥበቃ ሥራ ስልጠናና ሌሎች ሙያዊ ድጋፍን በማግኘቱ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሥነ ምህዳሩ በመስተካከሉ ተጨማሪ ሥራ እንድናከናውን አግዞናል ያሉት ደግሞ በሰሜን ሜጫ ወረዳ የብራቃት ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አርሶአደር አለሸኝ ደምለው ናቸው። በፕሮጀክቱ ባገኙት ድጋፍ የጓሮ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የእንስሳትና የንብ እርባታ በመሥራት ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አዳዲስ ዝርያዎችን በመጠቀም የሰብል ምርታማነትን መጨመር እንደቻሉ በመናገር ለሎችም ተሞክሮን እያካፈሉ እንዳለ ጠቅሰዋል።

ማዕከሉ የግብርና ምርምር ባለሙያዎችን በማሳተፍና አርሶ አደሩን በማደራጀት ተጨባጭ ውጤት እስኪመጣ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር ሲያደርግ መቆየቱ ተጠቅሷል።

የመማሪያ ተፋሰስ በውሃና መሬት ሀብት ማዕከል አስተባባሪነት ጐርፍን በማስቀረት፣ የተራቆተውን መሬት በማልማት የተፈጥሮ ሀብትን ከምርምር ጋር በማያያዝ የሕዝቡን የባለቤትነት ስሜት በማዳበር በትብብር የሚሠራ ተሞክሮ ሲሆን፣ በአሁን ወቅት በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች እየተተገበረ ይገኛል።

# ከ398 ሺህ በላይ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ መግባታቸው ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ከ398 ሺህ በላይ የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር እንዲገቡ መደረጉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ ሀገራችን በምግብ ራሷን ለመቻል የምታደርገውን ጥረት ለመደገፍና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ባለፉት ጊዜያት የፖሊሲና የአሠራር ማሻሻያዎችን ማድረጉን ነው ያስታወቀው።

በዚህም በክረምት ብቻ ይመረት የነበረውን የተለመደ አሠራር በመቀየር በበጋ ወቅትም አርሶ አደሩ መስኖን ተጠቅሞ እንዲያመርት ለማስቻል ከአጋር ድርጅቶች ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑን ሚኒስቴሩ ገልጿል።

በመሆኑም አርሶ አደሩ በዓመት እስከ ሦስት ጊዜ በማምረት ተጠቃሚ መሆኑን ተገልጿል።

ምርትና ምርታማነትን ለመጨመርም የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ ባለ ሀብቶች እንዲበረታቱ ከቀረጥና ታክስ ነጻ በማድረግ ለግብርናው አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እንዲገቡ መደረጉ ተጠቅሷል።

በዚህም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ 10 ዓይነት የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እንደ ትራክተር፣ ኮምባይነርና ሁለገብ መውቂያ፣ የውሃ ፓምፕ ከእነመለዋወጫው እና መሰል እቃዎች በጥቅሉ 398 ሺህ 627 የግብርና ቴክኖሎጂዎች በ23 ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸው ታውቋል።

በተመሳሳይ የዘንድሮውን የበጋ ስንዴ ልማት ለማሳካትም በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት እየሰጡ ካሉት በተጨማሪ 75ሺህ ውሃ መሳቢያ ሞተሮች የሚያስፈልግ ሲሆን ለዚህም ሁለት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ይጠይቃል ተብሏል። ወጪውም በክልልና በፌዴራል መንግሥት በጀት ድጋፍ የሚሸፈን መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል።

# ኢትዮጵያና ሶማሊያ ሽብርተኝነትን የመከላከል ትብብራቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያና የሶማሊያ የመረጃ ተቋማት በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና እየተስፋፋ የመጣውን ሽብርተኝነት ለመከላከል የሚያከናውኗቸውን የጋራ ስምሪቶች አጠናክረው ለመቀጠል ስምምነት ማድረጋቸው ተገለጸ።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳመለከተው፤ በአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ምክትል ዳይሬክተር ጀኔራል አቶ ሲሳይ ቶላ የተመራ ልዑክ ጥቅምት 19 ቀን 2015 ዓ.ም በሶማሊያ ከተፈጸመው የሽብር ጥቃት ጋር በተያያዘ ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የሚደርሱ ከኢትዮጵያ መንግሥት የተላኩ የሕክምና መሣሪያዎችንና መድኃኒቶችን ይዞ ወደ ሶማሊያ ተጉዟል።

የአገልግሎት መሥሪያ ቤቱ ምክትል ዳይሬክተር ጀኔራል አቶ ሲሳይ ቶላ ከመርሐ ግብሩ ጎን ለጎን ከሶማሊያ አቻ ተቋም ዳይሬክተር ጀኔራል ማሐድ ሞሐመድ ጋር በወቅታዊና በሁለትዮሽ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አድርገዋል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር ጀኔራል አቶ ሲሳይ ቶላ በውይይቱ ወቅት ሰሞኑን በሶማሊያ ሞቃዲሾ በደረሰው የሽብር ጥቃት የተሰማቸውን ኃዘን መግለጻቸውን ያመለከተው መግለጫው፤ እንደዚህ አይነት ክስተቶች የሚፈጥሩትን ሥጋት ለማስቀረት በምሥራቅ አፍሪካ የሚደረጉ የጸረ ሽብር ትግልን የተመለከቱ አጋርነቶችንና ትብብሮችን ማጠናከር እንደሚገባ መናገራቸውን ጠቁሟል።

የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ከሶማሊያ አቻው ጋር ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ በአቅም ግንባታ መስኮችና በመረጃ ልውውጥ የሚያደርገውን ትብብር አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያስታወቁት አቶ ሲሳይ፤ ከሰሞኑ የሽብር ጥቃት ጋር በተያያዘም መንስኤዎቹንና መፍትሔዎችን በተመለከተ ጥናት የሚያከናውንና ለሀገሪቱ መንግሥት እገዛ የሚያደርግ ቡድን በመላክ ሥራ መጀመሩን ጠቁመዋል።

የሶማሊያ ናሽናል ኢንተለጀንስ ኤንድ ሴኩዩሪቲ ኤጀንሲ ዳይሬክተር ጀኔራል ማሐድ ሞሐመድ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ መንግሥት ለተደረገው እገዛ ምስጋናቸውን ማቅረባቸው ተጠቁሟል።

ሽብርተኝነትን የመከላከል ስምሪቶች የተቀናጀ እንቅስቃሴ የሚፈልጉ በመሆናቸው በምሥራቅ አፍሪካ እየተስፋፋ የመጣውን ሥጋት ለመመከት ቁልፍ አጋር ከሆነችው ኢትዮጵያ ጋር ትብብሩ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ስምምት ላይ መደረሱን መናገራቸው ተመልክቷል።

ከብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የሶማሊያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼክ መሐሙድ በቅርቡ በኢትዮጵያ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ጋር የድንበር አካባቢ የጸጥታ ሁኔታዎችን በማሻሻልና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶችን በማሳደግ ረገድ የደረሱባቸው ስምምነቶች ተግባራዊ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ምክክር ተደርጓል።

# ከሕግ ውጭ በሚሠሩ የፋርማሲ ባለቤቶች ላይ እስከ እስር የሚደርስ ቅጣት እንደሚጥል ባለስልጣኑ አስጠነቀቀ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ችግሮቻቸውን በአስቸኳይ ማስተካከል በማይችሉና ከሕግ ውጭ በሚሠሩ ፋርማሲዎችና ባለቤቶቻቸው ላይ እስከ እስር የሚደርስ ቅጣት እንደሚጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን አስታወቀ።

በትናንትናው ዕለት በአጠቃላይ በፋርማሲዎች ላይ ያሉ ችግሮችን በተመለከተ ከፋርማሲ ባለሙያዎች፣ በዘርፉ ከተሰማሩ ባለንብረቶችና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተደርጓል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ታደሰ አጥላባቸው እንደገለጹት፤ በውይይቱ ወቅት በፋርማሲዎች ችግሮች መኖራቸውንና በአስቸኳይ ማስተካከል እንዳለባቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተግባብተናል። መስተካከል ካልቻሉ እስከ እስር የሚደርስ ቅጣት የምንቀጣበት ሁኔታ ስለመኖሩ ገልጸዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ያልተፈቀዱ የተለያዩ መድኃኒቶች በኮንትሮባንድ ወደ ሀገራችን ይገባሉ። በምናደርገውም ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን የት እንደተመረቱ የማይታወቁ፣ ደረሰኝ የሌላቸውና ግልጽ ያልሆኑ መድኃኒቶች በአንዳንድ ፋርማሲዎች ውስጥ ተገኝተዋል።

ባለስልጣኑም በሕገወጥ የገቡ መድኃኒቶችን የመሰብሰብና ለፋርማሲዎች ያልተገባ ድርጊት መሆኑን በማስተማር ማስጠንቀቂያ የመስጠት ሥራዎችን እየሠራ ነው። ከመሰል ሥራቸው የማይታገሱ ካሉ አስተማሪ የሆነ እርምጃ ይወሰዳል። በቀጣይ በሕገ ወጥ መንገድ የሚገቡ መድኃኒቶችንና አደንዛዥ እጾችን በተመለከተ በጥብቅ ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልት እየነደፍን ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ውስጥ ባሉ ፋርማሲዎች ላይ በሠራነው የኦዲት ሥራ ከአሠራር ሥርዓቱ ውጭ የሆኑ ግኝቶች ተገኝተዋል። ፋርማሲው የሚሠራበት አካባቢያዊ ሁኔታ ለተገልጋይ አመቺ አለመሆን፣ ፋርማሲዎች ውስጥ ያሉ ምርቶች ጊዜያቸው ያለፈ፣ መድኃኒቶች የተፈቀዱና በሕጋዊ መንገድ የገቡ አለመሆን በአንዳንድ ፋርማሲዎች ላይ መኖሩን ግኝቶች እንደሚያሳዩ ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

የፋርማሲ ሙያ የሌላቸው ነርሶች መድኃኒት ያድላሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ይህ ከመንግሥት አሠራር ውጭ በመሆኑ መታረም አለበት። የፋርማሲው አቀማመጥ ለተገልጋይ ምቹ አለመሆንና አገልግሎት ሊወስድ የመጣ ታካሚ ምንም አይነት መረጃ ሳይሰጠው መድኃኒቱን ይዞ ይሄዳል። መድኃኒቱ ሊያመጣ ስለሚችለው የጎንዮሽ ጉዳት አለማስረዳትም ሌላው በግምገማ የተገኘ ችግር ነው ብለዋል።

ያልተፈቀዱ መድኃኒቶችን በተለይ የጸረ ባክቴሪያ ተዋሲያን መድኃኒት፣ ለተለያዩ ሕመም የሚወሰዱ ማስታገሻዎችና ሌሎች መድኃኒቶች ባልሆነ መልኩ እየተተገበሩ ያገኘንበት ሁኔታ በመኖሩ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው። እንዲሁም ትራማዶል የሚባለው መድኃኒት በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉ ወጣቶች በከፍተኛ ደረጃ እየተጠቀሙት ነው። ይህ ደግሞ በልጆች ጤና ላይ ከባድ የጤና መታወክ እያመጣ በመሆኑ በቀጣይ ሕጋዊ ሥርዓት የማስያዝ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጸዋል።

ስለመድኃኒት አጠቃቀም ኅብረተሰብ ግንዛቤ እንዲኖረው እየሠራን ያለነው ሥራ በቂ አይደለም ያሉት አቶ ታደሰ፤ ችግሮችን ከመቀነስ አኳያ በመድኃኒት አጠቃቀም ዙሪያ በሚዲያና በትምህርት ቤት ከፍተኛ ሥራ ለመሥራት እየተንቀሳቀስን ነው። ማንኛውም መድኃኒት ተጠቃሚ ዜጎች መድኃኒቶች መፈወሻ ብቻ ሳይሆኑ የጎንዮሽ ጉዳት እንዳላቸው አውቀው በነቃ ሁኔታ ማየትና ባለሙያን ማማከር እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል።

# ስምምነቱ በሕዝቡ ኑሮ ላይ ያለውን ምስቅልቅል እንደሚያስተካክል የመቀሌ ነዋሪዎች ተናገሩ

**ዳግማዊት ግርማ**



አዲስ አበባ፡- ሰሞኑን በሕወሓትና በፌዴራል መንግሥት መካከል የተካሄደው የሰላም ስምምነት በትግራይ እና ሌሎች የሃገሪቱ ክፍሎች የተከሰተውን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች እና በሕዝቡ ኑሮ ላይ የተከሰተውን ምስቅልቅል እንደሚያስተካክል የመቀሌ ነዋሪዎች ተናገሩ።

የከተማዋ ነዋሪዎች በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት በፌዴራል መንግሥት እና ሕወሓት መካከል በተደረሰው የሰላም ስምምነት መደሰታቸውንም ገልጸዋል።

ሰሞኑን ለጀርመን ድምፅ ሬዲዮ አስተያየታቸውን የሰጡት የከተማዋ ነዋሪዎች እንደገለጹት፤ ሰላምን ከትግራይ ሕዝብ በላይ የሚፈልግ የለም፤ ምክንያቱም በተለይ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በአካባቢው የደረሰው ሰብዓዊና ቁሳዊ ቀውስ ከፍተኛ ነው።

ሆኖም ሰሞኑን በሕወሓት እና በፌዴራል መንግስቱ መካከል የተደረሰው ስምምነት ይህንን ችግር በመፍታት በአካባቢው ሰላምን ለማስፈን የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው።

የመቐለ ከተማ ነዋሪውና በመንግሥት ሥራ የሚተዳደሩት አቶ ዳዊት ገብረሚካኤል እንደተናገሩት፤ የሰላም ጉዳይ ለትግራይ ሕዝብ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ሰላምን ከትግራይ ሕዝብ በላይ የሚፈልግ አለም ብለው አያስቡም።

እንደ አንድ የትግራይ ተወላጅ ስምምነቱ በሕዝቡ ኑሮ ላይ ያለውን ምስቅልቅል የማስተካከል ዕድል ይፈጥራል የሚል እምነት እንዳላቸው የገለጹት አቶ ዳዊት፤ ሕዝቡንም ከመፈናቀልና ከብዙ መከራ እንደሚያድነው ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል ።

እንደ አቶ ዳዊት ገለፃ፤ ባለፉት ሃያ አራት ወራት የትግራይ ሕዝብ በጦርነት ሰበብ ብዙ መከራ አይቷል፣ ሲቸገር ቆይቷልና የሰላምን ዋጋ ከትግራይ ሕዝብ በላይ ማንም ሊረዳ አይችልም።

በስምምነቱ ግልፅ ያልሆኑና ያልጠሩ ነገሮች ቢኖሩም ለትግራይም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ብቸኛ አማራጭ መሆን እንደሚገባው የገለጹት አቶ ዳዊት፤ ዝርዝር አፈፃጸሙ እንዴት እንደሚሆን የስምምነቱ ተፈፃሚነት ላይ ፍርሀትና ጥርጣሬ እንዳላቸውም አልሸሸጉም።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ጦርነት አብቅቶ የሰላም ስምምነት በመደረጉ ደስተኛ ነን ያሉት የመቐለ ከተማ ነዋሪው አቶ ልጃለም በበኩላቸው፤ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ተግባራዊ መሆን እንደሚገባውም አሳስበዋል።

በሰላም ስምምነቱ የተሰማቸውን ደስታ የገለጹት አቶ አወት፤ የትግራይ ሕዝብ ጥያቄም ይኸው መሆኑን ነው የገለጹት።

ጦርነቱ እጅግ አስከፊ ጉዳት ሲያደርስ መክረሙን የገለጹት አቶ አወት፤ ተኩስ አቁም ተደርጎ ሰላም ለማስፈን የሚደረገው ጥረት የሚበረታታ ነውም ሲሉ ተናግረዋል።

ስምምነቱ ወደ ዘላቂ ሰላም እንዲሸጋገር ተስፋ አደርጋለሁ ያሉት አቶ አወት፤ በክልሉ ሰው በየቀኑ እየሞተ ነው፤ የታመመ መታከም የተቸገረ መረዳት አለበትና በስምምነቱ በክልሉ ያሉትን ችግሮች ይፈታል ብለን እናምናለን ብለዋል።

የከተማዋ ነዋሪዎች በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት በፌዴራል መንግሥት እና ሕወሓት መካከል በተደረሰው የሰላም ስምምነት መደሰታቸውንም በመግለፅ ለተግባራዊነቱ ብርቱ ሥራ መሥራት እንደሚያሻም አመላክተዋል።

ዜና

# የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች በርካታ የስራ እድሎችን እየፈጠሩ ነው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ ፡- እስካሁን ድረስ በአገራችን ከተፈጠሩ የሥራ እድሎች እና ኤክስፖርት በማድረግ ከሚገኘው ገቢ በአብዛኛው የሚገኘው ጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ሀገራት የሚሳተፉበት 8ኛው የአፍሪካ ሶርሲንግና የፋሽን ሳምንት ዓለም አቀፍ ዐውደ ርዕይ ከትላንት ጀምሮ በአዲስ አበባ ስካይላይት ሆቴል ተከፍቷል።

ከጥቅምት 25 እስከ ጥቅምት 28 ቀን 2015 የሚቆየውን ይህንኑ ዐውደ ርዕይ የከፈቱት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደተናገሩት፣ አውደ ርዕዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በኢትዮጵያ ያለውን እድል እንዲገነዘቡ የሚያደርግ እና ለሀገር ውስጥ አምራቾችም ሰፊ የገበያ ዕድል የሚፈጥር ነው።

ዐውደ ርዕዩ ለጋርመንት እና ቴክስታይል ኢንዱስትሪዎቻችን ትልቅ የምሥራች ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ በኮቪድ እና በሀገር ውስጥ የሰላም እጦት ምክንያት ከእነዚህ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ማግኘት ሳይቻል መቆየቱን አስታውሰዋል።

በኢትዮጵያ በርካታ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በከፍተኛ መሠረተ ልማትና ወጪ ተገንብተው ሰፊ የሥራ ዕድል እና የኤክስፖርት ገቢ እንዲያስገኙ ታስበው እንደነበር ጠቅሰዋል። በመሆኑም ዐውደ ርዕዩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኙና ኢትዮጵያን ለማስተዋወቅ ያግዛልም ብለዋል። ከኮቪድ በኋላ የዚህ ዓይነት ሁነት ሲዘጋጅ የመጀመሪያ መሆኑን ገልጸው፤ ባለፉት ዓመታት ከኮቪድና ኮቪድን ተከትሎ በመጡት የንግድ ሰንሰለቶችና አቅርቦቶች ችግር በተለይም በጋርመንት እና ቴክስታል እንዲሁም በቆዳው ዘርፍ ተፅዕኖ አሳድሮ እንደነበር አስታውሰዋል።

አፍሪካ ከሰው ሀብት ጀምሮ የተትረፈረፈ የተፈጥሮ ሀብት እና ጥሬ እቃዎች መገኛ በመሆኗ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለሆኑ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ምቹ መሆኗንም ጠቁመዋል።

እ.ኤ.አ ከግንቦት 2021 ጀምሮም በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የሀገር ውስጥ ምርቱን ከማነቃቃት እንዲሁም በአጉዋ እግድ ሳቢያ የተቀዛቀዘውን የውጭ ገበያ ለማገዝ አማራጭ ገበያ ለመፍጠር ሥራዎች ሲሠሩ እንደነበርም አስታውሰዋል።



ፎቶ - እዮብ ተፈሪ

ዐውደርዕዩ ከብዙ ሀገራት የመጡ አምራቾች እና ዲዛይነሮች የተሳተፉበት በመሆኑ ሁነቱን በማዘጋጀት በኩል ሚና ለነበራቸው አዘጋጆች እና ተባባሪ ባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበዋል። የተሳካ የፋሽን ትርዒት እንዲሆንም ተመኝተዋል።

በመክፈቻው ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የቱሪዝም ሚኒስትሯ ወይዘሮ ናሲሴ ጫሊ ከተለያዩ አገራት ለመጡ አምራቾች እና እንግዶች እንኳን ወደ ምድረ ቀደምት ሀገር በደህና መጣችሁ ብለዋል።

በእንግዳ ተቀባይነቷ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ይህንን ዓይነት ዐውደ ርዕይ በማዘጋጀቷ በቱሪዝም ዘርፍ ያላትን እምቅ አቅም ለመጠቀም እንደሚያስችላትም አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ከጥጥ የሚዘጋጁ ጋቢዎች፣ ነጠላዎች፣ ኩታ እና ቀሚሶች የማይዳሰሱ ቅርሶቿ ድምቀት እና የቱሪዝም አቅሟን የሚያሳድጉ መሆናቸውንም ጠቅሰዋል። ለባዛሩ ተሳታፊዎችም የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ አስደሳች ቆይታ እንዲኖራቸው ተመኝተዋል።

ከትላንት ጀምሮ ለአራት ቀናት የሚቆየው ዐውደ ርዕዩ ከ30 አገራት የተውጣጡ 200 ዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾችና ላኪዎች ምርቶቻቸውን የሚያሳዩበት ሲሆን ከ50 አገራት የሚመጡ ከ6000 በላይ ዲዛይነሮች እና ገዢዎች እንደሚሳተፉበት ይጠበቃል።

# ሰቆጣ ከተማ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚረዳ የጥገና ሥራ መጀመሩንም አገልግሎቱ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነቱ ምክንያት ለወራት በድቅድቅ ጨለማ ተውጣ የከረመችው ሰቆጣ ኤሌክትሪክ እንድታገኝ የሚደረገው የጥገና ሥራ ቀጥሏል።

በጥይት ተመተው የተበላሹ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮችንና የተበላሹ የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመሮችን የመተካት ሥራ በስፋት እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የአላማጣ-ሰቆጣ የ66 ኪሎ ቮልት የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና በሁለት ቀናት ውስጥ እንዳበቃ አስፈላጊው የፍተሻ ሥራ እንደሚከናወን ጠቁመዋል።

ከፍተሻው በኋላ የሰቆጣ ከተማና በዙሪያዋ የሚገኙ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ዳግም የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንደሚያገኙ ይጠበቃል ብለዋል።

በተመሳሳይ በጦርነቱ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን የሁመራና አካባቢው የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያና የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ጥገና ሥራ መጀመሩን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አቶ መላኩ አስታውቀዋል።

ከዚህ ቀደም በሁመራና አካባቢው የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያና ማስተላለፊያ ላይ የደረሰውን ጉዳት የመለየትና ዳግም አገልግሎት ለመጀመር የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የመለየት ሥራ ሲከናወን መቆየቱን አቶ መላኩ ገልጸዋል። ።

ከልየታ ሥራው በኋላ የተጎዱ መስመሮችን የመጠገን ተግባራት በመከናወን ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ በቀጣይ ቀናት የጥገና ሥራው ሲጠናቀቅ ሁመራና አካባቢው ዳግም የአሌክትሪክ አገልግሎት አገልግሎት የሚያገኙበት ዕድል እንደሚፈጠር አስረድተዋል።

የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ የሁመራና አካባቢው የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያ የመሠረተ ልማት ጥገናን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በጥምረት እያከናወኑት ይገኛል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከ66 ኪሎ ቮልት በታች ያሉትን የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያዎች ጥገና ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዛፎች ያረፉባቸውንና በመሣሪያ የተመቱ የኤሌክትሪክ መስመሮችን የመቀየር ሥራውም እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በጦርነቱ ምክንያት የተጎዱ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶችን የመጠገን ሥራውን እያከናወኑ የሚገኙ ባለሙያዎች አካባቢዎቹ ዳግም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ሥራቸውን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ቀንና ሌሊት አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

በአስቸጋሪ መልክዓ ምድርና ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ በቅንነትና በታታሪነት እየሠሩ ለሚገኙ ባለሙያዎች በተቋማችን ስም ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ ብለዋል ዳይሬክተሩ።

አቶ መላኩ እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማት ጥገና በተከናወነባቸው ቆቦ፣ ዋጃ፣ አላማጣ፣ ላሊበላና የተለያዩ አካባቢዎች ዳግም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማግኘታቸው የሚታወስ ነው።

# «የሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሰላም፣ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ማስጠበቅ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ስምምነቱ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያጸና በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ለተግባራዊነቱ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል።

ስምምነቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን የጋራ ጥቅም ባስከበረ መልኩ መጠናቀቁን ጠቁመው፤ በዚህም በአንድ ሉዓላዊ ሀገር ውስጥ ሁለት የታጠቀ ኃይል ሊኖር እንደማይችልና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበር እንደሚገባ ስምምነት ላይ ተደርሷል ብለዋል።

ከዚህ አኳያ ከሕገ-መንግሥት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች ቆመው በትግራይ ክልል በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ ጊዜያዊ አስተዳደር እንደሚቋቋም ተናግረዋል።

ያለን አማራጭ እና መፍትሔ በጋራ ተሳስሮ መሄድ ነው ያሉት አምባሳደር ሬድዋን፤ ከዚህ አኳያ ጉዳት የደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ከጉዳታቸው አገግመው ወደ ቀደመው ማኅበራዊ ትስስር እንዲመለሱ በጋራ ይሠራል ነው ያሉት።

የደረሰው ጉዳት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው÷ ከዚህ አኳያ የወደሙ ተቋማትን ጨምሮ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች በጋራ ርብርብ ሊከናወኑ ይገባል ብለዋል።

የትስስርና የተግባቦት ሥራዎችም የሕዝቦችን መጻኢ የጋራ ጉዞ ታሳቢ ያደረጉ ሊሆኑ እንደሚገባም አስረድተዋል።

ያሉንን አቅሞች በማስተባበር ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች መልሶ ለማቋቋም ርብርብ ማድረግ እንደሚገባም ነው የተናገሩት።

በግጭቱ ምክንያት በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲ እንዲሁም በሌሎች መስኮች የደረሰውን ጫና በማስተካከል ረገድም በትብብር መሥራት ይጠበቃል ብለዋል።

ከዚህ ረገድ በተለይ የመገናኛ ብዙኃን ቁርሾዎችን ማባባስ ሳይሆን ዜጎች ከችግሩ ተምረው በቀጣይ አብሮነታቸውን አጠናክረው የሚሄዱበትን ሁኔታ መፍጠር ላይ ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በግጭቱ የተጎዳችው የሁላችንም የጋራ ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ ናት ያሉት አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን÷ በመሆኑም ስምምነቱ በሁሉም ዜጎች ተሳትፎ ኢትዮጵያን ከፍ ለማድረግ ዕድል እንደሚፈጥር አንስተዋል።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሰላም ሂደቱን ለማደናቀፍ የሚሠሩ አካላትን ደግሞ በጋራ ማስቆም እንደሚገባ መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ሁሉም ዜጋ ለስምምነቱ ተግባራዊነት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ እንደሚገባም አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ጥሪ ማቅረባቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ከዚህ አኳያ መድረኩ የቀጣይ ስራዎች ትብብር ላይ ትኩረቱን ያደረገ ስለመሆኑም አብራርተዋል።

# ከስምምነቱ ማግስት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መቻሏን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ዘመዴነህ፣ የግድ ስለሆነ እንጂ ጦርነት የማንም ኢትዮጵያዊ ምርጫ አይደለም። ነገር ግን ለሁለት ዓመታት ያህል የዘለቀውና መተኪያ የሌለውን የሰው ሕይወት ያጠፋ እና የአገሪቱን ኢኮኖሚ ክፉኛ የጎዳውን ጦርነት በሰላም ከመቋጨት በላይ የሚያስደስት ነገር የለም።

ከዚህ አንጻር የአገሪቱን ሕልውና ለመታደግ ለሌሎች የልማት አውታሮች ይውል የነበረ በርካታ ገንዘብ ለጦርነቱ ለማዋል መገደዷን የጠቆሙት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ በሰላም ስምምነቱ መሠረት በአገሪቱ ሰላም ከሰፈነ ለጦርነት የሚውል ሀብት ወደ ልማት በማዞር የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ከመቅረፍ ጎን ለጎን ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ያለው ፋይዳ እጅግ የጎላ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ምናልባት የአገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ወደኋላ ሊመልሱ የሚችሉ በቢሊዮን ብር የሚቆጠሩ መሠረተ ልማቶች መውደማቸውን ያወሱት አቶ ዘመዴነህ፤ በአንጻሩ ደግሞ በስምምነቱ ምክንያት በብድርና በእርዳታ መልክ ለኢትዮጵያ ለመስጠት ታስቦ የተያዙ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ገንዘቦች ሊለቀቁ ስለሚችሉ አካባቢዎቹን መልሶ ከመገንባት በዘለለ ለኢኮኖሚ እድገቱ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ከፍተኛ መሆኑን አመልክተዋል።

አሜሪካ ኢትዮጵያ አጎዋ የሚባለው የነጻ ገበያ እድል ተጠቃሚ እንዳትሆን ማዕቀብ በመጣሏ ምክንያት ምርታቸውን በብዛት ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ እንደ ሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ያሉ ግዙፍ ፋብሪካዎች ላይ ከባድ ተጽዕኖ ከመፈጠሩን የተነሳ ባለሀብቶቹ አገር ለቀው ለመውጣት መፈለጋቸውን የተናገሩት አቶ ዘመዴነህ፤ ነገር ግን ሰሞኑን ከአሜሪካ ባለሀብቶች ጋር በተደረገው ውይይት የሀገሪቱ ሰላም ወደ ነበረበት ከተመለሰ የአጎዋን ችግር መፍታት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት ማሳየታቸውም ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዘመዴነህ ማብራሪያ፤ ከኮሮና ወረርሽኝና ከሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ችግር ዓለም አቀፋዊ ችግር ነው። በኢትዮጵያ ችግሩን ያጎላው ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ነው። ከዚህ በኋላ ጦርነቱን በማሳበብ በኢትዮጵያ ላይ የሚደረገው ጫና ስለሚቀለበስና ሀገሪቱ ፊቷን ወደ ልማት ስለምታዞር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በቀጣዩ ዓመት አሁን ካለው እጥፍ ማደጉ ምንም ጥርጥር የለኝም ብለዋል።

አቶ ዘመዴነህ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከዚህ በፊት የተጀመረውን የአገሪቱን ኢኮኖሚ የማሻሻል እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



## የሌማት ትሩፋት

ገጽ 8

## ከ6 ሺ በላይ

ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚገነባው የካሊድ-ዲጆ የመስኖ ፕሮጀክት

ገጽ 14



**«መንግስታችን እያለማ ያለው ስንዴ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም መመገብ ይችላል»**

- አቶ በንቲ ፉፋ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት የቦርድ አባል

ገጽ 6



## የፈገግታው ቋጠሮ ሲፈታ

ገጽ 17

## በውስጥ ገጾች

ከአሜን ማግሥት! ገጽ 9

ሰላምን ማብዛት ገጽ 12

# የዘመን እንግዳ

# “መንግስታችን እያለማ ያለው ስንዴ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም መመገብ ይችላል”

\- አቶ በንቲ ፉፋ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የተግባር ምክር ቤት የቦርድ አባል

ማሕሌት አብዱል

ትውልድም ሆነ እድገታቸው በቀድሞው አጠራር በሸዋ ክፍለ አገር በጅባትና ሜጫ አውራጃ በአንቦ ወረዳ ቶኬ በሚባል አካባቢ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ቶኬ ራስ መስፍን ስለሺና ዶኬ ኢሬሳ በተባሉ ትምህርት ቤቶች ነው የተማሩት፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ አምቦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከታተሉ ሲሆን የ11ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ወስደው ውጤታቸውን እየተጠበቁ ሳሉ ግን የአንደኛ ዙር ብሔራዊ ውትድርና ሲጀመር መሄድ አለብህ ተብለው ተይዘው ይታሰራሉ፡፡ ይሁንና ሌሊት ከእስር ቤት አምልጠው ከአካባቢዉ ተሰወሩና ለስድስት ወራት ያህል ቆዩ፡፡ ሁለተኛ ዙር ምልመላ ሲጀመር ግን ከወትድርና ማምለጥ እንደማይችሉ ተገነዘቡ፡፡ እናም ምድር ጦር ስፖርት ክለብ ውስጥ በነበረ የአክስታቸው ልጅ አማካኝነት ምድር ጦር ውስጥ በሚገኘው መቻል ስፖርት ክለብ ተቀጠሩ፡፡

በዚያ መሰረት አዳማ በሚገኘው ታንከኛ ማሰልጠኛ ክምፕ ውስጥ የውትድርና ትምህርት እንዲወስዱ ተላኩ፡፡ ለስድስት ወራት ውትድርና ትምህርታቸውን ተከታትለው ሲጨርሱ ወደ ምድር ጦር ስፖርት ክፍል ተመልሰው ለሶስት ወራት ያህል አገለገሉ፡፡ በመቀጠልም ወደ ሆለታ ገነት የመኮንኖች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የመኮንነት ትምህርት ለሁለት ዓመት ተከታተሉና በምክትል መቶ አለቃነት ተመረቁ፡፡ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ እዚያዉ ጦር ትምህርት ቤት አዲስ እጩ መኮንኖችን ስፖርት እንዲያሰለጥኑ ተመድበው ለሁለት ዓመታት አገለገሉ፡፡ ሙሉ መቶ አለቃ ሲሆኑ ደግሞ ወደ ምድር ጦር ስፖርት ክፍል ተመለሱና በአትሌትክስና በመረብ ኳስ ሲሳተፉ ቆዩ፡፡

ከስፖርቱ ጎን ለጎን የጤና ረዳት ኮርስ ወስደው እየሰሩ የነበሩት እንግዳችን በኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ላይ መፈንቅለ-መንግስት ተሞክሮ ሲከሽፍ ስፖርተኞች በሙያቸው ተመድበው ወደ ስራ ይግቡ ተባለና እሳቸውም ወደ ምድር ጦር መሳሪያ ጥገና እና እደሳ ግምጃ ቤት ተመደቡ፡፡ እዚያው እየሰሩ ሳለ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን መጣና ለአንድ ሳምንት ከተማው እስኪረጋጋ ድረስ እሳቸውም ሆነ ሌሎች ሰራተኞች እቤታቸው እንዲቆዩ ተደረገ፡፡ ከአንድ ሳምንት በኋላ የጤና ባለሙያና መካኒኮች ስራ እንዲጀምር ጥሪ ተደረገላቸውና ዳግመኛ ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ ይሁንና ሁኔታዎች እንዳሰቧቸው አልቀጠሉም፤ በሶማሊያ ጦርነት ወቅት የተበተኑ መሳሪያዎችን የመሰብሰብ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው በተላኩበት ወቅት ጓደኞቻቸው ተገድለው ጠበቋቸው፡፡

ይህ ሁኔታ እጅግ ተስፋ ያስቆረጣቸው እንግዳችን ስራቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን ትተው ጫካ ገቡ፡፡ የኦነግ አባል ሆነው መታገል እንደጀመሩ ያሰቡት አልጠበቃቸውም፤ የድርጅቱ አባላት እርስበርስ የተከፋፈሉና በመካከላቸው የሌላን አካል ተልዕኮ የሚያስፈፅሙ መሆናቸውን ተረዱ፡፡ በተለይ ደግሞ እሳቸው ነጻ አወጣዋለሁ ብለው ላሰቡት ንፁህ ህዝብ ይልቅ እርስበርስ የማይተማን ፖለቲከኛ መሆኑ ክፉኛ ያበሳጫቸው ስለነበር ተቋውሟቸውን ባገኙት አጋጣሚ ማንሳት ጀመሩ፡፡ ይህም በአንዳንድ የኦነግ አመራሮች ጥርስ ውስጥ አስገባቸው፡፡

በሌላ በኩል እሳቸው ጫካ ሳሉ በሕወሓት ተላላኪዎች በተደጋጋሚ የግድያ ሙከራ ተደርጎባቸውም ነበር፡፡ በኋላ ነገሩ እየባሰ ሲመጣ እየታገሉ ወደ ሱማሊያ ተሰደዱ፤ ቀጠሉም ኬኒያ ገቡ፡፡ በኬኒያ እያሉም በተደጋጋሚ የግድያ ሙከራ የተደረገባቸው እኚሁ ሰው ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በእንግሊዟ ለንደን ከተማ ኑሯቸውን አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ምክር ቤት የቦርድ አባል በመሆንም የአገራቸው ጠበቃና ዲፕሎማት በመሆን የምዕራባውያኑን ተፅዕኖ ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ ከእንግዳችን ጋር በወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ዙሪያ ቆይታ አድርገናል፡፡



**አዲስ ዘመን፡- ወደ ትግል የገቡበት አጋጣሚ ያስታወሱንና ውይይታችንን እንጀምር ?**

**አቶ በንቲ፡-** ደርግ ከወደቀና በጊዜው ከነበረው አገዛዝ ጋር ስራ ከጀመርኩኝ በኋላ በደርግ ጊዜ ከሱማሌ ጋር በተደረገው ጦርነት በምስራቅ ኢትዮጵያ ሄጄ የወደሙ መሳርያዎችን ሰብስበን ለመጠገን ከመካኒኮች ጋር ተልከን ነበር። በትዕዛዛችን መሰረትም 111 ታንኮችን ሰብስበን በመጠገን 68 ታንኮች ለስራ ዝግጁ አድርገን ከስድስት ወር ቆይታ በኋላ ታንኮቹን ወደ ድሬደዋ አመጣንና ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። አዲስ አበባ ከተመለስኩኝ በኋላም ሰላም ለማስከበር ቡሩንዲ እንደምሄድ ተነገረኝና ያንን ግዳጅ እየተጠባበኩኝ ሳለሁ በጣም የምወዳቸዉ ጓድኞቼ ተገደሉ። ለምን ተገደሉ? ብዬ ስጠይቅ መንግስት እንደገደላቸው ሰማሁኝ። በመሆኑም እነዚህ ሰዎች በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከቀጠሉ በኋላ እኔንም አይተውኝም ብዬ ኦነግን ተቀላቀልኩ። ወጣቶችን በማደራጀትና በማስታጠቅ በድብቅ በሜጫና ቱለማ ልማት ማህበር ስር የወጣቶች ምክትል ፕሬዚዳንት ሆኜ መስራት ጀመርኩኝ።

ታስቦ የነበረው ምርጫ ሊሳካ ባለመቻሉና ቻርተሩም በመፍረሱ ኦነግ ወደጫካ ተመለሰ። ከዚያ በኋላ በአዲስ አበባ፣ በወሊሶ፣ በአምቦ በስለላ ሰራዊት በማደራጀት የወቅቱን አገዛዝ መውጫና መግቢያ አሳጣናት። በዚህ አይነት እንቅስቃሴ ያደራጀነው ሰራዊት ቁጥር እየጨመረ እኔንም ክትትል ስለበዛብኝ ኦነግ ወደአለበት ሃረርጌ በረሃ ለመሄድ ወሰንኩኝ። እናም ለማንም ሳልናግር አንድ የሦስት ዓመትና የሁለት ወር ልጆቼን ለእናታቸው በመተው የነበረችኝን ስድስት ሺህ ብርና አንድ ቶዮታ መኪና በመያዝ ሶስት ሆነን ድሬደዋ ገባን። ድሬደዋ 15 ቀን ከቆየሁ በሁዋላ የመኪናዬን ቁልፍ አንዱን ለደጋፊዎች ከነመኪናዉ አንዱን ራሴ ይዤ ወደ በርሃ ገባሁ።

በርሃ ከደርስኩ በኋላ ቁልፉንና ገንዘቡን እዛ ቦታ ላይ ለሚገኘው አዛዥ ሰጥቼ የመጣሁበትን ምክንያትና በሸዋ ውስጥ በተለያየ ቦታ ሰራዊት አደራጅተን በወቅቱ ከነበረው አገዛዝ እየተፋለምን መሆናችንን አስረዳሁት። በኋላም አዲስ ምልምሎችን የማሰልጠን ኃላፊነት ተሰጥቶኝ ለሶስት ወራት አሰለጠንኩኝ። ሁለቱ ጓደኞቼ ግን ሌላ ቦታ ተመደቡ፤ እኔ እዛው ማሰልጠኛ ካምፕ ተመድቤ የተለያየ ውጊያዎች ላይ ብሳተፍም ምንም ጉዳት ሳይደርስብኝ ቆየሁኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በሕወሓት ተላላኪዎችም ሆነ በኦነግ ሰዎች የመግደል ሙከራ ተደርጎቦት እንደነበር ይታወቃል። እስቲ ይህን ያብራሩልን?**

**አቶ በንቲ፡-** ልክ ነሽ ። እ.ኤ.አ በ1994 የኦነግ ገዳይ ቡድን ሪሳ የሚባል ግሩፕ እኔና ጓደኛዬን ለመግደል ተልኮ ቢመጣም ሳይመቸው ቀርቶ ከግድያው አመለጥን። ሆኖም ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ለሶስተኛ ጊዜ ሊገሉን ተዘጋጅተው ሳለ እኔ በአጋጣሚ ወጥቼ አላገኙኝም፤ ጓደኛዬም ወደ ሰላሌ ሄዶ ስለነበረ እኛን ሲያጡን አልይ አደረ የሚባልና የጋላሳ ድልቦ ቀኝ እጅ የነበረን ሰው ገደሉት። እኔም አገር ሰላም ነው ከወጣሁበት ወደ ጫካ ስመለስ ያገኙኛል፤ አንደኛው ‹‹ከየት መጣህ?›› ብሎ ጠየቀኝ፤ እኔም የመጣሁት ከአዲስ አበባ መሆኑን ግን ደግሞ ትውልዴ አምቦ መሆኑን ስነግረው ደንግጦ ‹‹ወይኔ ወንድሜ! እራሴን በራሴ በልቼ ነበር፤ አንተና ኣብደታን ግደል ተብለን ከዚህ ጋር ሶስት ጊዜ አጣናቹ፤ እናንተን ስናጣ አልይ ኣዳሬን ገድለን መጣን›› አለኝ። እኔም ያላሰብኩት ስለነበር በጣም ደነገጥኩና ለምን ገደላችሁት ብዬ ስጠይቀው በኦሮሞ ስም የተደራጀ አብሶ የሚባል የተደራጀ ጠላት ቡድን ተልዕኮ ተሰጥቷቸው እንደሆነ ነገረኝ። መደንገጤን ያዩ ሌሎች አባላት ደግሞ በሳምንቱ መሳሪያዬን ተቀብለውኝ ‹‹ስምንት ቁጥር›› በሚባለው መንገድ አስረውኝ ቀጠቀጡኝ። በዚህ መልኩ ለሁለት ወር ታስሬ ከቆየሁ በኋላ ሌላ ቦታ ተልኬ እንድታከም ተደረኩኝ፤ ብታከምም ግን አሁንም ድረስ እጄ አይሰራም፤ ከባድ እቃ ማንሳት አልችልም።

የሚገርምሽ ከስድስት ወር በኋላ ደግሞ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ ጠርተውኝ ስለተደረገብኝ ነገር ይቅርታ ጠየቁኝ። ምንም ማድረግ ባልችልም ባደረጉት ትግል በሰራዊቱና በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅ ሆንኩኝ። አንድ ቀን በጊዜው ከነበረው አገዛዝ ጋር ባደረግነው እልህ አስጨራሽ ውጊያ እግሬ ላይ በሁለት ጥይት ተመታሁ። ከዚያ ውጭ ምንም ጉዳት ደርሶብኝ አያውቅም። በመጨረሻ እ.ኤ.አ በ1996 መጨረሻ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እኛን ለማጥፋት ዘመቻ ከፈቱብን፤ ያንን ዘመቻ መቋቋም አልቻልንም፤ አዛዦች በአንድ ወንዝ ውስጥ ሰብስበውን ‹‹የተከፈተብን ዘመቻ ከብዶብናል፤ ተበታትነን መኖር አለብን፤ ከሶስት ወር በኋላ እዚሁ እንገናኝ›› አሉን። ለካ አንዳንዶቹ ከአገዛዙ ጋር ይሰሩ ኖሮ እነሱ እንደሄዱ እኛ ከወንዙ ውስጥ ስንወጣ በጠላት ተከበብን፤ ውጊያ ጀመርን ያለቀው አለቀ፤ ሌላው ተበታተነ፤ እኔም ብቻዬን ቀረሁኝ። ለሶስት ወራት በባሌ ተራራና ቆላማ ስንከራተት የሚበላ አጥቼ ቁልቋል እየበላሁ ቆየሁኝ። በመጨረሻ ግን ቁልቋሉም ጠፋ፤ መሬቱ ሁሉ ደረቀ፤ ራሃቡ ሲጠናብኝ ሃያ የተባለ አፈር እየበላሁ በየቦታው ተደብቀው ያሉትን

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ቁስለኞች ማሰባሰብ ጀመርኩኝ።

የዚያዉ አካባቢ ተበትነው የገቡ 68 ልጆች ይዤ ወደ ሱማሌ ጉዞ ጀመርን። በጣም የሚገርምሽ በጉዞ ላይ ሆነንም አንድም የምንበላው ምግብ የለንም ነበር። ለ28 ቀናት በቅጠልና በውሃ ብቻ ተጉዘን የሱማሌ ድንበር ስናቋርጥ በሁለት ክላሽ ጠመንጃ አንድ ግመል ገዝተን በላን። በዚያው እለት ሁለት ልጆች ሞቱብን፤ ከዚያ በፊት ደግሞ ሕወሓት ከፊታችን ጠብቆን ተኩስ ከፈተብን ሶስቱ ልጆች ሞተውብን ነበር። በኋላም ከበባውን ሰብረን ወጣንና በ32ኛ ቀናች ሁዱር የምትባልና በሁሴን አይዲድ የምትቆጣጠር የሱማሌ ድንበር ላይ የምትገኝ ከተማ ገባንና ሱማሌዎች ተረከቡን።

ሱማሌ ከገባን በኋላ ጠፍተው የነበሩት አዛገሮች ከአሜሪካና ከአውሮፖ ሞቃዲሾ ላይ ተሰብስበው ምርጫ አካሄዱ። ከዚያ በኋላ ግን እኔ እንድገደል ሰው ተላከብኝ፤ ሆኖም አስቀድሞ መረጃ ስለደረሰኝ ሊገድሉኝ የመጡት ከሰራዊቱ ውስጥ ቢጠሩኝም ወደ እነሱ ሳልሄድ በሩጫ አመለጥኳቸዉ። ተኩሰውም ኣላገኙኝም። በሶስት ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘው ከሄድኩኝ በኋላ ሁሴን አይዲድ አይሮፕላን ልኮልኝ ወደ ሞቃድሾ ወሰደኝ። በኋላም ጉዳያችን በሽምግልና እንዲያልቅ ተደረገ፤ ይቅርታም ተጠየኩኝ።

እ.ኤ.አ በ1999 ደግሞ ከውጭ ሀገር ሰራዊትና መሳሪያ ሲመጣልን ይህንን ሰራዊት ይዘን ወደ ኢትዮጵያ እንመለስ ብለን ጥያቄ ስናቀርብ እናንተ አትመለሱም ብለውን ያንን ሰራዊት ቤዳቦ የምትባል ቦታ ወስደው አስጨረሱት። ከዚያ በኋላ እኔም ከትግሉ ተስፋ ቆርጬ ትቼ ወጣው። ሆኖም አሁንም እንድገደል ወስነው ማሳዳዳቸውን አላቆሙም ነበር። ግን ሊያገኙኝ አልቻሉም። ኬኒያ ናይሮቢ ከገባሁኝ በኋላም ከመታሰር ጀምሮ በጥይት ሶስት ጊዜ በላይ የመግደል ሙከራ ተደርጎብኛል። አንድ ጊዜ እንዳውም በሁለት ጥይት በግራ በኩል ከጡቴ በላይ ተመትቼ አሁን ድረስ ጉዳቱ ብዙ ችግር አድርሶብኛል። ወደ እንግሊዝ ለመሄድ አንድ ወር ሲቀረኝ መርዝ አጠጥተውኝ ሆስፒታል ገብቼ ተርፌያለሁ። አሁን በምኖርበት አገር ሳይቀር ተደራጅተው መጥተውብኝ አዋርጂ ነው የመለስኳቸው። እስካሁን በርካታ የግድያ ሙከራዎች ቢደረጉብኝም ፈጣሪ እንደሰው ባለመሆኑና እሱ ከፈቀደው ቀን ውጭ ሊሆን ስለማይችል እስካሁን በህይወት አለሁኝ።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ የውጭ ኃይሎች የሚፈጽሙት ሴራና በመንግስት ላይ የሚያደርጉት ጫና በእርሶ እምነት የምን ፍላጎት ነው?**

**አቶ በንቲ፡-** በእኔ እምነት የውጭ ጠላቶቻችን አንድ እንዳንሆን፤ እንዳንስማማ፣ ወደ ልማት እንዳንገባ፤ እንዳንማርና ከመሃይምነት እንዳንወጣ ያደረጉት ከጥንትም ቢሆን በአባቶቻችን በአድዋ ላይ ድባቅ በመመታታቸው ቂም ስለያዙብን ነው። ይህቺ ደሃ ሃገር ትላንት አዋርዳናለች፤ ለዘመናት ለእኛ ሳትገዛ ነው የኖረችው፤ አሁንም የእኛ ትዕዛዝ የማትቀበልናት በሚል በቂም በቀል ተነሳስተው የሚያደርጉት ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ የጂኦግራፊያዊ አቀማመጧ ሌላውን አገር ለመቆጣጠር የሚያስችል ስትራቴጂካዊ ቦታ ላይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ካመለጠቻቸው አፍሪካ ላይ እንደፈለጉ መሽከርከር እንደማይችሉ ስለተገነዘቡ ነው። በመሆኑም አሁን ላይ የደከመች፤ የተሰባበረችና የተበታተነች ኢትዮጵያ እንድትሆን በጠላትነት መንፈስ የሚያደርጉት ነው።

እኛ ራሳችንን ከቻልና እና ከድህነት ከወጣን ለሃያላኑ አንታዘዝም፤ እርዳታቸውንም አንፈልግም። ይህ ሲሆን ደግሞ እነሱ ኑሯቸው፤ ኢኮኖሚያቸው የተመሰረተው በአፍሪካ ላይ ስለሆነ ያንን ያጣሉ። በተጨማሪም ትላንትም አባቶቻችን ድል እንዳደረጓቸው እኛም ድል ስናደርጋቸው በዚህ የተነሳ እኛ ደግሞ በተራቸው ማንበርከክ አለብን በሚል ነው ዓላማችንን ይፈጽሙልናል የሚሏቸውን ኃይሎች ተላላኪ አድርገው ሲጠቁሙባቸው የቆዩት። በአድዋ ላይ ጥለውት የሄዱትን የከፋት ዘር አሁንም ከመቶ ዓመት በኋላ ለመድገም እየሰሩ ነው ያሉት። በተለይ ለውጡ ሲመጣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቁጭት ከድህነት መውጣት አለብን ብሎ ሲነሳ ከድህነት እንዳንወጣና የእነሱን ፍላጎት ብቻ እንድናስፈፅም ሲሉ የማይምሱት ጉድጓድ የለም። እርግጥ ነው ተላላኪ መንግሥት በነበረበት ዘመን ቅኝ አልተገዛንም ብንልም በስውር በተላላኪዎቻቸው አማካኝነት ተገዝተን ነው የኖርነው። ለውጡ ሲመጣ ግን ይህንን ማስቀጠል ስላልቻሉ ነው እንቅልፍ አጥተው እያተራመሱን ያሉት።

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ኃይሎች ጫና በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት እያየለ መጥቷል። በዋናነትም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ በውስጥ ጉዳይ ላይ እያደረጉት ያሉትን ጣልቃ ገብነት እንዴት ያዩታል?**

**አቶ በንቲ፡-** አንዳንድ የምዕራቡ አገራት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ጣልቃ የሚገቡት፤ በተለይ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ጫና እያደረጉ ያሉት ለኢትዮጵያ ህዝብ አስበው ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም መከበር እንደሆነ ግልፅ ነው። በሚል ነው። ምክንያቱም እነሱ ህዝብ የመረጠውን መንግስት አንቀበልም ብለው ትናንትም በስውር ሲያስተዳድሩን የነበረው በዚህ በተላላኪዎች አማካኝነት ስለነበረና የእሱ መውደቅ ደግሞ እነሱ ተልዕኳቸውን እንዳይፈፅም ስለሚያደርጋቸው ነው። በመሆኑም ከእነሱ አስተዳደር ውጭ መኖር አትችሉም በሚል ሊገዙን፤ ሊያንበረክኩን ይፈልጋሉ፤ እኛ ደግሞ አንገዛም ብለን ሉዓዊነታችንን ላለማስደፈር እየታገልን ነው ያለነው።

አስቀድሜ እንዳልኩሽ ልዩነት እንዲኖረን ያደረጉት እነሱ ናቸው። አሁንም በዚህ ጦርነት የምዕራባውያኑ ፍላጎትና አላማ ገሃድ ወጥቷል። ደጋግመው የኢትዮጵያ ጉዳይ አጀንዳ የሚያደርጉት የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት የሚሉትን ለማስታጠቅና ህይወት ለመዝራት ነው እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብ ብሎም ለትግራይ ህዝብ አስበው አይደለም። ይሁንና ጠላቶቻችን መመከት የምንችለው አንድ ሆነን በፍቅር ስንቆም ነው። አንድነታችንን እስካጠነከርን ድረስ ግን ተፅዕኖው ሊጎዳን አይችልም።

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ተፅዕኖውን በመከላከል ረገድ ዲያስፖራው ምን እየሰራ ነው፣ ምንስ ይጠበቅበታል?**

**አቶ በንቲ፡-** በዲያስፖራው በኩል በመጀመሪያ ይሄ ለውጥ ሲመጣ በጣም ደስ የሚል አንድነት ፍቅር ኃይል ነበረን። እንደሚታወቀው ጠላቶቻችን በመካከላችን በረጨብን መርዝ ምክንያት ከፊሉ በመንግስት ላይ ያኮረፉ ነበሩ። ሌላው ደግሞ ፖለቲከኞች «እኔ አውቅልሃለሁ» በሚል በጎሰኝነት እንድንከፋፈል አድርገውን ነበር። ይሁንና የጠላቶቻችንን ሴራ እንዲጋለጥ በዲያስፖራው የተግባር ምክር ቤትም ሆነ ሌሎች አካላት ካደረጉ በኋላ አሁን ላይ አብዛኛው ዲያስፖራ ወደ አንድ መንፈስ መጥቷል። ከዚያም አልፈን በአገራችን አንድነት አንደራደርም ብለን፤ በአንድነት ቆመን በሰላማዊ ሰልፍ፤ እውቀት ያለው በእውቀቱ፤ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፤ ጉልበት ያለውም በጉልበቱ እየተባበርን አብረን እየሰራን ነው። ውጭ ከምናደርገው ትግል ባሻገር መከላከያችንና ህዝባችንን ለመደገፍ የተግባር ምክር ቤቱ አባላት በተለያየ ዙር አገር ቤት ድረስ በመምጣት አጋርነቱን አረጋግጧል። ምክር ቤቱ ጠላቶቻንን «ኢትዮጵያ ፈርሳለች፤ አገሪቱን ለቃችሁ ውጡ» እያሉ የሃሰት ፕሮፖጋዳ በሚነዙበት ወቅት የዲያስፖራ ምክር ቤት አሰባስቦ 500 የሚሆኑ የዲያስፖራ አባላትን ይዞ መጥቷል። ከዚያም ጠቅላይ ሚኒስትራችን ባቀረቡት ጥሪ መሰረት አባቶቻችን ወደ አገራቸው ገብተው አጋርነታቸውን አሳይተዋል። ይህም ለኢትዮጵያ መፍረስ ጉድጓድ ሲቆፍሩ የነበሩ ጠላቶቻችንን አሸነፍን ማለት ነው። ህዝባችንን ለመከፋፈል የሚፈልጉ የጠላቶቻችንን ተላላኪዎችና ፖለቲከኞች ነን ባዮች እቅድ ሊሳካላቸው አልቻለም። እኛም በየሚዲያዎቹ እየዞርን ህዝባችንን እያስተማርን ነው። ፈጣሪ ይመስገን አሁን ላይ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው ዲያስፖራ ወደአንድነትና ፍቅር መጥቷል። ቀን ከሌሊት ሳይል ስራውንም ሆነ የግል ህይወቱን በመተው ለአገሩ ጥቅም ዘብ የቆመበት ጊዜ ነው ያለነው። በቀጣይም ይኸው ትግላችንን ተጠናክሮ ነው የሚቀጥለው።

በየሚዲያው ላይ እንደሰማሽው ደግሞ አንዳንድ አገራት እያደረጉ ያሉትን ጣልቃ ገብነት እንዲያቆሙ በያለበት አገር ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ተቋውሞውን እያሰማ ነው። በቀጣይም በአሜሪካና በሌሎችም አገራት ተመሳሳይ ልክ እንደ «No More» አይነት ከባድ ነውጥ የሚያስነሳ የተቃውሞ ሰልፍ ይካሄዳል። በተለይ እኛ በምኖርበት አገር ለንደን ከተማ ላይ ከፍተኛ የሆነና በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ የሚሳተፍበት የተቋውሞ



ሰልፍ ለማካሄድ ዝግጅታችንን አጠናቀናል። ከሁሉም አቅጣጫ አገራቸውን የሚወዱ ኢትዮጵያውያኖች ድጋፋቸውን እያረጋገጡልን ነው ያሉት። በእውቀታቸውና ጉልበታቸውና ገንዘባቸውን ሳይሰስቱ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው። ህዝባችን ለዚህ ቆርጦ ተነስቷል። ትልቁ ነገር ምንድን ነው አገር ቤት ውስጥ ያሉትም፤ ውጭ ያሉትም በመናበብ እየሰራን መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል ግን ዲያስፖራው በአገሩ ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ሲመጣ አንዳንድ በመንግስት ስር የተሸጎጡ አካላት በቢሮክራሲና በሙስና አማርረው ያመጣውን ገንዘብ እንዲያጠፋ አድርገው ያለምንም ውጤት ተመልሶ እንዲወጣ ያደረጉበት ሁኔታ አለ። ይህም ቁጥሩ ቀላል የማይባለውን ዲያስፖራ አስኮርፎታል። ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ላይ ጥላቻና ዘመቻ ወሬ መንዛት ጀምረው ነበር። ይህም ማለት መንግስት ውስጥ ያሉ ሰዎች ህዝብ ወደ መንግስት እንዳይቀርብ ያደረጉበት ሁኔታ ፈጥሮ ነበር።

ይሁንና በዲያስፖራው ምክር ቤት አማካኝነት ይህንን አጀንዳ ለዲያስፖራው ያቀበለውና ዲያስፖራው በመንግስት ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደረገውን ጠላት ሴራ በማጋለጥ ከፍተኛ ርብርብ አድርገናል። አሁን ላይ ብዙዎቹ ሴራውንና ያለውን ችግር ተረድተው ከዚህ ተግባራቸው ታቅበዋል፤ ተመልሰውም አገራቸውን በመደገፍ ላይ ነው የሚገኙት።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በምግብ እህል ራሷን ለመቻል በተለይ የስንዴን ምርታማነት እያሳደገች ነው። ይህ የልማት ስራ ያሳስደሰታቸው የምዕራቡ አገራት በኢኮኖሚ ደረጃ እያደረጉ ያሉትን አሻጥር እንዴት ያዩታል?**

**አቶ በንቲ፡-** በነገራችን ላይ የስንዴው ልማት ብቻ አይደለም ሌሎችንም የልማት ስራዎች ማስፋት ይገባናል። ምክንያቱም እርዳታ ጠባቂ የሆነ መንግስትና ህዝብ መቼም ቢሆን በሁለት እግሩ መቆም አይችልም። የሚገርመው ነገር በአፍሪካ ውስጥ ጥሬ ሃብቷ ያልተበላው ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ይህንን ጥሬ ሃብት ትኩስና ወጣት ሃብት እያለን እስከዛሬ መለመናችን በራሱ ሊያሳፍረንና ሊያስቆጨን ይገባል። በእርግጥ የነበረው አስተዳደር በራሱ የሚኖረው አስተዋፅኦ አለ። በንጉሱ ጊዜ የቴክኖሎጂ አቅማችን ወደኋላ አስቀርቶናል፤ በደርግ ዘመን ኮሎኔል መንግስቱ አጋዥ አላገኙም ነበር። በነገራችን ላይ መንግስቱ ሃይለማርያም ሲናገሩ የነበሩት ሁሉ አሁን በተግባር እያየነው ነው ያለው። እሳቸው ለአገራቸው ብዙ ራዕይ ቢኖራቸውም አሁን እንደምናየው በምዕራባውያኑ ተንኮል ከአገራቸው ወጡ።

ስለዚህ አሁንም መንግስታችን እያለማ ያለው ስንዴ አይደለም ኢትዮጵያን አፍሪካንም ጭምር መመገብ ይችላል። ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መንግስት ለምን ይህንን አላደረገም ከሚል እኔ ምን አደረኩኝ ለዚህች አገር ብሎ ራሱን ሊጠይቅ ይገባል። ይህንን ማድረግ ከቻልን እንለወጣለን፤ ከጠባቂነት ወጥተን እናድጋለን፤ ከማንም ጋር ደረታችንን ነፍተን የምንኖርበት ሁኔታ ይፈጠራል ባይ ነኝ። እኛ ኢትዮጵውያን ነን፤ ቀኝ አልተገዛንም፤ አንገዛም፤ ትላንት ረሃብተኛና መሃይም ያደረጋችሁን እናንተ ናችሁ። አሁን ነቅተናል፤ ከችግር ለመውጣት በራሳችን እንቆማለን ከሚያከብሩን ጋር ኃይላችንን አጠናክረን እንቆማለን። ከማንኛው ጠላት ጋር ተጋፍጠን የአገራችን ህልውና እናስጠብቃለን።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ በንቲ፡-** እኔም እንግዳችሁ ስላደረጋችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# የሌማት ትሩፋት

እፀገነት አክሊሉ



ስንዴ፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ ሙዝ እንዲሁም ሌሎች አገራችን የምታመርታቸው ጤናማ የሆኑና ጤናንም ለመጠበቅ ትልቅ አቅም ያላቸው ስለመሆናቸው ተደጋግሞ ይነሳል። መነሳትም ብቻ ሳይሆን ሁሉም አንደ አቅሙ ከገበታው ባይለያቸው ተብሎም በጤና ባለሙያዎች ይመከራል። መንግስትም ግሪን ሌጋሲ በሚል እነዚህ ምርቶች አንድም ከጤና በረከታቸው ሁለትም በምግብ እህል እራስን ከመቻል አንጻር ይለመዱ ይዘወተሩ ባህልም ይሆኑ ዘንድ ሰፋ ያለ ስራን እየሰራባቸው ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ከሰሞኑ በምድረገነቷ አርባ ምንጭ ከተማ ላይ በመገኘት "የሌማት ቱርፋትን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ" ይፋ አድርገዋል። ይህ የሌማት ቱሩፋት አገራችን ውስጥ የሚመረቱ ለጤናም በምግብ እህል ራስን ከመቻል አኳያም ከፍ ያለ ጥቅም ይኖራቸዋል የተባሉ የአትክልትና ፍራፍሬ አይነቶችን ለማስለመድ አዲስ የልማት ዘመቻ የሚጀመርበት ነው።

እስከ ዛሬ ጤናማ ያልሆኑ እንደ ስኳር፣ በመደበኛ የቤት ውስጥ ሙቀት የሚረጋ ዘይትና የአትክልት ቅቤ፣ የጨው መጠናቸው የበዛባቸው ምግቦችና መጠጦች፤ አዘውትረን በመመገባችን በዓለም ላይ እየተንሰራፉ ለመጡት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችና ለሌሎች የጤና ችግሮች ተጋላጭ ሆነን ቆይተናል። በሌላ በኩልም ፈጣንና በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምግቦችን አብዝተን መጠቀማችንም ለልብና የደም ቧንቧ በሽታዎች የልብ ድካምና ስትሮክ፣ ካንሰር፣ ሥር የሰደዱ የመተንፈሻ አካላት ህመሞች እንዲሁም ሥር ለሰደደ የሳምባ ምችና አስም። የስኳር በሽታም አጋልጦናል።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ብዙ ሰዎች በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምግቦችን ገዝቶ የመጠቀም ልምድ እያደበሩ በመሆኑም እነሱን ለማከም አገር ከፍ ያለ ወጪ ውስጥም ወድቃለች።

እ.ኤ.አ. በ 2019 በአገሪቱ የተመዘገበው 39 ነጥብ 2 በመቶ አጠቃላይ ሞት ተላላፊ ባልሆኑ ህመሞች ማለትም እንደ ልብ፣ ስትሮክ፣ የስኳር በሽታና ካንሰር ባሉ ሥር በሰደዱ በሽታዎች ምክንያት መሆኑን የጤና ሚኒስቴር መረጃዎች ያመላክታሉ።

በ2017 ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች አጠቃላይ የመንግስት ወጪም 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የነበረ ሲሆን በዚሁ ዓመት ይህ ወጪ ደግሞ 31 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የኢኮኖሚ ኪሳራ እንዳደረሰም ነው መረጃው የሚያመለክቱት። ይህም ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት 1 ነጥብ 84 በመቶ አካባቢ ይይዛል እንደማለት ነው።

አብዛኛዎቹ ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ጤናማ ባልሆነ አመጋገባችን ምክንያት የሚከሰቱብን መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ጤናማ የአመጋገብ ልማድን በመከተል ራሳችንና ቤተሰባችንን ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች መከላከልም እንዲሁም እንደ አገር የተያዘውን የግሪን ሌጋሲ ዘመቻ ተግባራዊ እያደረግን በአገራችን ምርት መጠቀምን መልመድ የሁሉም ኃላፊነት ነው።

የስነ ምግብና የህክምና ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ዘላለም ደበበም አለማችን ላይ ጤናማ ያልሆኑ አመጋገቦች የሰውን ልጆች እየጎዱ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስር እንዲሰዱ ምክንያት እየሆኑና ሰዎች ያለ እድሜያቸው እንዲሞቱ እያስገደዱ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

ጤናማ ያልሆኑ አመጋገቦች ከተፈጥሮ ውጪ በሆኑ ምርቶች የተዋቀረ ምግብን አዘውትሮ መመገብ ማለት ነው፤ የሚሉት ዶክተር ዘላለም ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ አደጋዎች ብዙ ናቸው።. አካላዊ እና አእምሯዊ እድገታችን በምንመገባቸው ንጥረ-ምግቦች ላይ የተመሰረተ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሚዛናዊ እና ጤናማ ያልሆነ እድገት እንዲፈጠር ያደርግል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በልጆችና በታዳጊዎች ላይ የጎላ ተጽዕኖን ይፈጥራል፡፡

በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምርቶች፣ የማምረቻ ሂደት ያላቸው ኬሚካሎች፣ ጣዕምን የሚያሻሽሉ ንጥረ ነገሮች፣ ማቅለሚያዎች ለጤና አደገኛ የሆኑ ሁሉንም አይነት ንጥረ ነገሮችን ያካትታሉ ይላሉ። እነዚህ ምግቦች ደግሞ በአጭርና በረጅም ጊዜ በጤና ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ከማድረሳቸውም በላይ በተለይ በልጆች ዘንድ ሱስ የመሆን ሂደታቸው ሰፊ ነው።

ከጥቂት አሥርተ ዓመታት በፊት የኢንዱስትሪ መጋገሪያዎች በስኳር የተሞሉ ኬኮች ጣዕም የሚያሻሽሉ ንጥረ ነገሮች ፋሽን አድርገው ነበር የሚሉት ዶክተር ዘላለም፤ እነዚህ ምርቶች በልጆች አመጋገብ ውስጥ እየተለመዱም መምጣታቸው ግን አሁንም በልጆቻችን አካላዊና አእምሯዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ከማሳደሩም በላይ አዋቂዎችም በማዘውተራቸው ምክንያት ከላይ ለገለጽናቸው ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች መበራከት የራሳቸውን ሚና እየተወጡ መሆኑን ያብራራሉ።

እንደ ዶክተር ዘላለም ገለጻ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ምግብ በሚሰጡ ሬስቶራንቶች የሚዘጋጁ ምግቦች እጅግ የተቀነባበሩና ምግቡን ለማዘጋጀት ተጨማሪ ጊዜን እንዳይወስዱ በፍጥነት የሚዘጋጁ ናቸው። የዚህ አይነት ምርቶች በቅባት የተሞሉ በመሆናቸው ጤናማ አይደሉም።

እነዚህ ምርቶች ጣዕምን የሚያሻሽሉ፣ የበለፀጉ እና ለመመገብ ቀላል የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ይዘዋል የሚሉት ዶክተር ዘላለም ለዚህም ነው ሱስ የሚያስይዙት፤ ሲበሉም መጠናቸውን ለመወሰን አስቸጋሪ የሚሆነው፤ ነገር ግን ጨዋማ መክሰስ መብላት ከፈለጉ የተጠበሱ ፍራፍሬዎችን መምረጥ ተገቢ ስለመሆኑም ይናገራሉ።

በምድጃ ውስጥ ቀድመው የበሰሉ ምርቶች መኖራቸው ገንቢ እና ጤናማ ምግብ ለማዘጋጀት ጊዜ ለሌላቸው መፍትሄ ነው። የቀዘቀዙ ምግቦች በአብዛኛው ከፍተኛ መጠን ያለው የሳቹሬትድ ስብ ይይዛሉ እና በዘይት መቀቀል አለባቸው ይህም ተጨማሪ ስብን ይጨምራል በዚህ ምክንያት አስቀድመው የተዘጋጁ ምግቦች ጤናማ ምግብ አይደሉምና የቤተሰብ አመጋገብ አካል መሆን የለባቸውም ብለዋል፡፡

ጤናማ አመጋገብ እንዲኖረን የሚያደርጉ የተፈጥሮ ምርቶች ናቸው። ፍራፍሬዎች፣ አትክልት፣ ሁሉም ዓይነት ሥጋ፣ ዓሳ፣ የወተት ተዋጽኦዎች፣ እንቁላል፣ ጥራጥሬ፣ ናቸው። በአጭሩ፣ አንዳንድ የአመጋገብ አስተዋፅዖ ያላቸው ከሁሉም ቡድኖች የተውጣጡ ምግቦች ማለት ናቸው።

ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ የሚጀምረው ምግቡን ካለመመጠን ነው የሚሉት ዶክተር ዘላለም የምንመገበው ምግብ ወይ በዝቷል አልያም በቂ አይደለም፤ ለምሳሌ ያልተፈተጉ ብለን የምንላቸውና ኮልስትሮልን ጨምሮ በርካታ ህመሞችን የሚከላከሉልን ምግቦች በዕለት ተዕለት አመጋገባችን ውስጥ ከሌሉ ወይም በቂ ካልሆኑ፤ ፍራፍሬና አትክልቶችን ከገበታችን የማናካትት ከሆነ፤ ፈሳሽ በበቂ ሁኔታ ካልጠጣን፤ በቂ እንቅስቃሴ እናደርጋለን ወይ የሚሉት ዋና ዋና ሀሳቦች መሆናቸውን ይናገራሉ።

## ጤናማ አመጋገብ እንዲኖረን የሚያደርጉ የተፈጥሮ ምርቶች ናቸው

በሌላ በኩልም በእለት ተዕለት አመጋገባችን ላይ ጨው። ቅባት፤ ስኳር ያለመጠን የበዛባቸውን የምግብ አይነቶች የምናዘወትር ከሆነም በራሱ ጤናማ ያልሆነ የአመጋገብ አካሄድ ከመሆኑም በላይ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የመጋለጥ እድልንም በእጥፍ የሚጨምሩ መሆናቸውን ዶክተር ዘላለም ይናገራሉ።

ዶክተር ዘላለም እንደሚናገሩት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ተላላፊ ላልሆኑ ህመሞች በተለይም ለልብ ህመም፤ ለስኳር፤ ለሳምባ ምችና ለካንሰር ህመሞች ዋና መነሻ ተብለው የሚጠቀሱት ጤናማና በቂ ያልሆኑ የአመጋገብ ልምዶች መሆናቸውን ያብራራሉ።

በአገራችን እነዚህ ህመሞች ቀደም ባለው ጊዜ የሀብታም ህመም ይባሉ ነበር፤ አሁን ላይ ግን በጣም በርካቶች በዚህ ህመም እየተጎዱ ነው፤ ነገር ግን እነዚህ ህመሞች እንዳይከሰቱ የሚያስችሉ መረጃዎችን በማግኘት በኩልም ሰፊ ክፍተቶች አሉ።

አሁን ላይ ጤናማ ባልሆነ አመጋገባችን ከሚመጡ ህመሞች መካከል ስኳር ከጠቅላላው ማህበረሰባችን 4 በመቶ ያህሉን ያጠቃል፤ ይህ አሃዝ ደግሞ በዋና ዋና ከተሞች ላይ ቁጥሩ ከፍ ይላል፤ ልብና የደም መዘዋወሪያ ህመሞች በቀጣይነት ትልቁን የጉዳት መጠን የሚያስከትሉ ናቸው። ጉዳታቸው ደግሞ ከፍ የሚለው ከፍ ያለ የህመም ደረጃ ላይ እስከሚደርሱ ድረስ ምንም አይነት የህመም ምልክት አለማሳየታቸው ነው። በመሆኑም እንደ አገር ከሚሞተው የሰው ቁጥር መካከል 52 በመቶው በእነዚህ ህመሞች የሚሞት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 8 በመቶው በቂ ምግብ ወይንም ደግሞ ጤናማ የአመጋገብ ስርዓትን ባለመከተል የሚደርስ ነው ይላሉ ዶክተር ዘላለም።

ጤናማ ባልሆነ አመጋገባችን ምክንያት የሚከሰቱትን ህመሞች ለማከም ደግሞ አገርም ብዙ ሃብትን ሙአለንዋይ ታፈሳለች የሚሉት ዶክተር ዘላለም ለህክምና ከሚወጣው በላይ አምራቹ ኃይል ታሞ እቤት በመቅረቱ በስራ ገበታው ላይ ባለመገኘቱ ቢገኝም ውጤታማ ስራን መስራት ባለመቻሉ ብሎም በመሞቱ የምታጣው ብዙ ነው በማለት ያስረዳሉ።

ዶክተር ዘላለም እንደሚሉት መጀመሪያ ልናደርግ የሚገባን ነገር ችግሩ ምኑ ጋር ነው? የሚለውን ማየት ነው፡፡ ይህንን ካወቅን በራሳችን የምንሄድባቸው ርምጃዎች ውጤታማ ያደርጉናል። በሌላ በኩል መረጃዎችን መከታተል የጤና ባለሙያ ምክርን መተግበር ያስፈልጋል። ጤናማ ያልሆነን አመጋገባችንን ለማስተካከል መከተል ካለብን ነገር አንዱ አትክልትና ፍራፍሬን ከምግባችን ውስጥ አለመለየት ነው፡፡ በዚህም በቀን ቢያንስ 400 መቶ ግራም መመገብ በህክምናው ተመካሪ ነው የሚሉት ዶክተር ዘላለም ይህ ማለት ምናልባት ሁለት ሙዝ ወይም አንድ ብርቱካን አንድ ሙዝ ሊሆን ይችላል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጎመን፣ ካሮት፣ ቆስጣ፣ ሰላጣ፣ ቀይ ስር ያሉትን አትክልቶች በምግባችን ውስጥ በማካተት ጤናችንን መጠበቅ ይገባል ባይ ናቸው። ሌላው መክሰስ ተብሎ ወይንም ደግሞ በመንገድ ላይ ስንጓዝ ደከም ሲለን ከመንገዱ ዳርቻ ገዝተን የምንመገባቸው ምግቦች በጣም ጤናማ ያልሆኑ ከመሆናቸው የተነሳ በመንገድ ላይ የሚሸጡ ምግቦችን ማስወገድን ይመክራሉ።

ዶክተር ዘላለም እንደሚሉት የፋብሪካ ውጤቶች የሆኑ ምግቦችን ተወት በማድረግ በቤታችን የሚዘጋጁ ከተቻለም ደግሞ አሰር ያላቸውን ምግብ ማዘውተር በጣም አስፈላጊ መሆኑን በመናገር በአገራችን ተፈጥሯዊና ጥሩ የምግብነት ይዘት ያላቸውን እንደ አቮካዶ፣አቾሎኒ፣ ተልባ፣ድብርቅ፣ ጥቁር አዝሙድ በመጠቀም ምግባችንን ማስተካከል ይገባናል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የትኛውንም አይነት ምግብ ተመግበን ቁጭ ማለት ገዳይ ነው የሚሉት ዶክተር ዘላለም በቀንም ቢያንስ ለግማሽ ሰዓት እንቅስቃሴን ማድረግ ይገባል።

ከአመጋገባችን አንዱና ዋናው ልናስወግደው የሚገባው ነገር ጨው ነው፤ ይህም ሲባል አንድ አዋቂ ሰው በቀን በጣም ቢበዛ ከሚመገባቸው ምግቦች ከአንድ የሻይ ማንኪያ በላይ ጨው መጠቀም አያስፈልገውም። ጨውን መቀነስ ደግሞ ጤናን በማሻሻል በኩል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው ይላሉ ዶክተር ዘላለም።

ስኳርም በተመሳሳይ ለአንድ አዋቂ ሰው በቀን ከአምስት የሻይ ማንኪያ መብለጥ የለበትም፣ ስኳር የበዛባቸው ምግቦችን መቀነስም ከፍ ያለ ጠቀሜታ እንዳለውም ያስረዳሉ።

በመሆኑም ጤናማ ያልሆነ አመጋገብን ከምግብ ስርዓታችን አስወግደን ጤናችንን መጠበቅ እንደሚገባን የሚናገሩት ዶክተር ዘላለም ይህንን ማድረግ ማሰብ እንጂ ብዙ ወጪንም የሚጠይቅ አለመሆኑን በመግለጽ ሁሉም ማህበረሰብ በተቻለ መጠን ዘመናዊነት ያመጣውን ያልተስተካከለ አመጋገብ ሊያስወግድ እንደሚገባ መክረዋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ከአሜን ማግሥት!

**«ነገርን ከሥሩ»**

ስለ ርዕሳችን መሪ ቃል ጥቂት ማብራሪያ በመስጠት ወደ ንባብ መንገዳችን እንዝለቅ። የምድራችን በርካታ ቋንቋዎች በቤተኛነት ከሚገለገሉባቸው ቃላት መካከል፤ ምናልባትም በቀዳሚነት፤ አንዱ ለዋና ርዕስነት የመረጥነው "አሜን!" የሚለው ቃል ነው። ሥርወ መሠረቱን ከእብራይስጥ ቋንቋ ያደረገው ይህ ቃል የቅርብ ዝምድናው ከሃይማኖቶች ጋር ብቻ የተያያዘ ይምሰል እንጂ አገልግሎቱ ከዚያም ላቅ ይላል።

እርግጥ ነው በአይሁድ፣ በክርስትና በእስልምናም ሆነ በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ቃሉ እንደ ማረጋገጫ ቀመር አገልግሎት ላይ እየዋለ እንደሆነ አይካድም። እንደ መዛግብተ ቃላት ፍቺ ከሆነ "አሜን!" የሚለው ቃል ከሃይማኖት መጻሕፍት ንባባት ጋር ሲጎዳኝ እውነት ነው ማለት ይሆናል። በጸሎት መሃል "አሜን!" የሚባል ከሆነ ደግሞ "ይሁንልኝ፣ ይደረግልን" እንደ ማለት ነው።

በታሪክ ነገራና ትርክት ጣልቃ የሚገባ ከሆነም "እውነት ነው፣ ያስማማናል" የሚል መልዕክት ያስተላልፋል። በትዕዛዝ መካከል ቃሉ የሚጠራ ከሆነ ደግሞ "እሺ እታዘዛለሁ" የሚል ትርጉም ይኖረዋል። በአጭሩ "አሜን!" የእምነት ወይንም የአቋም ማረጋገጫና የስምምነት መግለጫ ጽንሰ ሃሳብ የተሸከመ ክቡድ (ጽኑ) ቃል ነው ማለት ይቻላል።

**«የእርቀ ሰላሙ አሜንታና ቀጣዩ ዝግጅት»**

ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ ከፍ ባለ መድረክ ገዝፋና አሸንፋ የወጣችበት ታሪካዊ ቀን ነበር። ይህንን አሸናፊነቷን ሲገልጹ የዋሉት ደግሞ የዓለም መንግሥታት፣ ሕዝቦችና ታላላቅ ሚዲያዎች ጭምር ነበሩ። እስካሁንም በዜናቸው፣ በሀተታቸውና በትንታኔያቸው መሪ ርዕሰ ጉዳይ አድርገው እየዘከሩ ያለው "እንደ ጠቅላይ ሚኒስትራችን አገላለጽ መቶ በመቶ" በሚባል ደረጃ በደቡብ አፍሪካ (ፕሪቶሪያ) የፌዴራል መንግሥትና የሕወሓት የሰላም ንግግር ስኬትን በዋነኛነት በማጉላት ነው።

እርግጥ ነው አጀንዳው የመላው የዓለም መንግሥታትና የምድራችንን አየር የተቆጣጠሩት ሚዲያዎች ዋነኛ ትኩረት ይምሰል እንጂ እንደ እኛ እንደ ባለጉዳዮቹ ጦርነቱ ያስከፈለው የደም፣ የላብ፣ የሃብትና የሥነ ልቦና ቀውስ ጥዝጣዜው በእኩል ደረጃ እየተሰማቸው ነበር ለማለት ያዳግታል። በዲፕሎማሲ ጦርነቱ፣ በአስፈላጊ መሠረታዊ ወታደራዊ ጉዳዮቻችንና በዕለት ርዳታ አቅርቦት ረገድ አንዳንድ ወዳጅ አገራትና የተራድኦ ድርጅቶች ከጎናችን ተሰልፈው ያበረከቱልንን አስተዋጽኦ ግን የምንዘነጋው ስላልሆነ "አሜን!" በማለት ማመስገንን አንዘነጋም።

የሰላም ንግግሩ "በሰላም መጠናቀቅ" ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ትርጉሙ እጅግ የላቀ ነው። በየቤተ እምነታቸው ዐውደ ምህረት ላይ ለጸሎትና ለዱኣ ሲደፉ፣ ሲንበረከኩና ሲሰግዱ ለነበሩት ዜጎች (በተለይም እናቶችና አባቶች) የስምምነቱ ውጤት በፈጣሪ ርዳታ ጭምር እንደተገኘ ስለሚያምኑ እንደ እምነት ቀኖናቸው አመኔታቸው ከፍ ያለ፤ ዕልልታቸውም እጅግ የደመቀ ነው።

ከዚህኛውም ሆነ ከዚያኛው ወገን የደምና የላብ ግብር ለመክፈል በፍልሚያው ጎራ ልጁ የተሰለፈው እናት ወይንም አባት ወይንም ቤተዘመድ የሁለት ወገን ንግግሩ "በሰላም ተቋጨ" ሲባል ደስታቸው እንዴት ስሜታቸውን ፈንቅሎ "አሜን!" እንደሚያሰኛቸው መገመቱ ለማንም የሚከብድ አይደለም።

በወረራውና በጦርነቱ ፍልሚያ መሃል በዱር በገደል ወድቀው ለቀሩት የክፉ ቀን ታዳጊ የመከላከያና የሕዝባዊ ሠራዊት ጀግኖቻችን ለከፈሉልን የሕይወት ዋጋ ክብር ለአጽማቸው! ክብር ለነፍሳቸው! ይሁን በማለት "አሜን!" እንላለን። ንብረታቸው ወድሞ፣ ሀብታቸው ተዘርፎ፣ አካላቸው ጎድሎ፣ ተደፍረው፣ በሥነ ልቦና ቁስል ተመትተውና በመፈናቀል ተንከራታች ሆነው ቀኑ ለጨለመባቸውና እምባቸውን ቀለብ አድርገው መከራቸውን ለተቋቋሙ ዜጎቻችን ክብርና ሞገስ እንዲሆንላቸው ደግመን ደጋግመን አሜንታችንን በአክብሮት እንገልጻለን።

በአገር ላይ የተፈጸመው ግፍ፣ ዕልቂት፣ ወድመትና ጥፋት ታሪካችን በጥቁር መዝገቡ በዝርዝር አስፍሮ ለትውልድ እያቀበለ ስለሚኖር ደግመን ደጋግመን ቁስል እየቀሰቀስንና እየቆሰቆስን መልሰን መላልሰን ከመዘከር እንታቀባለን። የሰላም ንግግሩ ስምምነትም አይፈቅድልንም። ቁርሾና ቂም እየመዘዝንም በደል መተረኩም አይበጀንም። ይልቁንስ ንግግሩ በአሜንታ መቋጨቱ አንድ ነገር ሆኖ እንደ አገር መከናወንና መተግበር ስላለባቸው ጉዳዮች መመካከሩና መወያየቱ ይበልጥ የተሻለ እንደሚሆን እናምናለን።

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ "መጽሐፈ ነህሚያ" በሚል ርዕስ የሚታወቅ አንድ ድንቅ የታሪክ መጽሐፍ ይገኛል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚተረከው ታሪክ በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት (ከ464 - 425 ዓ.ም) በአይሁዳዊያን ላይ የተፈጸመ ምርኮና ስደት ምን ይመስል እንደነበር በዝርዝር ይተርካል። በተለይም አይሁዳውያን በትልቅ ክብር የሚኮሩባት፣ የሚመኩባትና "ቅድስት" ብለው የሚያሞካሹዋት የእየሩሳሌም ከተማ እንዴት በጠላቶች እንደተማረከችና ቅጥሮቿም ፈራርሰው እንደወደሙ በዝርዝር ይተረካል።

ከምርኮኞቹ መካከል በማራኪያቸው ቤተመንግሥት ውስጥ ያገለግል የነበረው ነህምያ የሚባለው ቀናኢ ሰው በንጉሡ ፈቃድ ወደ እየሩሳሌም ተመልሶ የፈራረሰችውን ከተማቸውን ዳግም ለመሥራት ከምርኮ ከተረፉት ቅሬታዎች ጋር ሲመካከር የተናገረው ድንቅ ንግግር በብዙ የአመራር ጥበብ ተመራማሪዎችና አስተማሪዎች ዘንድ ደጋግሞ ይጠቀሳል።

ለእኛ ዐውድ ሊቀራረብ ይችላል ብለን በማሰብ እንደሚከተለው ከንግግሩ አንድ አንቀጽ እንጠቅሳለን። "ያለንበትን ችግር ይኸው ታያላችሁ፤ እየሩሳሌም ፈርሳለች፤ በሮቿም በእሳት ጋይተዋል። አሁንም ኑና የእየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና ተረባርበን እንስራ፤ ከእንግዲህስ መሳለቂያ አንሆንም አልኳቸው" (ምዕራፍ 2 ቁጥር 17)።

እርግጥ ነው ነህምያ ቅጥሩን ሲሰራ ሁሉም "አሜን!" ብሎ ተባብሮት ነበር ማለት አይቻልም። እንዲያውም ተግዳሮቱን የገለጸው እንዲህ በማለት ነበር፡- "ቅጥሩን እንደምንሰራ ጠላቶቻችን በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ፤ እጅግም ተበሳጩ። ተሳለቁብንም።... እነዚህ ደካሞች ምን እያደረጉ ነው? ቅጥራቸውን መልሰው ሊሰሩ ነውን? እንዲዚያ ተቃጥሎ የፍርስራሽ ክምር የሆነውን ድንጋይ ነፍስ ሊዘሩበት ይችላሉን? እያሉ አላገጡብን።" በማለት የክፉዎችን ድርጊት በሚገባ ተርኮታል።

> «ያለንበትን ችግር ይኸው ታያላችሁ፤ እየሩሳሌም ፈርሳለች፤ በሮቿም በእሳት ጋይተዋል። አሁንም ኑና የእየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና ተረባርበን እንስራ፤ ከእንግዲህስ መሳለቂያ አንሆንም አልኳቸው»

እኛም ዘንድ ቢሆን አንደኛውን ለይቶላቸው የሰላም ስምምነቱን በተመለከተ የሚያካኪሱ፣ የሚያራክሱ፣ የሚያላግጡ፣ የሚቃወሙና የክፋት መርዛቸውን ባገኙት መድረክ ሁሉ ለማቀርሸት የሚቅበዘበዙ ፀረ ሰላሞች በዚህኛውም ሆነ በዚያኛው ወገን ይጠፋሉ ለማለት አይቻልም። ስምምነቱ በገቢር ስለመተርጎሙም በቅንነት የሚጨነቁ አንዳንድ ዜጎች እንደሚኖሩም ይገመታል። እነዚህም ተባለ እንደዚያ ኢትዮጵያ ከአሸናፊነት ክብሯ ዝቅ ብላ ዳግም ለጥፋት መልእክተኞች ጆሮ እንደማትሰጥ በአሜንታዋ አረጋግጣለች። "አውድማ የቆረጠችውን ቆርጣለች፤ ፌጦ በከንቱ ትረጫለች" እንዲል ብሂሉ ዳግም ወደ ጥፋቱ የሚመለሰው "ቡቾ" የምንለው የቤት እንስሳ ብቻ ነው።

በተለኮሰብን የጦርነት ሰደድ እሳት ምክንያት የፈራረሱብን "ቅጥሮች" እጅግ ብዙዎች ናቸው። የአገራዊ ኢኮኖሚያችን "ቅጥር" መናጋቱ እውነት ነው። ሰብዓዊ ጉዳቶቻችንም ገና በአግባቡ ተለይተው አልተጠናቀቁም። የበርካታ ማሕበራዊ እሴቶቻችንና ተራክቧችን "ቅጥሮችም" ክፉኛ ፈራርሰዋል። በጥቅሉ ለመግለጽ ካስፈለገ ምክንያት አልባው ጦርነት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የከፋ ችግርና መከራ ላይ መጣሉን በብዙ ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል።

ምናልባትም የገጠመን ፈተና በእስከዛሬው ታሪካችን ተፈጽሞ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ስለዚህም እንደ አገር ለእኛ የከፋ ጉዳት፣ ለዓለም ማሕበረሰብ ደግሞ መሳለቂያና መዘባበቻ ያደረጉንን ፍርስራሾቻችንን እንደገና በተሻለ ሁኔታ አሳምረን ለመገንባት ምን ማድረግ ይገባናል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በትጋት መሰለፉ ይበልጥ ስለሚመረጥ በመልሶ ግንባታ ረገድ ማድረግ ስለሚገቡን ጉዳዮች አንዳንድ ሃሰቦችን ፈነጣጥቀን እናጠቃልላለን።

በጦርነቱ ምክንያት የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉልን ጀግኖቻችን ወላጆችና ቤተሰቦች መጽናናትና መደገፍ ይገባቸዋል። አይዟችሁ መባልንም ይሻሉ። ስለሆነም እንዴት ነው በሀዘን ግርዶሽ የተሸፈኑትን ወገኖቻችንን ሕይወት የምናለመልመው? እንዴትስ ነው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ከሰላም ስምምነቱ "አሜንታ" ማግሥት የምንታደጋቸው? ይህን መሰሉ ከፍ ያለ የቤት ሥራ ከፊታችን ገዝፎ እየጠበቅን ስለሆነ በአግባቡ ልንመክርበት ይገባ ይመስለናል።

ንብረቱና ሀብቱ፣ በአንድ ጀንበር ወድሞበት ኑሮውንም፣ ትዳሩንም ሆነ ልጆቹን እንዳጣው እንደ ቅዱሱ መጽሐፉ ጻድቁ ኢዮብ እጃቸውን አጨብጭበው በሁለንተናቸው ባዷቸውን የቀሩትና ድጋፍ የሚፈልጉ ወገኖቻችን ሺህ ምንተ ሺህ ናቸው። የሥነ ልቦና ቀውስ ደርሶባቸው በራቸውን ዘግተው እያነቡ ያሉ ዜጎቻችንም ከግምታችን እጅግ የበዙ ናቸው። የተፈናቀሉትን፣ የተሰደዱትን፣ የተንከራተቱትን እያልን ብንዘረዝር ቆጥረን የምንዘልቀው አይደለም። በአጭሩ የፍርስራሹ ስፋትና ግዝፈት ይህ ልክህ ብለን ልንወስነው የምንችል አይመስለንም።

ተገደውም ሆነ ወደው በዚያኛው ወገን ፕሮፓጋንዳ በመሸነፍ አምላካዊ ጥሪያቸውን በመዘንጋት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ያወገዙ የሃይማኖት ተቋማትና መሪዎች ያፈራረሱት የጋራ "ቅጥር" መጠገን የግድ ይላል። ተቀዳሚ ባለጉዳዮቹ የኢትዮጵያ ቤተ እምነት መሪዎች እንደ ነህምያ ጨክነውና ቆርጠው "ከመሳለቂያነት" ሊታደጉንም ይገባል።

የኪነ ጥበቡም ቅጥር የተነቃነቀና ስንጥቅ የሚታይበት ይመስላል። በዚህም ዘርፍ የአገሪቱ የጥበብ ቤተሰቦች ብዙ ሥራ ይጠበቅባቸዋል። የአገሪቱ ምሁራን፣ በሀብት የተባረኩ ዜጎች፣ የፖለቲካ ልሂቃንና የማሕበረሰብ አንቂዎች፣ የአካባቢና የፌዴራል መንግሥታት አመራሮች፣ የአገሪቱ ሚዲያዎች፣ ወጣቶችና አረጋውያን ከገጠመን መከራና "ጉስቁልና" ፍርስራሾቻችንን አሳምረንና አስውበን እንድንገነባ እጃችንን በአንድነት ልናበረታታና የድርሻችንን ልንወጣ ታሪካዊው ግዴታና ሰብዓዊው ውዴታ ግድ ይለናል።

በሰላም ንግግሩ መቋጨት ማግሥት የሚጠበቅብን አገራዊ ኃላፊነት በጥቂቱ ይህንን ይመስላል። ቢቻል ለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት በሙሉ አሜንታ የዜግነት ድርሻችንን በአቅማችን ልክ ለመወጣት እንጨክን። የማይሆንልን ከሆነ የጥሞና ጊዜ ወስደን ጉዳዩን በሰከነ ስሜት ለመከታተል ኮስተር ብለን እንወስን። በትንሽ በትልቁ እየተቃወምን "ንፉስ እንድንጎስም" ስሜታችን የሚጎተጉተን ከሆነ ደግሞ ለራሳችንና በራሳችን ጊዜ በራችንን ዘግተን እንቆዝም እንጂ የሚሊዮኖችን የተስፋ ብርሃን ለማጨለም የበጋ መብረቅ አንሁን። መንፈሳችንንና ሰብዓዊነታችን በሁከት ሱሰኛነታችን ምክንያት ተጠይፈውንና ንቀውን ጥለው እንዳይረግጡን ለራሳችን ክብር እንስጥ። አሜን! ሰላም ይሁን።

# ተናጋሪው ዶሴ

## የግለሰቡ እና የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ክርክር እስከ ሰበር

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ሰውየው ከቦረና እስከ ሰበር ድረስ ዘልቀው የማይደፈረውን ደፍረው፤ ጥርሳቸውንም ነክሰው መብታቸውን ለማስከበር ጥረታቸውን ጀምረዋል፡፡ ወዲህ ደግሞ የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ቀጥታ ፍርድ ቤት ለመቅረብ አይገደድም፡፡ በዛሬው ዕትማችን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች በሚል የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በ2008 ዓ.ም ከውሳኔዎች መካከል ለህትመት ካበቃቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ይሆናል። የሰነድ መለያ ቁጥር 98541 ያለው የክርክር ጉዳይ ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም የመጨረሻውን ውሳኔ ያገኛል። ታዲያ አምስት ዳኞች ከፍርድ መንበሩ ተሰይመው የመጨረሻ የተባለውን ውሳኔ ሊበይኑ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ አመልካች አቶ አለማየሁ ኦላና በአካል ተገኝተው እንዲሁም ተጠሪው የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት (UNDP) በጥሪ ታልፎ በአካል በሌሉበት የፍርዱን መጨረሻ ቃል ይጠባበቃሉ፡፡ የፍርድ ሚዛን ወደየት ይሆን?

### የሳቤን ዋጋ...

የሰበር ጉዳይ የቀረበው አመልካች በተጠሪ ላይ የአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎችን መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክስ ተጠሪ በሌለበት ታይቶ በክርክሩ ከተረጋገጠበት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሳት አመልካች የተለያዩ ክፍያዎች በተጠሪ እንዲከፍሏቸው በወረዳው ፍርድ ቤት በተወሰነው መሰረት የአፈጻጸም መዝገብ ከፍተው ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ ተጠሪ የመከሰስ መብት የለውም ተብሎ የአፈጻጸም መዝገቡ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች መዘጋቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

አመልካች ተጠሪ ከህግ ውጭ ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ አቤት አሉ፡፡ በያበሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የአሁኑ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመደምደም ለአመልካች ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ውሳኔውን ለማስፈፀም በወረዳው ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ ከፍተው ጉዳዩ መታየት ከጀመረ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የተባበሩት መንግስታት ኮንቬንሽንን አንቀፅ 2(3) በዋቢነት ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቶታል።

### ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት

በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበውም ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ መስጠቱ የታለፈ ሲሆን ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሆኖ አመልካች የሚከራከሩት የተባበሩት መንግስታት አካል ከሆነው ድርጅት ጋር መሆኑን፣ ከእንደዚህ አይነት ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የማይገዛ መሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 3(ሀ) ስር መመልከቱን፣ ተጠሪና መሠል አካላት በሕግ የተለየ ከለላ ያላቸው መሆኑ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀጽ 105፣ በተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ ለመደንገግ በወጣው ስምምነት አንቀጽ 2(2) እና 3 ስር መደንገጉን፣ ኢትዮጵያም ይህንኑ ስምምነት መፈረሟን በዋቢነት ጠቀሰ፡፡ ከመነሻውም ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት መከሰሱ ተገቢነት እንደሌለው፣ አመልካች ያላቸው መፍትሔም በ"United Nations Commission on International Trade Law (UNCITRAL)" ደንቦች መሰረት ከተጠሪ ጋር ባላቸው ስምምነት መሰረት በእርቅ መጨረስ መሆኑን፣ በዋናው ጉዳይ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑን ከተጠሪ ጥቅምና ከባለ መብቶች አንፃር ሲታይ ዋናውን ውሳኔ ሕጋዊ የማያደርገው መሆኑን ዝርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለንም በማለት የአፈጻጸም መዝገብ መዝጋታቸውን በመቀበል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡



### ወደ ሰበር

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነበር፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በዋናው ጉዳይ ላይ ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት ሁኔታ በአፈጻጸም መዝገብ የተጠሪን ያለመከሰስ ከለላ በመጥቀስ ዋናውን ውሳኔ ውድቅ ማድረግ ሥነ ሥርዓታዊና የሕግ የበላይነት እንዲሁም አመልካች እንደ ዜጋ ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን ያላገናዘበ ነው በማለት ተከራከሩ፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በጽሑፍ መልስ መስጠቱ ታለፈ፡፡

### ዲፕሎማቲክና ሚሲዮኖችን ያጣቀሰው ምርመራ

ሰበር ችሎት ጉዳዩን ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ምርመራ ጀመረ፡፡ ፍሬ ነገሩ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ግንኙነት የቅጥር ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ዋናው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ታይቶ ዳኝነት ማግኘቱን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የተለያዩ ዓይነት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች የሚኖሩ ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚገዙበት የሕግ አግባብም ይለያያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ግንኙነቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ይህ አዋጅ በየትኞቹ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚችል በዋነኝነት የሚመራው የአዋጁን የተፈጻሚነት ወሰን የደነገገው አንቀጽ 3 ነው፡፡ ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የአንቀጹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሶስት በፊደል "ሀ" ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ንዑስ ድንጋጌ ስር የስራ ግንኙነቱ በንዑስ አንቀጽ ሁለት ስር የሚወድቁ ባለመሆናቸው በአዋጁ አንቀጽ 1 መሰረት በቀጥታ ሊፈጸምባቸው የሚችል ቢሆንም በንኡስ አንቀጽ 3 ስር በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት ከአዋጁ ሽፋን ውጭ ሊደረጉ የሚችሉ የስራ ግንኙነቶችን የሚመለከት ነው የሚል ሃሳብም በምርመራው ተካተተ፡፡

በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሰርቱት የሥራ ግንኙነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ወይም ኢትዮጵያ በምትፈርማቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በአዋጁ ሊሸፈኑ እንደማይችሉ ተመልክቷል፡፡

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሁንታ...

በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ሲታዩ አዋጁ በአጠቃላይ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚቋቋም በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም በአዋጁ 260 በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ህግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም አሁንም አዋጁ የሚሸፍናቸው የሥራ ግንኙነቶች ሊሆኑ ቢችሉም ነገር ግን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ኢትዮጵያ የምትፈርማቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሚወስኑት መሰረት ከአዋጁ ሽፋን ውጭ ሊደረጉ የሚችሉ መሆኑን ተመለከተ፡፡

በመሆኑም ሕግ አውጪው የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ስምምነትና ልምድን ለማክበር ሲባል የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚስዮኖቹና ኢትዮጵያውን ሠራተኞቻቸው የሚያደርጉት የቅጥር ግንኙነት ላይ የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ወይም ኢትዮጵያ ከውጭ ድርጅቶች ጋር በምትፈራረምባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚደረግበት አግባብ መኖሩን ሕግ አውጪ በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3((ሀ)) መሰረታዊ ዓላማ የውጭ አገር መንግሥታት ተወካዮችን ሉአላዊነት እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማክበር ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን በተጨባጭ ባለው ሁኔታ ደግሞ የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ጋር ስምምነት ተፈራርመው ይኼው የመንግስት አካል በእነዚህ ተቋሞች ተቀጥረው የሚሰሩት ኢትዮጵያውንን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተካተተው አግባብ የተፈጠረው አለመግባባት ሰላማዊ በሆነ መንገድ በማግባባትና በድርድር እንዲፈታ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው፡፡

### የመንግስት ፍርድ ቤት የማይቀርበው ድርጅት

የአመልካች ክርክር ያቀረቡት ግንኙነቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3(ሀ)) መሰረት ሊገዛ ከማይችል አካል ጋር ነው፡፡ ተጠሪ የተባበሩት መንግስታት አካል ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገ ስምምነትም በማንኛውም መንግስት ፍርድ ቤቶች ተከሶ መቅረብ የሌለበት መሆኑን በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ 105 እንዲሁም ከተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገው ስምምነት አንቀጽ 2(2) እና 3 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር የሌለ ቢሆንም አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት በዋናው ጉዳይ ውሳኔ ከአረፈ በውሳኔው መሰረት ከሚፈጸም በስተቀር የተጠሪ በሕግ ያለው የተለየ ከለላ እንደ አቢይ ምክንያት ተወስዶ አፈፃፀሙ ሊቆም የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ነው፡፡

በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ ዋጋ እንዳይኖረው የሚደረገው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢነት እንደሌለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 378 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነ ዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠን ውሳኔ በሕጉ አግባብ ማስፈፀም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78(1) እና 79(1) እና (4) ስር የተረጋገጠውንና የተከበረውን የነጻ ፍርድ ቤት መኖርንና የዳኝነት ስልጣን በአግባቡ ተግባራዊ የሚያደርገው እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ስር የተረጋገጠው የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብትም ውጤት ባለው መልኩ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ መሆኑ ታመነበት፡፡

### አፈፃፃም

በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ትርጉም እንዲኖረው የማድረግ ውጤት ያለውና በተገቢው መንገ ድም መፈፀም ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ግን ለማን ኛውም ጉዳዮች ሁሉ ይሰራል ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ተገቢ ያልሆነ ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ እሙን ነው ይላል የዶሴው ዝርዝር። በእርግጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌ ስር በስነ ስርዓት ጉድለት አንድ ፍርድ ውድቅ ሊሆን እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ይህ ግን የሚሰራው የፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ሕጉ ተፈፃሚነት ወሰንን መሰረት በማድረግ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በሕግ ባልተደነገገበት ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ከመነሻውም ኢትዮጵያ በፈረመችው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ላለመዳኘት ነገር ግን ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር ለመሰረተው ግንኙነት በሌላ አግባብ ጉዳዩን ለመጨረስ የሚያስችል ስርዓት ያለው ወገን በዋናው ክርክር ጊዜ ቀርቦ ባለመከራከሩና በይግባኝ ጉዳዩን ባለማሳረሙ ምክንያት ብቻ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም የሚገደድበት አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጉዳይ የተለየ ባሕርይ ስንነሳ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 እና 4 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተጣምረው ሲታዩ አፈፃፀሙ ዋጋ ያለውን ፍርድ መሰረት ያደረገ ነው፣ ጉዳዩ ከስነ ስርዓት ጉድለት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡

ተጠሪ በሕግ የተጠበቀለት የከለላ መብትና ጥቅም እያለው ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም ማድረግ ሕግ አውጪው የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ልምድን ለማክበር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3(ሀ)) ስር ያስቀመጠውን ድንጋጌ ዋጋ የሚያሳጣው እና በዲፕሎማቲክ ግንኙነቱም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተመራጭ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ሲጠቃለልም የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ሲታይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌን ጠቅሶ አፈፃፀሙን ማስቀጠል የሚቻልበት አግባብ ስለሌለና አመልካችም እንደዜጋ መንግስት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በኩል በዘረጋው ስርዓት መሰረት መብትና ጥቅማቸውን የሚያስከበሩበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ የሕግ የበላይነት አልተከበረም፣ ዜጋ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት ተጥሷል ለማለት ስላልተቻለ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስኗል፡፡

### ውሳኔ

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመለያ ቁጥር 163639 ታህሳስ 07 ቀን 2006 ዓ.ም የበታች ፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝ በማፅናት የተሰጠው ውሳኔ በፍትሃ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት የፀና ሲሆን፤ የአመልካች የአፈጻጸም ክስ መዘጋቱ ተገቢ ነው ሲል በይኗል፡፡ አመልካች አለኝ የሚሉትን መብትና ጥቅም በሌላ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ሲልም ሰበር ዶሴውን ዘግቶታል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## «ሕይወት መቅጠፊያ ፍቃድ» በ3ሺ ብር!

ቦጋለ አበበ

በትራፊክ አደጋ በዓለም ላይ በየዓመቱ ከ1.3 ሚሊየን በላይ ሰዎች ሕይወታቸውን እንደሚያጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በኢትዮጵያም በቀን 13 ሰዎች በዓመት ደግሞ 4680 ያህል ዜጎች ሕይወታቸውን በዚሁ አደጋ ምክንያት እንደሚያጡ የቅርብ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

በኢትዮጵያ ይህን አስከፊ አደጋ ለመቀነስ የመንገድ ትራፊክ የተለያዩ የአሰራር ስርአቶችን ዘርግቶ ወደ ስራ ሲገባ ቢስተዋልም፣ አደጋውን ቀንሶታል ብሎ ደፍሮ ለመናገር አይቻልም።ካለፈው ሰኔ ወር በፊት በነበሩ ስድስት ወራት የትራፊክ አደጋ በኢትዮጵያ ከ5 እስከ 7 በመቶ ያህል መጨመሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ከህግ አስከባሪውና አሽከርካሪው በተጨማሪ እግረኞች ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው የዘርፍ ባለሙያዎች በተለያየ አጋጣሚ ሲገልፁ ይሰማል።ያም ሆኖ በኢትዮጵያ ለትራፊክ አደጋ መንስኤ ከ85 በመቶ በላይ ምክንያት የሆኑት አሽከርካሪዎች ናቸው። አሽከርካሪዎች ሲባል ደግሞ በብቃትና በጥሩ ስነምግባር ህግ አክብረው የሚያሽከረክሩትን አይደለም። የአንበሳውን ድርሻ የሚይዙት ብቃቱ ሳይኖራቸው ህጋዊም ይሁን ፎርጅድ መንጃ ፍቃድ ይዘው የሚያሽከረክሩትን ነው። ፎርጅዱ መንጃ ፍቃድ በአንድ ስሙ ህገ ወጥ ነው። ትዝብቴን እንዳካፍል ያነሳሳኝ ትክክለኛውን መንጃ ፍቃድ ብቃቱ ሳይኖራቸው በህጋዊ መንገድ አውጥተው የሚያሽከረክሩትን የተመለከተው ጉዳይ ነው።

የአሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ጉዳይ ብዙ ጊዜ አከራካሪ ነው። የአሽከርካሪዎችን ብቃት መዝነው መንጃ ፍቃድ የሚሰጡት ሰዎች ለዚህ ችግር ዋነኞቹ ተጠያቂዎች ናቸው። ይህን በድፍረት እንድናገር ያደረገኝን ትዝብት ላካፍል።

ከሳምንታት በፊት እንደሰው መንጃ ፍቃድ ለማውጣት የንድፈ ሃሳብ ትምህርቱንና የተግባር ልምምዱን ጨርሼ ቃሊቲ ለተግባር ፈተና በተቀጠርኩበት ማለዳ ተገኘሁ። እንደኔው ለተግባር ፈተና ማልደው በስፍራው የተገኙ(በብዛት ወጣቶች ናቸው)፣ ፈታኞችና አስተማሪዎች መካከል ያለው ወከባ አይጣል ነው። የመጀመሪያዎቹ ተፈታኞች ጨርሰው ለተከታዩ ተፈታኝ እስኪያስረክቡ ዘለግ ያለ ወረፋ መጠበቅ ግድ ነው። ተራው እስኪደርሳቸው ድረስ ወረፋ እንዲጠብቁ በተዘጋጀው ቦታ ላይ በርከት ብለው የተቀመጡ ሰዎችን ተቀላቀልኩ። ሁሉም ተፈታኝ ማለት ይቻላል ከጎኑ ከተቀመጠው ጋር የሚያወጋው በተመሳሳይ የመንጃ ፍቃድ ፈተና ጉዳይ ላይ ነው።

አጠገቤ የተቀመጡ ሁለት ወጣቶች የሚያወጉትን ጉዳይ ግን ጆሮ ልነፍገው አልቻልኩም። ወጣቶቹ የሚያወጉት ጉዳይ ሲጠቃለል «ማንኛውም ተፈታኝ የቱንም ያህል ብቃት ቢኖረው ለፈታኞች በስውር ገንዘብ እስካልሰጠ ድረስ በትንሽ ስህተት ፈተናውን ይወድቃል» የሚል ነው። በአንጻሩ አንድ ተፈታኝ ለማሽከርከር የሚያበቃ ብቃት ባይኖረውም የተጠየቀውን ገንዘብ እስከከፈለ ድረስ መንጃ ፈቃዱን የማግኘት ጉዳይ አያሳስበውም።

ይህን ጉዳይ ቃሊቲ በቆየሁበት ግማሽ ቀን እንደ ጋዜጠኛ ሳይሆን እንደ ተፈታኝ ከተለያዩ ሰዎች ለማጣራት ባደረኩት ጥረትም እውነት መሆኑን ከተጨማሪ መረጃዎች ጋር ለማረጋገጥ ከባድ አልነበረም። አንድ ተፈታኝ መንጃ ፍቃዱን ለማግኘት በቅድሚያ ከተግባር አስተማሪው ጋር ይደራደራል። ጥሩ ተደራዳሪ ከሆነ ከሶስት ሺ እስከ ሶስት ሺ አምስት መቶ ብር ከፍሎ ለማሽከርከር ብቁ ባይሆንም መንጃ ፍቃዱን በእጁ ያስገባል። ከዚህ በላይ እንደየሁኔታው ከፍ ያለ ገንዘብ የሚከፍልም አለ። የተግባር አስተማሪውም ገንዘቡን ይዞ ለራሱ የሚገባውን ካስቀረ በኋላ ለፈታኞች ቀደም ብሎ የሚፈተነውን ሰው በማሳወቅ ያስረክባል። በቁጥር በርከት ያሉት ፈታኞችም ገንዘቡን ተከፋፍለው ተፈታኙን ያሳልፉታል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለማሽከርከር ብቁ ያልሆኑት ብቻ ሳይሆኑ ብቃቱ እያላቸው በተገቢው መንገድ ተፈትነው ማለፍ የሚችሉም ገና ለገና በጥቃቅን ነገር እወድቃለሁ በሚል ስጋት ክፍያውን ይፈጽማሉ። ሌሎች ደግሞ ፈተናውን ድንገት ወድቄ ለሌላ ፈተና ከማባክነው ጊዜ ይልቅ ገንዘቤን ይጭነቀው ብለው ይከፍላሉ።

በእርግጥ እዚህ ጋር ጥቂት ቢሆኑም የተጠየቁትን ገንዘብ አንከፍልም ብለው በተገቢው መንገድ ተፈትነው የሚገጥማቸውን ነገር የሚጋፈጡም አሉ። ፈታኞችም እንዲህ አይነቶቹን ሰዎች መጋፈጥ አይችሉም። ምክንያቱም የፈተናው ሂደት ሙሉ በሙሉ በካሜራ እይታ ውስጥ በመሆኑ ፈተናውን በብቃት ተወጥተው ቢወድቁ ማስመርመር የሚችሉበት እድል አለ። ነገር ግን ፈተና በራሱ ተፈታኝ ላይ የመደናገጥ ስሜት የመፍጠር ባህሪ ስላለው ብቃቱ ያላቸው ሰዎችም ስሜታዊ (ነርቨስ) መሆናቸው አይቀርም። ፈታኞችም ይህን ስለሚያውቁ ይመስለኛል በተፈታኞች ላይ የሚፈጥሩት ወከባና ማጣደፍ ሆን ብለው የሚፈጽሙት ነው። በዚህም ተረጋግቶ ማድረግ ያለበትን ነገር ሳያደርግ ቀርቶ የሚወድቅ ተፈታኝ ጥቂት አይደለም።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተደጋግሞ እንደሚነገረው ለአገራችን የትራፊክ አደጋ መባባስ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የመንጃ ፍቃድ አሰጣጥ ጉዳይ ነው። ፈታኞች ለትንሽ የገንዘብ ጥቅም ብለው ምንም የማሽከርከር ብቃት ለሌላቸው ሰዎች በሚያድሉት መንጃ ፍቃድ የስንቱ ሕይወት ተቀጥፎ ይሆናል፣ የስንቱስ ንብረት ወድሞ ይሆናል?። ኪስ በማይሞላ ገንዘብ የበርካቶች ሕይወት ተመሰቃቅሏል፣ በርካቶች ቤተሰብ አልባ ሆነዋል። የዚህ መዘዝ በግለሰብና በቤተሰብ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም። ማህበራዊ ጉዳቱ ይበልጥ የጎላ ነው። ብቃት ሳይኖራቸው ህጋዊ መንጃ ፍቃድ ይዘው እያሽከረከሩ አደጋ በሚያደርሱ ሰዎች ምክንያት አገርን መለወጥ የሚችሉ በርካቶች በአጭሩ ሊቀጩ ይችላሉ፣ ተቀጭተዋልም።

መንግስት ለዚህ አንገብጋቢ ችግር መፍትሄ ለማበጀት በየጊዜው ጥረት ቢያደርግም ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶታል ለማለት አያስደፍርም። የዚህን ችግር አሳሳቢነት ይበልጥ አጉልቶ በማውጣት ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ብቃት ሳይኖራቸው ህጋዊ መንጃ ፍቃድ ይዘው የሚያሽከረክሩ ሰዎች በሚያደርሷቸው አደጋዎች ዙሪያ ጥናቶች በስፋት መሰራት አለባቸው። መንጃ ፍቃድ ሰጠን ብለው "ሕይወት መቅጠፊያ ፍቃድን" በሶስት ሺ ብር የሚሰጡ ሰዎችም ህሊና ካላቸው በጥናቶቹ ውጤቶች ትንሽ ደንገጥ ብለው የሚሰሩትን ቆም ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸው ይሆናል።

# ዓለም አቀፍ



## ከሐምሌ ወር ወዲህ በሱዳን ግጭት 359 ሰዎች መገደላቸውን ተመድ አስታወቀ

ከሐምሌ ወር እስካሁን ባሉ ጊዜያት በሱዳን በጎሳ ግጭት ምክንያት ብቻ 359 ሰዎች መገደላቸውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መግለጹን አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል፡፡

ሰዎቹ ሕይወታቸውን ያጡት ግጭቱ የሚባዛባቸው ገጠራማ የአገሪቱ ክፍሎች መሆኑንም ተነግሯል፡፡

በተለይ በብሉ ናይል ግዛት እየተባባሰ የመጣው ብጥብጥ ወደ 97 ሺህ ሲያፈናቅል 469 ሰዎችን ለከፍተኛ ቁስል ዳርጓል።ብዙዎቹ ተፈናቃዮች ወደ አጎራባች ክልሎች መሰደዳቸውን የዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት አስታወቋል። ከሁለት ሳምንት በፊት በምዕራብ አፍሪካ በሚገኙ በሃውሳ ጎሳ እና በበርታ እና በሃማጅ ህዝቦች መካከል የተፈጠረውን የመሬት አለመግባባት ተከትሎ በ48 ሰዓታት በዘለቀው ሁከት ቢያንስ 230 ሰዎች ተገድለዋል።

ሀገሪቱን እያስተዳደሩ ያሉ የጦር ጄኔራሎች እና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና አንጃዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ እውንታ ያለው የሀገሪቱ የዲሞክራሲ ሽግግር እውን ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመራቸው ተከትሎ አመጽ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየጨመረ መጥቷል።ባሳለፍነው ወር ወታደሮቹ በሚቀጥሉት 24 ወራት ውስጥ ሀገሪቱን ወደ ምርጫ የሚመራ እና በሲቪል የሚመራ መንግስት ለመመስረት በሀገሪቱ የሕግ ባለሙያዎች ማህበር የተጻፈውን የሕገ መንግሥታዊ ሰነድ ረቂቅ ሲስማሙም በርካታ የዲሞክራሲ ደጋፊዎች ከወታደራዊ መንግስቱ ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውድቅ ተደርጓል።

እ.ኤ.አ በጥቅምት 2021 በመፈንቅለ መንግስት ወደ ሥልጣን ከመጡት የወታደራዊ መሪ ጄኔራሉ አብደል ፋታህ አልቡርሃን ጊዜ ጀምሮ ሱዳን በሁከት ውስጥ ትገኛለች።ለሶስት አስርት ዓመታት ሱዳንን ያስተዳደሩ ከአምባገነኑ የኦማር አልበሽር መንግስት መውደቅ በኋላ አጭር ዲሞክራሲያዊ ሽግግር መታየቱም ተገልጿል። የቀድሞው ፕሬዝዳንት አልበሽር እ.ኤ.አ በ2019 ከስልጣን ለመወገዳቸው ምክንያት ለሲቪል እና ወታደራዊ የስልጣን ክፍፍል መንገድ የከፈተው ሕዝባዊ አመጽ ነው ተብሏል።

ያም ሆኖ ሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት የሚፈጠረው ሕዝባዊ አመጽና የጎሳ ግጭት የሀገሪቱ መጻዒ እድል አጠያያቂ ማድረጉንም ተገልጿል።

## ትራምፕ ዳግም የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የመሆን እድላቸው ሰፊ መሆኑን ገለጹ



የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ እ.ኤ.አ በ2024 በአሜሪካ በሚካሄደው ምርጫ ዳግም ፕሬዚዳንት የመሆን እድላቸው በጣም ሰፊ መሆኑን ተናገሩ፡፡

ፕሬዝዳንቱ በአዋዮ ግዛት ለሪፓብሊካን ፓርቲ ደጋፊዎች ባደረጉት ንግግር፣ በቀጣዩ የአሜሪካ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ብርቱ ተፎካካሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ፍንጭ ሰጥተዋል።

ትራምፕ በ2024 ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ላይ ሊሳተፉ እንደሚችሉ ፍንጭ ሲሰጡ ይህ የመጀመሪያቸው አይደለም። ከዚህ ቀደም በፔንሲልቬኒያ እና ቴክሳስ ግዛቶች ዳግም ዕጩ ሆነው ሊቀርቡ እንደሚችሉ ተናግረው ነበር።

ትራምፕ ይህን ያሉት በአሜሪካ ፕሬዝዳንት የሥልጣን ዘመን አጋማሽ ላይ በሚደረገው "ሚድተርም" የምርጫ ቅስቀሳ ለሪፓብሊካን ፓርቲ እጩዎች ቅስቀሳ ባደረጉበት ወቅት ነው። ፕሬዝዳንት ጆ ባይደንም በዚህ ምርጫ የተሻለ ድምጽ ለማግኘት ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ቅስቀሳ እያደረጉ ነው፡፡

አሜሪካውያን የፊታችን ማክሰኞ በዚህ የሚድተርም ምርጫ የሚሰጡት ድምጽ በአሜሪካ ኮንግረስ እና ቁልፍ በሆኑ የግዛት አስተዳደሮች ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። የሚድተርም ምርጫዎቹ ከሁለት ዓመታት በኋላ ከሚካሄደው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ በፊት የአሜሪካን ፖለቲካ ቅርጽ ሊያስቀይሩ እንደሚችሉም ተነግሯል።

ትራምፕ ሐሙስ እለት ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ሲያደርጉ ምንም አይነት ማስረጃ ሳያቀርቡ በ2020 ፕሬዝዳታዊ ምርጫ ተጭበርብረው ማሸነፋቸውን ተናግረዋል።

"ሁለቴ ተወዳደርኩ፤ ሁለቱንም አሸንፊያለሁ፤ ከመጀመሪያው ሁለተኛውን በተሻለ መልኩ አጠናቅቂያለሁ፤ በ2016 ካገኘሁበት በላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ድምጾችን በ2020 አግኝቻለሁ" ያሉት ትራምፕ፤ በ2020 በአሜሪካ ታሪክ የትኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ያላገኘውን ድምጽ ማግኘታቸው ገልጸዋል።

አሁንም ቢሆን አሜሪካ የተሳካላትና ደኅንነቷ የተጠበቀ እና የተከበረች አገር ለማድረግ ዳግም ምርጫውን እንደሚወዳደሩ አመልክተዋል፡፡

ትራምፕ ይህን ሲሉ ታዳሚው በጭብጨባ ድጋፉን ገልጾላቸዋል። ትራምፕም "ተዘጋጁ" ሲሉ መልሰዋል።

ትናንት ሐሙስ በኒው ሜክሲኮ እና ካሊፎርኒያ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የቆዩት ጆ ባይደን በ2024 ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ላይ ዳግም ለመሳተፍ ከአማካሪዎቻቸው ጋር ስብሰባ ሲቀመጡ መቆየታቸው ተገልጿል።

ይህም ባይደን እና ትራምፕ ዴሞክራት እና ሪፓብሊካን ፓርቲ ወክለው ዳግም በ2024 ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ሊፋጠጡ ይችላሉ የሚለውን ግምት ከፍ አድርጓል።

## መጋቢ አዕምሮ

# ሰላምን ማብዛት

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ጭቃ እያቦኩ የሚጫወቱ የአንድ ሰፈር ልጆች ናቸው።በተለመደው የጨዋታ ቦታቸው ላይ ሆነው ዝማሬን ይዘምራሉ።እጃቸውን በጭቃ ውስጥ እንዳደረጉ ጭቃውን እያቦኩ መዝሙር ይዘምራሉ፤ የሰላምን ዝማሬ።በመንገድ ላይ ልጆቹን እያየ የሚያልፈው ሰው ሁሉ 'አይ ልጅነት ማማሩ' ይላል።በጭቃ የተበከለው ልብስ ሳያሳቅቃቸው፤ እፍረትም ሳይሰማቸው፤ ድምጻቸው ለሙዚቃ አመቺ መሆን አለመሆኑ ጉዳያቸው ሳይሆን የሚዘምሩ።ከዝማሬው ሲመለሱ ደግሞ መልሰው ጭቃውን ያቦካሉ፤ በጭቃውም የሚፎካከሩበትን ቤት ይሰራሉ፤ የሰሩትንም ቤት መልሰው ያፈርሳሉ፤ ሊጣሉም ሆነ ሊደባደቡም ይችላሉ፤ ልጅነት።

ከልጆቹ እልፍ ባለው ዛፍ ስር የተሰበሰቡ አዋቂዎች ሸንጎ ተቀምጠዋል፤ የተጣሉትን ለማስታረቅ።በሁለት አዋቂዎች መካከል የተፈጠረውን ጥል ለማርገብ የአካባቢው ሽማግሌዎች ለማስታረቅ ጥረት እያደረጉ ናቸው።ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን እውነት አቅርበው አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ጥረት እያደረጉ ከስሜት ጋር የተቀላቀለ የቃላት ውርዋሮ ውስጥ ናቸው።አንደኛው ግለሰብ ወይ ፍንክች 'የእኔን በደል ተመልከታችሁ እልባት የማትሰጡኝ ከሆነ ፍትሕ የለችም ማለት ነው፤ ወይ ፍንክች' ይላል።'እንዲህ ሆኖ፤ እንዲያ ተከትሎ፤ በዚህ ወጥቶ በዚያ ወርዶ ወዘተ' ይላል።ሌላኛው ወገንም ሽማግሌዎቹን አመስግኖ የራሱን ድምጽ ያሰማል።የሁለቱን ወገን የሚሰሙት ሽማግሌዎች ደግሞ ሚዛናዊ ፍርድ ለመስጠት በተመስጦ ናቸው።የግራ ቀኙ ክርክር ተሰምቶ በማለቁ ሽማግሌዎች የሚናገሩበት ምዕራፍ ላይ ሲደርስ ሰብሳቢው ሽማግሌም ንግግራቸውን ጀመሩ፤

"የሁለቱንም ወገን ንግግር አደመጥን፤ እኛ ደግሞ እንናገር።ልጆቼ እኔ ሁላችሁንም የምመክረው እዚያ ጋር ጭቃ እያቦኩ ያሉትን ልጆች እንድትመለከቱ ነው።ልጆቹን ተመልከቶ ጭቃ እያቦኩ፤ በአቦኩት ጭቃ ቤት እየሰሩ፤ የሰሩትን ቤት መልሰው እያፈረሱ፤ መልሰውም እየሰሩ፤ እንዲሁም እየተጣሉ፤ ከጥል መልስ ደግሞ አብረው እየዘመሩ፤ በዙሪያቸው ለሚሆነው ነገር ቦታን ባለመስጠት በራሳቸው ዓለም ውስጥ ሆነው የሚኖሩ ናቸው።ይህ የሚያሳየው ግጭት ሊያጋጥም የሚችል ልንቀንሰው እንጂ ልናጠፋው የማንችል መሆኑን ነው።ወደ እናንተ ጉዳይ ስመጣ ሁሉም ነገር ክርር ያለ ሆኖ አገኘሁት።ሁሉም እኔ ያልኩት ካልሆነ በማለት ነገሩን ሁሉ አክርሮ የመያዝ ከጉዳዩ በላይ የከረረ።ምድራችን አንድ ወገን የፈለገውን በሙሉ የሚያደርግባት አይደለችም።ሁላችንም በጋራ በሰላም እንድንኖር፤ ሁላችንም አሸናፊ እንድንሆን አንዳችን ለሌላችን ፍላጎት ቦታን የምንሰጥበት፤ አንዳንዴም ለትልቁ ሰላም ሲባል የምንተወው ትናንሽ ነገር ያለበት አካሄድ የግድ የሚልበት ነው።

ለአሁኑ ጉዳያችሁን ሰማን አንድ ጥያቄ ግን ለእናንተ ላቅርብ፤ እስከአሁን በራሳችሁ ጫማ ውስጥ ሆናችሁ ተናገራችሁ፤ እስኪ አሁን ደግሞ በሌላኛው ወገን ጫማ ውስጥ ሆናችሁ ደግሞ ክርክራችሁን አሰሙ።ሌላኛው ወገን ያመመውን ህመም እያሰባችሁ የሌላውን ወገን እውነት አቅርቡለት።ሌላኛው ወገን እንዲሰማለት የሚፈልገውን እናንተ እስኪ አሰሙለት።" በማለት መድረኩን መልሰው ለግራ ቀኙ ሰጡ።ሁለቱም ወገኖች የሌላኛውን ወገን እውነት ላይ ቆመው እንደ ባለጉዳዩ አድርገው ደስ ባይላቸውም እንዲሁም የራሳቸውን ለማቅረብ በስሜት ውስጥ ሆነው እንዳቀረቡት ባይሆንም፤ የሽማግሌውን ቃል መፈጸም ያለበት ነበርና ለማሰማት ሞከሩ።ሰላምን መፍጠር ብቻም ሳይሆን ሰላምን ስለማብዛት የሽማግሌዎችን ቃል አክብረው ተናገሩ።ወደ መፍትሔው በሽማግሌዎቹ በኩል ለመድረስ ጥረት እያደረጉ፤

በዛሬው ጽሁፍ ሰላምን ስለማብዛት እንጽፋለን።ሰላምን መፍጠር፤ መጠበቅ እንዲሁም ማብዛት ከግለሰብ እስከ አገር እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ለማንም ማስረዳት አስፈላጊ አይደለም፤ ሁሉም ይረዳዋል።ሰላምን ለማብዛት አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦችን በሰላም ዙሪያ፤ ችግርን በመፍታት ዙሪያ፤ አዎንታዊ ተጽእኖ በመፍጠር አቅጣጫ ጥናት ካደረጉ አጥኚዎች የተገኙ ምክረ ሃሳቦችን መነሻ በማድረግ እንመልከት።

በአንድ አገር የፖለቲካ ማህበረሰብ እንዲሁም እስከ ግለሰብ ድረስ ባሉ ደረጃዎች ችግር ማጋጠሙ አይቀሬ ነው።በግለሰብ ህይወት ውስጥ፤ በትዳር፤ በአካባቢ፤ በእምነት ቦታዎች፤ በአገር ወዘተ ደረጃ የሚፈጠሩ ችግሮች ሁሌም ይኖራሉ።ችግሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ በማሰብ ችግር ፈቺ ሆኖ መገኘት ለማንኛውም ሰው የሚያስመሰግን ነው።በመጽሐፍ ቅዱስ "የሚያስተራርቁ ብጹዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና" በማለት ማስታረቅ የሚያሰጠውን ትልቅ ቦታ ያሳያል።ችግር ፈቺነት ባህል በሆነባቸው አካባቢዎች ችግር በመፍታት ሂደት ውስጥ ወደ ውጤት መድረስ የሚቻልበት እድሉ ሰፊ ነው።ሰላምን ለመፍጠርም ሆነ ለማብዛት ችግር ፈቺነት ያለውን ሚና ተመልክቶ ወደ ግጭት የሚወስዱ ነገሮችን ከስራቸው ለመንቀል መስራት አትራፊ ያደርጋል።

እያንዳንዱ ሰው በተሰማራበት ዘርፍ ምንም ይሁን ምን ችግሮችን መጋፈጡ አይቀሬ ነው።የምንኖረው ውስብስብና ብዝሃ ህይወት ባለበት ዓለም ውስጥ ስለሆነ፤ ስራዎች የሚሰሩት ከሰዎች ጋር በሚፈጠር ግንኙነት ውስጥ ስለሆነ እና የምንጋፈጣቸውን ሁሉንም ሁኔታዎች ልንቆጣጠራቸው የምንችላቸው ስላልሆኑ ችግሮች ይከሰታሉ፤ ችግር ፈቺነት ደግሞ ሊኖር ግድ ነው፤ ሰላምን ለመፍጠርም ሆነ ለማብዛት።

የሚከተሉት ነጥቦች በየትኛውም ደረጃ ሰላምን የሚያደፈርስ ችግር ከመፈጠሩ በፊትና ከተፈጠረ በኋላ ማድረግ የሚገባንን ማወቅ ሰላምን ለማብዛት የሚረዳ ነው።

**1. ሰላምን የሚያሳጡ ችግሮችን አስቀድመው ማንበብ መቻል፣**

ችግሮች የማይቀሩ ስለሆነ አስቀድሞ ለማየት መሞከር ችግሩ በዝቶ ከሚያመጣው ጉዳት የመትረፍ እድልን ይሰጣል። ጠንካራ መሪዎች አስቀድመው ችግሮች ሳይመጡ ሊተነብዩአቸው ይሞክራሉ።መንገዶች ሁሉ ቀላል እንደሆኑ የሚያስብ ሰዎች ሁልጊዜ ከችግር ጋር ተጋፍጠው ችግርን በመፍታት ላይ ተጠምደው ይገኛሉ።ነገሮችን መርምሮ ሊመጣ የሚገባውን መለየት መቻል አስፈላጊ ነው።

**2. የሰላም እድልን ለማስፋት ተጨባጭ እውነታን በአግባቡ መረዳት መቻል፣**

ተጨባጭ እውነትን በመካድ ውስጥ መገኘት አንዳንዴ አላስፈላጊን ዋጋ ያስከፍላል።ሰላምን ለማብዛት ሁል ጊዜ ተጨባጩን እውነት መረዳትና ለእውነታው ምላሽ መስጠትን ይጠይቃል።ሰዎች ለሚገጥማቸው ችግሮች በተለያየ መንገድ ምላሽ ይሰጣሉ፤ አንዳንዱ ችግሩን ለመቀበል ባለመፍቀድ ምላሽ ሲሰጥ ሌላው ደግሞ ችግሩን ለመቀበል ይፈቅዱና ከነችግሩ መኖር ላይ ራሳቸውን ያገኛሉ፤ አስተዋይ ሰዎች ግን ችግሩን ተቀብለው ነገሮችን ጥሩ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ።መሪዎች ሁልጊዜ ችግርን ተቀብለው ነገር ግን ለማስተካከል ጥረት የሚያደርጉ መሆን አለባቸው።

ዛሬ በተለያየ አቅጣጫ የሚገጥመንን የሰላም ችግር ለመፍታት ላለንበት እውነታ ተጨባጭ ምላሽን ለመስጠት መሞከር ብልህነት እንጂ ሞኘነት ሊሆን አይችልም።ከእውነታ በተቃራኒው በሚደረግ ጉዞ ውስጥ ግን በመጨረሻ ለኪሳራ የሚዳርግ ክስተት ውስጥ ልንገኝ ያስችለናል።

**3. ከትናንሽ ጉዳዮች ራስን ማቀብ፣**

ሁሉም ሰው ከጥቃቅን ነገሮች ይልቅ ዋናውን ነገር በማሰብ መኖር ቢችል አትራፊ ይሆናል።መሪዎች ትልቁን ምስል እያዩ መምራት ይኖርባቸዋል።ከትልቅ ምስል በትንንሽ ጉዳዮች ላይ ተጠምደው የሚገኙ ሰዎች በስሜት ብቻ እየተመሩ መሄድን ምርጫቸው ያደረጉ ናቸው።እንዲሁም በዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ በመግባት አንኳር የሆነውን ጉዳይ ከመመልከት መስነፍም የለባቸውም።

ሰላምን ለማብዛት በዝርዝር ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ከማተኮር ትልቁን ምስል መመልከት አትራፊ ያደርጋል።ምንም ይሁን ምን ሰዎች እንዳይሞቱ፤ ሰላማቸውን እንዳያጡ፤ የሚመገቡት እንዳያጡ፤ ወዘተ ሌላውን ዝርዝር ጉዳይ ግን በመተማመን መንፈስ በጊዜ ውስጥ እያዩ መሄድ በፖለቲካው መድረክ ለሚፈጥሩ ቅራኔዎች የተሻለው መንገድ ይመስላል።

**4. ወደ ሰላም የሚያደርስ ቅደም ተከተልን መከተል፣**

ችግሮችን ለመፍታት ይቻል ዘንድ ቅደምተከተል ወሳኝነት አለው።ወደ ጦርነት ለመግባት የሂደት ውጤት እንደሆነው ሁሉ ከጦርነት ወደ ሰላም ለመድረስ እንዲሁ ቅደምተከተል ያስፈልጋል።ቅደምተከተሉን ሁሉም በጥንቃቄ ሊቀርጽ ይገባዋል።እያንዳንዱ ግለሰብ እንደ ግለሰብ የቅደምተከተል ሃላፊነት አለበት።የጦርነትን የአንድ ወገን አሰላለፍ ደግፎ የቆመ ነገሮች ወደ ሰላም እንዲመጡ በሚሰራበት ጊዜ ትኩረቱ ሰላምን መስበክ ላይ መሆኑ ጥርጥር የለውም።መሪዎች ከሁሉም በላይ ቅደምተከተልን የማስተካከል ሃላፊነት አለባቸው።

በግል ሕይወታችን የሚገጥመን ማናቸውም ሰላም ማጣትን አሸንፈን ለመውጣት ምን መቅደም ምንስ መከተል እንዳለበት በማመን ለአካሄዳችን ጥንቃቄ ማድረግ ጠቢብነት ነው።ሁሉንም ነገር በአንዴ ማሳካት የሚቻልበት ዓለም ውስጥ ባለመሆናችን ቅደም ተከተል አስፈላጊ ነው።በታሪክ ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች ሳይፈቱ አንዱ ቅራኔ ወደ ሌላ የቅራኔ ምእራፍ ሊገባ የቻለው የቅደም ተከተል መዛነፍ መሆኑን ማሰብ አለብን።በትዳር ውስጥ የሚኖር ቅራኔ ቶሎ ካልተፈታ ይባዛል የሚባለውም በዚህ ምክንያት ነው።በሌሎች ግንኙነቶችም ውስጥ ልዩነቶች ሲኖሩ ቶሎ ለመፍታት ጥረት ማድረግ ተገቢነት አለው።የቱ ይቅደም የቱስ ይከተል የሚለውን ግምት ውስጥ በማስገባት።

ጠቢብነት ቅደም ተከተሎችን አስተካክሎ ለመፍትሔው አንድ እርምጃ ወደፊት መቅረብ መቻል ነው። ሪቻርድ ስሎማ የተባሉ ሰው ሁሉንም ችግሮች አንድ በአንድ ልትፈታ አትሞክር ነገርግን ቅደምተከተል ሰጥተህ ተራበተራ ልትፈታቸው ሞክር በማለት ይመክራሉ።በችግር አፈታት ዙሪያ መሪዎች የሚቸገሩት በዙሪያቸው በርካታ ችግሮች ኖረው ችግሮችን እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መፍታት እንደሚችሉ አለማወቃቸው ላይ ነው።በዙሪያህ ልትፈታቸው የሚገቡት ችግሮች ብዙ ከሆነ በቅድሚያ አሁን ልትፈታ የምትችለውን በማስቀደም ሌላውን ለማስከተል ሞክር።

**5. ሰላምን ዋናው ግብ በማድረግ በየትኛውም ተግዳሮት ውስጥ አስመተው፣**

ሰላምን መፍጠር፤ ሰላምን ማብዛት፤ ሰላምን መጠበቅ በክፋት በተሞላች ምድር ውስጥ በቀላሉ የሚቻል ነገር አለመሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው።ሰላምን ዋናው ግብ ያደረገ ሰው በየትኛውም ተግዳሮት ውስጥ ቢያልፍም ግቡን ተከትሎ ወደፊት ይራመዳል እንጂ ወደኋላ አይመለስም።መሪዎች በተግዳሮት ግብን ማእከል አድርገው የሚጎዙ ናቸው።ሰላምን ማእከል አድርጎ መጓዝ ስሜትን ማረቅን፤ ከጥቅቃን ነገር ትልቁን ምስል መመልከትን፤ ከዛሬ ይልቅ አሻግሮ ነገን መመልከትን ይጠይቃል።

ደራሲ ጆርጅ ማቲው እንዲህ አሉ የምታስበው ነገር ማለት በህይወትህ ውስጥ ካሉት ነገሮች የሚበልጠው ማለት ነው።ከምትሰማው በላይ፣ ከምትኖርበት ቦታ በላይ፣ ከማህበራዊ መስተጋብርህ በላይ እንዲሁም ስለ አንተ ሰዎች ከሚያስቡትም በላይ ነው።ሁሉም



ፈተናዎች እራስህን ከእራስህ ጋር የሚያስተዋውቁህ ናቸው።ፈተናዎችህ እንዴት እንደምታስብና እንዴትም እንደተሰራህ የሚያሳዩህ ናቸው።

ከችግሮችህ ጋር ፊት ለፊት ስትጋፈጥ እንዴት ነው ምላሽ የምትሰጠው? ችላ ብለኸው በራሱ ጊዜ እንደሚሄድ ታስባለህ? ለመፍታት አቅም እንደሌለህ ሆኖም ይሰማሃል? ችግርን ለመፍታት ጥሩ ያልሆነ ልምድ ከእዚህ ቀደም ኖሮህ ተስፋ ቆርጠህስ ይሆን ወይንስ ፈተና ሲመጣ ለመጋፈጥ ፍቃደኛ ነህ? ፈተናዎች ገጥመውህ ስታሸንፋቸው ችግሮችን የመፍታት አቅምህን ያዳብሩታል።በየጊዜው የሚገጥምህን ችግር እየፈታህ በሄድክ ቁጥር በሂደቱ የምትማራው ነገርም ይበዛል።ነገር ግን ልትፈታው ካልሞከርክ ትወድቃለህ።

**የቤት-ስራ አድርገህ የምትወስደው ችግር የመፍታት አቅምህን ለማሻሻል የሚከተለውን አድርግ፣**

ችግሩን ተመልከት፡ - ችግሮችን ከመጋፈጥ ይልቅ መግፋትን የምትመርጥ ከሆነ ከእዚያ ውጣና ችግርህን ተመልከት።በምትጋፈጠው ጊዜ ስለሆነ ልምድ የምታገኘው ተጋፈጠው።መፍትሄ ሊገኝላቸው የሚገቡ በዙሪያህ ያሉትን ነገሮች መፍትሄ ለመፈለግ ጥረት አድርግ በሂደትም የችግር አፈታት አቅምህን እያዳበርክ ትመጣለህ።

የመፍቻ መንገድን ቀይስ - አንዳንድ ሰዎች ችግርን በመፍታት ውስጥ ከባድ ወቅትን ያሳልፋሉ፤ ምክንያቱም ችግርን የመፍታት ልምድ የላቸውም።የሚከተለውን TEACH የተሰኘውን ሂደት ተከተል፣

TIME - ችግሩን ከመሰረቱ ለመረዳት ጊዜ ውሰድ፣

EXPOSURE - ሌሎች እንዴት እንደሚሰሩ ለማወቅ ሞክር፣

ASSISTANCE - ቡድንህ ሁሉንም አቅጣጫ እንዲረዱ አድርግ፣

CREATIVITY - የተለያዩ መፍትሄዎችን አስብባቸው፣

HIT IT - የተሻለ የምትለውን መፍትሄ ተግብር

ዙሪያህን ችግር ፈቺዎች እንዲኖሩ አድርግ - አንተ ጥሩ ችግሩን መፍታት የምትችል ሰው ካልሆንክ ሊፈቱ የሚችሉ ሰዎችን ወደ ቡድንህ አምጣ።እነርሱም የአንተን ክፍተት በመሙላት ደግሞም ከችግር አፈታታቸው ትምህርት ልትወስድባቸው ትችላለህ።

**እስታዊ ጉርሻ፣**

ቦክሰኛው ግኒ ቱኒ የከባድ ሚዛን የዓለም ሻምፒዮን የሆነው ጃክ ድምፒሲን በማሸነፍ ነበር።አብዛኛው ሰው ቱኒ ማን እንደሆነ አያውቅም ነበር።ይህ ሰው ታዋቂ ከመሆኑ በፊት ሁለቱም እጆቹ ይሰበሩና ወደ ዶክተር ይቀርባል።ዶክተሩም በደረሰበት የእጅ ስብራት ምክንያት የዓለም ሻምፒዮን የመሆን እድል እንደ ሌለው ይነግረዋል።እርሱ ግን ሻምፒዮን መሆን ባልችም ግን ቦክሰኛ ሆኜ ከመቀጠል ወደ ኋላ አልመለስም በማለት ይቀጥላል።ነገርግን ሻምፒዮን መሆንም ቻለ።በመንገድህ ላይ በሚመጣ መሰናክል ከህልምህ እንዳትቀር ጥረት አድርግ።

# መሠረተ ልማት

## ከ6 ሺ በላይ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚገነባው የካሊድ-ዲጆ የመስኖ ፕሮጀክት

**መሳኩ ኤሮሴ**

ኢትዮጵያ ከ5 ነጥብ 8 እስከ 7 ነጥብ 5 ሚሊየን ሄክታር የሚሆን መሬቷ በመስኖ ሊለማ የሚችል መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ባለፈው ዓመት ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የወጣው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬት ውስጥ 1 ነጥብ 2 ሚሊየን ሄክታሩ ብቻ ነው በመስኖ እየለማ ያለው። ይህም ማለት በሀገሪቱ ውስጥ በመስኖ ሊለማ ከሚችል መሬት ውስጥ ጥቂቱን ብቻ እያለማች ስለመሆኑ ማሳያ ነው።

የመስኖ ልማት መሰራት ባለበት ልክ ባለመሰራቱ በርካታ አርሶ አደሮች የዝናብ ወቅትን እየጠበቁ የግብርና ስራቸውን ይሰራሉ። በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በዓመት ሁለትና ከዚያ በላይ ጊዜ ማምረት የሚችሉ አርሶ አደሮች የመስኖ ልማት ትኩረት ያላገኘ በመሆኑ ምክንያት የዝናብ ውሃ በመጠበቅ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እያመረቱ ነው። ይህም ሀገሪቱ በምግብ ራሷን እንዳትችል ካደረጓት ምክንያቶቹ አንዱ ሊባል ይችላል።

ለበርካታ ዓመታት በሀገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ የግብርና ምርቶችን ከውጭ ሀገራት ስታስገባ ኖራለች። የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ አቅም ማሟላት አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ለኢንዱስትሪ የሚሆኑ የግብርና ምርቶች ጭምር ከውጭ ሀገራት ስታስገባ ነው የኖረችው። ይህም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና ሲያሳድር ቆይቷል።

መንግስት ይህንን ሁኔታ ለመቀየር በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ የአስር አመት መሪ እቅድ ላይ ለመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው። ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ሀገሪቱ ለመስኖ ልማት ከፍተኛ በጀት መድባ እየተንቀሳቀሰች ነው። በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ለመስኖ ልማት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷል። በመላ ሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች አዳዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ እና የተጀመሩትን ለማጠናቀቅ ጥረቱ ቀጥሏል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ግንባታቸው ከተጀመሩት የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች መካከል በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በስልጤ ዞን በዳሎቻ ወረዳ በካሊድ ዲጆ ወንዝ ላይ እየተገነባ የሚገኘው የካሊድ- ዲጆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት አንዱ ነው። ይህ ፕሮጀክት በመንግስት ትኩረት ከተሰጣቸው የመስኖ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ብዙነህ ቶልቻ እንደሚያብራሩት፤ በ1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በጀት እየተገነባ የሚገኘው የካሊድ-ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ለግንባታው በወርሃ ሰኔ 2 ቀን 2012 ዓ.ም ስምምነት የተደረገ ሲሆን፣ ከአንድ ዓመት በኋላ በመስከረም ወር 2013 ዓ.ም ነው ግንባታው የተጀመረው። ፕሮጀክቱን የ2016 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ለማጠናቀቅ ግብ ተቀምጦለታል።

ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ አንድ ሺህ 800 ሄክታር መሬት በመስኖ የማልማት አቅም አለው። ከስድስት ሺ በላይ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል። በፕሮጀክቱ ከሚከናወኑት ውቅሮች መካከል የግድቡ ርዝመት 1ሺ828 ነጥብ 25 ሜትር፣ የግድቡ ከፍታ 26 ነጥብ 4 ሜትር ሲሆን ስምንት ሚሊዮን ሜትር ኪዮብ ውኃ በመያዝ 1ሺ800 ሄክታር መሬት ያለማል። ግድቡ የሚይዘው ውኃ 64 ሄክታር ላይ ወደ ኋላ እንደሚተኛም ነው ያብራሩት።

ፕሮጀክቱን መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በባለቤትነት እያስገነባው ሲሆን፣ የፕሮጀክቱ ተቋራጭ ደግሞ የደቡብ ውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ነው። የፕሮጀክቱ በአለትና በውስጥ በኩል በሸክላ አፈር እንደሚገነባም አቶ ብዙነህ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ብዙነህ ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ እየተገነባ ያለበት አካባቢ አየር ንብረት እና አፈር ለምርታማነት እጅግ አመቺ ነው፤ በአካባቢው የመስኖ ልማት ስራ ባለመሰራቱ የአካባቢው አርሶ አደሮች ከምቹ የአየር ንብረትና ለእርሻ አመቺ ከሆነው አፈር በሚፈለገው ልክ ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቆይተዋል። አርሶ አደሮቹ በአካባቢው ለመስኖ ልማት አስቻይ ሁኔታ ባለመኖሩ በዓመት አንድ ጊዜ ነው ሰብሎችን እያመረቱ የሚገኙ ሲሆን፣ በቂ ውሃ ካገኙ ከደጋ ሰብሎች በስተቀር ሁሉንም አይነት አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ሰብል ማምረት ይችላሉ።

በተለይም በአካባቢው በብዛት በምርት የሚታወቀውን በርበሬ በስፋት ለማምረት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ፕሮጀክቱ የአፈር መሸርሸርን በመከላከል እና በዘመናዊ ዘዴ በአመት ሁለት ጊዜ እና ከሁለት ጊዜ በላይ የተለያዩ ምርቶችን ማምረት ያስችላል። የቆላ ስንዴ፣ አቮካዶ፣ ፓፓዬ እና ቲማቲምም በአካባቢው በስፋት ሊመረቱ ከሚችሉ ምርቶች መካከል ናቸው። በዚህም የአካባቢው ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ከፍ ማድረግ ያስችላል።

ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚፈጠረው ሰው ሰራሽ ሀይቅ ለአሳ እርባታም ሊውል እንደሚችል አቶ ብዙነህ ጠቁመዋል። ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው አሳ እያረቡ ለከተማውም ዓሳ ማቅረብ የሚችሉበትን ሁኔታ እንደሚፈጥር ገልጸዋል፤ በዚህ ሁሉ ለአካባቢው ማህበረሰብ የገቢ ምንጭ ከመሆኑ ባሻገር የስራ እድል ይፈጥራል ይላሉ። ከዚያ ባሻገር የሚፈጠረው ሀይቅ አካባቢው የአረንጓዴ እጽዋት እንዲላበስም ያደርጋል። ይህም የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ከማገዙ ባሻገር የአካባቢውን ውበት ይጨምራል ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ አቶ ብዙነህ ማብራሪያ፤ የካሊድ- ዲጆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ከወራቤ ከተማ ቅርብ ርቀት ላይ በመገንባት ላይ ያለ መሆኑም ፕሮጀክቱን በሀገራችን ውስጥ ከተገነቡት እና እየተገነቡ ካሉት ከሌሎች የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለየት ያደርገዋል። የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶቹ ከከተሞች ቢያንስ የ100 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገነቡት።

የካሊድ- ዲጆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግን ከወራቤ ከተማ በ10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እየተገነባ ነው። ከተማው እያደገ ሲሄድ በፕሮጀክቱ እና በከተማው መካከል ያለው ርቀት ከ10 ኪሎ ሜትርም ያጠረ ይሆናል። የመስኖ ፕሮጀክቱ በከተማው አቅራቢያ መገንባት ለከተማው እና አካባቢው በርካታ እድሎችን ይዞ ይመጣል። በመሆኑም ግድቡ ለመዝናኛነት ሊውልም ይችላል። ሪዞርቶችን እና ሆቴሎችን መገንባት ከተቻለ በአካባቢው የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር የሚያስችል ነው።

ከወራቤ ዩኒቨርሲቲም በቅርብ ርቀት ላይ እየተገነባ ያለ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ለዩኒቨርሲቲው ብዙ ፋይዳ ሊኖረው ይችላል፤ የሚፈጠረው ሰው ሰራሽ ሀይቅ ላይ የተለያዩ የዓሳ ዝርያዎች ስለሚኖሩ ዩኒቨርሲቲው በነዚያ የዓሳ ዝርያዎች ላይ ምርምር ሊያካሂድ ይችላል። የተለያዩ አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች ላይ ጥናት በማድረግ እና ዝርያዎችን በማሻሻል ለማህበረሰቡ እንዲያቀርብ ያስችላል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ በአሁኑ ወቅት ለበርካቶች የስራ እድል መፍጠሩን የጠቆሙት የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ፤ በ2014 በጀት ዓመት ለአካባቢው ነዋሪዎች ለ85 ወንዶች፣ ለ52 ሴቶች በድምሩ ለ137 ሰዎች የስራ ዕድል መፍጠሩን ጠቁመዋል። በቀጣይም ለተጨማሪ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር እንደሚችል አመልክተዋል።

የካሊድ-ዲጆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት የግድብ እና ተያያዥ ስራዎች እንዲሁም የመስኖ አውታር ግንባታን በ2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት የ14 ነጥብ 53 በመቶ አፈጻጸም በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 56 ነጥብ 55በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሰራ ነው።


ፕሮጀክቱ በ2016 ይጠናቀቃል ተብሎ ቢታቀድም፣ በተለያዩ ተግዳሮቶች ምክንያት ፕሮጀክቱ መዘግየት እንደሚታይበት ይጠቁማሉ። ከፕሮጀክቱ ተግዳሮቶች መካከል የካሳ ክፍያ መዘግየት፣ በባለድርሻ አካላት በኩል የሚደረግ እገዛ እና ድጋፍ በቂ ያለመሆን ፣የሥራ ተቋራጭ ድርጅቱ የአቅም ውስንነት፣ የማሽነሪ አቅርቦት አነስተኛ መሆን ተጠቃሽ መሆናቸው ጠቅሰው፣ ተቋራጩ ባሳየው ዝቅተኛ አፈጻጸም ምክንያት ማስጠንቀቂያ እንደተጻፈበትም ያመለከቱት። ተቋራጭ ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ማሽነሪዎችን በአፋጣኝ ወደ ፕሮጀክቱ እንዲያስገባ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል ይላሉ። የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን ተግባራዊ ካደረገ ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ሊጠናቀቅ ይችላል ብለዋል።

ተቋራጩ አቅሙን ማሻሻል፣ አዳዲስ ማሽነሪዎችን ማስገባት፣ የሰው ሀይል መጨመር ካልቻለ በ2016 መጨረሻ ለማጠናቀቅ አዳጋች እንደሚሆን ጠቅሰው። የማሽነሪዎችን ቁጥር ከጨመረ፣ እና በቂ የሰው ሀይል ካስገባ ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ይጠናቀቃል ሲሉ ጠቁመዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎች የተወሰዱ ሲሆን፣ ከተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል የካሳ ግመታው በአስቸኳይ ተሰርቶ ገንዘቡ ወደ ወረዳ ተልኮ እንዲከፈል መደረጉ፤ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የክልል፣ ዞን እና ወረዳ መስተዳደሮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ ለፕሮጀክቱ የሚፈለገው ድጋፍ እና እገዛ እንዲደረግ ግፊት መደረጉ ተጠቃሽ ናቸው ፤ ሆኖም አሁንም ያሉ ክፍተቶችን በትኩረት ለይቶ መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል።

የፕሮጀክቱ ግንባታ በተጀመረበት እለት ንግግር ያደረጉት የዞኑ፣ የወረዳው እና የከተማ አስተዳደሩ የስራ ሀላፊዎች ፤ ፕሮጀክቱ ለረጅም ዓመታት የህዝብ የልማት ጥያቄ ሆኖ ቆይቶ በጉጉት ሲጠበቅ እንደነበረ ጠቁመው ነበር። ዞኑ በትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ የነበረውን ልምድ እንደ እርሾ በመጠቀም ለፕሮጀክቱ ስኬታማነት የዞኑ አስተዳደር አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግም ቃል ገብቶም ነበር። ግድቡ ለኢኮ ቱሪዝም፣ ለመስኖ ልማት ሁለንተናዊ ፋይዳው የጎላ በመሆን ለግድቡ ስኬት አስፈላጊውን ትብብር በማድረግ ከተቋራጩ ተቀራርበው እንደሚሰሩም አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል።

ፕሮጀክቱን በተያዘለት ጊዜ ውስጥ አጠናቅቆ ወደ ስራ ለማስገባት ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በተፋሰሱ ውስጥ በርካታ ስራዎችን መስራትም ያስፈልጋል። የተፋሰስ እንክብካቤ እና የአፈርና የውሃ ጥበቃ ስራ በስፋት መስራት የሚፈጠረው ሀይቅ በደለል እንዳይሞላ አስፈላጊ ተግባር ነው። በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት በመተባበር የተፋሰስ እንክብካቤ እና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ በስፋት ሊሰሩ ይገባል። በተለይም የዞኑ እና የወረዳው መዋቅር በዚህ ረገድ ጠንክሮ መስራት ይጠበቅባቸዋል።



ፎቶ፦ ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የፌስቡክ ገጽ

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከሰላም ስምምነቱ ተጠቃሚ ለመሆን ሁሉም የሚጠበቅበትን መወጣት አለበት!

ጦርነት ሀገር አውዳሚ ነው። ሕዝብ ጨራሽና አፈናቃይ ነው። በሰዎች ስነልቦና ላይ ጥሎ የሚያልፈው ጠባሳም በጊዜ ሂደት ካልሆነ በስተቀር በቀላሉ የሚሽር ቁስል አይደለም። ይሄንኑ በተደጋጋሚ ጊዜ በሃገራችንና በዓለም ላይ ከታዩ ጦርነቶች አይተናል። ሀገሮች ፈርሰው ዜጎች ሲሞቱና በየሀገራቱ ሲሰደዱ በቅርቡ እነሶሪያን፣ ሊቢያን፣ የመንን... ሁሉ አይተናል። ሆኖም አሁንም በቅርቡ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት በሀገራችን አሳዛኝ ፣ ዘግናኝና አስከፊ የጦርነት ጉዳቶችን አስተናግደናል።

ሆኖም አሁን መንግሥት ባለው ሆደ ሰፊነት ችግሩ ሁሉ በሰላማዊ ንግግር እንዲፈታ ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካ የመፍታት እሳቤ በአፍሪካ ኅብረት አሸማጋይነት የሰላም ስምምነቱ እውን ሆኗል። ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ሁሌም አጥብቀው የሚሹትና እንዲሆንም የሚመኙት ስለሆነ እሰየው የሚያስብል ነው።

አሁን ቀጣዩ እርምጃ ችግሩ በነበረባቸው አካባቢዎች ያለው ሕዝብ ኃዘንና ቁስሉን ሳያስብ ከሰላም ስምምነቱ ተጠቃሚ ለመሆን ዝግጁ እንዲሆን መሥራት ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ለሰላም ስምምነቱ የሚጠበቅበትን ሁሉ መወጣት አለበት።

በእርግጥ ጦርነቱ ከፍተኛ ኪሳራን ያስከተለ፣ የስነልቦና ጫናን የፈጠረ እንደ ማኅበረሰብም በቤተሰብ መካከል እንኳን ሳይቀር መለያየትን ጭምር ያስከተለ መሆኑ አይዘነጋም። ሆኖም ግን ሕዝብ የገጠመውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቡናዊ ጫና እንዲያክም ሰፊ የእፎይታና የጥሞና ጊዜ እንዲያገኝ በትዕግስት መሥራት ይጠይቃል። አሳዛኙ ክስተት እውነተኛ ትምህርት አድርጎ መውሰድ ይገባል።

ዛሬ ላይ ቆመን የነገውን ተስፋችንን ማስተካከልና መሥራት ይጠበቅብናል። ያለፈውን መጥፎ የጦርነት ጊዜ የማያዳግም ትምህርት የምንቀምርበት አጋጣሚ አድርገን ለታሪክ በመተው ካለፈው ሂደት መማር አለብን። ያለፈውን የባከነ የልማትና የዕድገት ጊዜያችንን ለማካካስ በቁጭት የምንሠራበት እንዲሆንም በሁሉም መልኩ ጥረት ማድረግ አለብን።

ይህንን ስናደርግ ብቻ ነው በጦርነት ያጣነው ጉዳት መልሰን የምንገነባው፤ ይህንን ስናደርግ ብቻ ነው የሀገር አንድነት ወደ ነበረበት የምንመልሰው። ለዚህ ደግሞ የአዕምሮ ዝግጁነትና የልቦና ቀናነት ያስፈልጋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሃገራችን በተካሄደው ጦርነት ብዙ ሀብትና ንብረት ወድሟል። የሰው ልጆች ሕይወት ተቀጥፏል። እጅግ ብዙ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራን ደርሷል። እንዲሁም ከወደመው ሃብትና ንብረት፤ ከተፈናቀለውና ለረሀብና ችግር ከተዳረገው ሕዝብ በተጨማሪም የስነልቦና ችግር ያስተናገደው በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ነው። በአንድም በሌላም ምክንያት ዜጎች የጦርነቱ ተጎጂዎች ሆነዋል።

ይሁን እንጂ ጦርነቱ ያመጣውን ከባድ ኪሳራ ዛሬ ማረምና ማስተካከል የሚቻለው ለሰላም ስምምነቱ ጠንክሮ በመሥራት ብቻ ነው። ምክንያቱም የሰላም ስምምነቱ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው። ለዚህም ነው ስምምነቱ ስኬታማ እንዲሆን ሁሉም አካል የሚጠበቅበትን ሁሉ ማድረግና መሥራት አለበት የሚባለው።

የሰላም ስምምነቱ ሉዓላዊነትን ያረጋገጠ የኢትዮጵያ ልዩነትን የሚያጠብ ፣ ጥላቻ ፣ ቂምና በቀልን አጥፍቶ ሕዝብን ወደ ቀደመ አንድነቱና መተሳሰቡ የሚመልስ ኃይል ያለው ነው። የወደመ የሃገርና የሕዝብን ንብረት መልሶ በመገንባት ሕዝቡ የቀደመ ኑሮውን እንዲኖር የሚያስችል ነው። በመሆኑም ለዚህ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።

በተለይ በችግር የተፈተኑ የትግራይ፣ የአማራና የአፋር ክልል ነዋሪዎች ብርሃን ናፍቋቸዋል። የመገናኛ አውታሮች ተቋርጠው ከዘመድ አዝማድ ተቆራርጠው ቆይተዋል። ሠርቶ መብላት ብርቅ ሆኖባቸዋል። ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውሎ መግባት የሩቅ ዘመን ታሪክ መስሏቸዋል። በአጠቃላይ ሕዝቡ ከጨለማው የሰቀቀን ኑሮ መውጣት ናፍቆታል።

አሁን ለሁለት ዓመታት በችግርና በስቃይ የኖረው ሕዝብ ወደ ቀደመ ሰላሙ ተመልሶ ሰላማዊ ኑሮን የሚጀምርበት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መክፈቻ ነው። ይሄንን የተጎዳን ሃገርና ሕዝብ መልሶ መገንባት ታዲያ የሚጠበቀው ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነው፤ የሀገራችን ሰላም ተመልሶ ሁሉም በራሱ ጥሮና ግሮ ፤ ሠርቶና ለፍቶ እንዲኖር የጦርነት ሳይሆን የልማት መለከት የሚለፈፍበት ዘመን እንዲመጣ ሁሉም ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት።

ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው። ወጥቶ ለመግባት ፣ ያሰቡት ደረጃ ለመድረስ ከሁሉም በላይ ሰላም ወሳኝ ጉዳይ ነው። ምንም ነገር ለማድረግ አርቆም ሆነ አቅርቦ ለማሰብ ፤ አስቦ ለመሥራት፤ ሰርቶ ለመለወጥ የሀገር ሰላም እጅጉኑ ያስፈልጋል። ስለዚህ አሁን በመንግሥት ሆደ ሰፊነት ለሰላም ባለው ዝግጁነት በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት የሰላም መንገዱ በጥሩ ሂደት ላይ ይገኛል። ይሄ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ተሳክቶ የሰላም ሀሳቡ በድል ይቋጭ ዘንድ ሁሉም ለሰላም ስምምነቱ የበኩሉን ሁሉ ማድረግ እና የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ለውጪ ጠላት መሳሪያ እንዳንሆን እንንቃ!

ፈኔት (ከጠሮ)

ኢትዮጵያ የአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ህዝብ የኩራት ምንጭ ናት:: ይህንን ለማደብዘዝና በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያን ለማዋረድ የሚደክሙ ብዙዎች ናቸው። ይህም የአደባባይ ሚስጥር ነው። በዚህ ምክንያት ነፃነት መለያዋ የሆነች አገር ድህነት አንገት አስደፍቷት ዓመታትን አሳልፋለች::

እንደ ሰሞኑን ሁሉ ኢትዮጵያን የሚያዳክሙ ድርጊቶችን በመፈፀም አሸባሪዎችን እና ጸረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን በመፍጠርና በማሳደግ ባገኙት አጋጣሚ አገሪቱን ለማዳከም በሚጥሩ የውጪ ጠላቶች ምክንያት ኢትዮጵያ በውስጥ ችግሮቿ እየተናወጠች ከድህነት መውጣት መንታ ልጅን በምጥ የመውለድ ያህል ፈተና ሆኖባት ኖራለች::

እነዚህ የውጪ ጠላቶች ዋነኛ መነሻቸው ጥቁሮች ከነጮች እኩል መሆናቸውን ለዓለም ያሳየች አገር አለች እንዲባል ፈፅሞ አለመፈለጋቸው ነው:: እንኳን መኖር በታሪክ ውስጥ ስሟ እንዲጠቀስ አይሹም:: በቀኝ ገዢ አልገዛም ያለች እና ለጥቁሮች ሁሉ ኩራት የሆነች አገር ስለመኖሯ ማሰብም ሆነ ስለእርሷ መስማት ለአንዳንድ ነጮች የሚፈጥርባቸው የመበለጥ ስሜት የሚናቅ አይደለም::

አፍሪካን በመበዝበዝ ያደጉና በቀጣይም የመበዝበዝ ፍላጎት ያላቸው አገራት በ1888 ዓ.ም እና በ1933 ዓ.ም ለነጭ አልገዛም ብላ በዓለም አደባባይ ትልቅ ታሪክ መሆኑዋን በማውጠንጠን፤ ለአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆኑ ለሌሎችም ቀኝ ተገዢዎች ስለነፃነት እንዲያስቡና እንዲታገሉ በር እንደከፈተች በማሰላሰል፤ በቀጣይም የኢኮኖሚ ነጻነቷን በራሷ አቅም አጎልብታ፤ የዓለም ገዢነን አስተሳሰብን በራሳቸው ውስጥ የገነቡ አገራትን ትዕዛዝ አልቀበል ትላለች የሚል ስጋት አለባቸው።

ልትሄድበት የቀረጠችበት የብልጽግና መንገድ ለሌሎች አፍሪካውያን አገራት እንደ ቀደመው ዘመን አዲስ ነጻነት /የኢኮኖሚ ነጻነት/ በማጎናጸፍ፤ ራሳቸውን ችለው ከምዕራባውያን ተፅዕኖ ነፃ የሚሆኑበት አስቻይ ሁኔታ ይፈጠራል የሚል ፍርሀትም አለባቸው::

ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊየን ያላነሰ የህዝብ ቁጥር ለዛውም ከ75 በመቶ ያላነሰ ሊሠራ የሚችል የወጣት ኃይል ያላት መሆኗን ሲያስቡ ይጨነቃሉ:: በዛ ላይ እንደሌሎች አፍሪካ አገራት በነጮች አለመዘረፏ የብዙ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት መሆኗን ሲያስቡ ደግሞ የነገ ተስፋዋ፤ ልትፈነጥር የምትችልበት መሰረት ያላት መሆኑ ያሳስባቸዋል::

ነገ እነርሱን የምትገዳደር አገር ልትሆን የምትችልበት ሁኔታ መኖሩን ሲያስቡ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ዕቅድ ይዘው

**በሃሳብም ሆነ በተግባር አንድ ብሔር በሌላ ብሔር ላይ እንዲነሳ ተሳትፎ ማድረግ የብሔርን ነፃነት ማስከበር ሳይሆን ኢትዮጵያን የማጥፋት ዕቅድ ይዘው የሚንቀሳቀሱ የውጪ ጠላቶች ደጋፊ መሆን ነው**

ሳይታክቱ በትጋት ይሠራሉ:: ለዚህም ልዑዋላዊነቷን አስከብራ እንዳትኖር በውስጥ ክፍፍል እንድትዳከም የማይቧጠጥ የሰማይ ክፍል የማይገፋት ተራራ የለም::

እስካሁን ባይሳካላቸውም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሊገኝ የሚችለውን ምቹ መንገድ በመጠቀም ለዘመናት ኢትዮጵያውያንን በመከፋፈል ለማዳከም ብዙ ሰርተዋል:: ነገር ግን ኢትዮጵያ ዛሬም ስሟ አልጠፋም:: አሁንም ኢትዮጵያ የምትባል አገር አለች:: ነገም ትኖራለች::

ይህን እውነት ያልተረዱ /ተረድተውም አገርን ከራሳቸው በላይ አድርገው የሚያዩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ከውጪ ጠላቶች ጎን በመቆም ቀርቦ በመወያየት ሳይሆን ርቆ ጫካ ገብቶ ጦር በመነቅነቅ ኢትዮጵያውያንን በመፍጀት፤ መንግስትን በማዳከም፤ የውጪ ጠላት መጠቀሚያ በመሆን ኢትዮጵያ ለዘመናት የድህነት ቀንበርን ተሸክማ እንድትኖር ሰርተዋል፤ አሁንም እየሰሩ ነው::

አሁንም የዓለም ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ኢትዮጵያን እየኮረኮሙ ለመቅበር የማይጠቀሙት መንገድ የለም:: አንደኛው እና አሁን አሁን በስፋት እየተጠቀሙበት ያለው አገር ውስጥ ክፍፍል ተፈጥሮ በጎሳ ግጭት ህዝብ እንዲተላለቅ መደላድል መፍጠር ነው:: በሌላ በኩል ኢኮኖሚያዊ ጫና በመፍጠር ሕዝብ ተማሮ ከመንግስት ጋር እንዲጣላ መሥራት ነው::

አሁንም እንደሚታየው ምዕራባውያን የተለያዩ የዓለም የገንዘብ ተቋማት፣ ገንዘብ አበዳሪዎች እና እርዳታ ሰጪዎች ነን ባዮችን በመጠቀም አሁንም ከድህነት ያልተላቀቀችውን ኢትዮጵያን ቢችሉ ለማፍረስ ባይችሉ ለማዳከም የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት ላይ ናቸው::

ከዚህም ውስጥ ዋነኞቹ ዕርዳታ እና ብድር አለመስጠት፤ በተለያየ መንገድ በኢኮኖሚው ሁኔታ ወይም በዋጋ ግሽበት ሕዝቡ እንዲማረር ማድረግ፤ የአገር ውስጥ አሸባሪ ድርጅቶችን በመደገፍ እና በማበረታታት አገርን ማዳከም ናቸው::

ወቅቱ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በእነዚህ የውጪ ጠላቶች ላይ ነቅተን ልንቆምበት የሚገባ ነው። አንዱ በገንዘብ ተታሎ ሲጮህ አብሮ ከመጮህ ይልቅ ቆም ብሎ ማሰብ ራስን እና አገርን የሚጠቅም ነው ወይ ብሎ ማሰላሰል ያስፈልጋል::

በሃሳብም ሆነ በተግባር አንድ ብሔር በሌላ ብሔር ላይ እንዲነሳ ተሳትፎ ማድረግ የብሔርን ነፃነት ማስከበር ሳይሆን ኢትዮጵያን የማጥፋት ዕቅድ ይዘው የሚንቀሳቀሱ የውጪ ጠላቶች ደጋፊ መሆን ነው:: እውቀት እና እውነተኛ ብቃት ያለው ማንኛውም ዜጋ ከሚናገረው ብቻ ሳይሆን ከሚያስበው ጀምሮ መነሻው ኢትዮጵያ ጎድላ ሳይሆን ሞልታ ለቀጣይ ትውልድ ማስረከብ ላይ ጠንክሮ መስራት አለበት::

መንግስትን መቃወም፤ የተለየ አቋም መያዝ ወይም ብሔርን የተመለከተ አጀንዳ መያዝ መብት ነው:: ሃጥያት አይደለም:: ነገር ግን የነፃነት ተምሳሌት የሆነችውን ኢትዮጵያን ለማጥፋት መተባበር ግን ደማቁን የኢትዮጵያን ቀይ መስመር መጣስ ነው:: ይህንን በሚመለከት የትኛውም ኢትዮጵያዊ ዝም ሊል አይገባም::

ለአገራችን ችግሮች አሁን ላይ ዋነኛው መፍትሔ ጦርነት አይደለም፤ የተለየ ሃሳብ ያለው ቀርቦ ጥያቄ ያንሳ፤ ሌላው ህዝብ ደግሞ ሀቀኛ ሆኖ በቅንነት ይስራ፤ ሁሉም ስለኢትዮጵያ ዘላቂ ዕድገት ይትጋ፤ ያለብሔር ልዩነት ሁሉም ይተባበር፤ ተራ የፖለቲካ ንትርክና አሉባልታ ይቁም፤ ሁሉም ኢትዮጵያ የውጪ ጠላት ያለባት መሆኑን ተረድቶ ይህንን ጠላት ለማሳፈር እና ከድህነት ለመላቀቅ በየሥራ ድርሻው ኃላፊነቱን ይወጣ፤ ይህ ከሆነ ኢትዮጵያ ተዓምረኛ ዕድገትን የምታሳይበት ዘመን ሩቅ አይሆንም:: ሰላም !

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

# የፈገግታው ቋጠሮ ሲፈታ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የፊታቸው ጸዳል በእጅጉ ሰው ያቀርባል፣ ለንግግር ይጋብዛል።በጨዋታቸው መሀል ፈገግ ማለት ልምዳቸው ነው።እያወሩ ፈገግ ይላሉ፣ ፈገግ እያሉ ያወራሉ።ፈጽሞ ለዓይን አይከብዱም። ቀረብ ብሎ ለማውጋት ቀለል ያሉ ናቸው።

ሁኔታቸውን ላስተዋለ ችግር ይሉትን የሚያውቁት አይመስሉም።በፊታቸው ብሩህነት ያያቸው ሁሉ እንዲህ ቢገምት አይፈረድም።በፈገግታቸው ማንነታቸው ተሸፍኖ ኖሯል።በፊታቸው ገጽታ ዕንባን በሳቅ መልሰዋል።ግንባራቸው ኮስታራ አይደለም።ውስጣቸው ግን በሌላ ስሜት ተይዟል። በፈግታ በተሸፈነ፣ በሳቅ ጸዳል በተሰወረ ድብቅ ችግር።

**ወጣትነትን በስራ**

አባባ ጉግሳ ደሜ ዕድሜያቸውን በመንግስት ስራ ላይ አሳልፈዋል።

ጉግሳ ደሜ በ1960 ዓ.ም ከትውልድ አገራቸው ጊንጪ ወለንኮሚ አዲስ አበባ መጡ።የዛኔ ገና ወጣት ነበሩ። የልጅነት ዕድሜያቸው ለስራ ዝግጁ ነበርና መቀመጥ አልሆነላቸውም። አገራቸው የሚያሳርሱት የአባታቸው መሬት ቢኖርም ከተማውን ወደዱት።

የከተማ ሕይወት እንደገጠር አይሆንም። ኑሮ እንደዛሬው ባይከብድም መተዳደሪያ ያስፈልጋል። ሰርቶ የሚገባ ለኪሱ ገንዘብ፣ ለቤቱ ጥሪት አያጣም። ጉግሳ ይህ ሁሉ አልጠፋቸውም። ቀያቸውን ትተው ሲወጡ ሥራ መያዝ ግድ እንደሆነ ያውቃሉ።

አዲስ አበባ በዘመድ ቤት የቆዩት ጉግሳ የልባቸውን ሊሞሉ ዞር ዞር ማለት ያዙ።ለእሳቸው የሚበጅ የሚመጥን ስራ ለማግኘት ወዳጅ ዘመድ ጠያየቁ። ያገኙትን እየመረጡ፣ የመረጡትን እየተው ጥቂት ቀናት ቆዩ።ወጣቱ እንግዳ በጥሩ ደመወዝ የመንግስት ሰራተኛ መሆን ፍላጎታቸው ነው። እንደብዙዎች በቀን ሥራ ውሎ ራሳቸውን ማድከም አልፈልጉም።እናም ጥቂት ጊዜያት ጠበቁ።

ከጊዚያት በኋላ ከጉግሳ ጆሮ የምስራች ደረሰ። በማዕድን ሚኒስቴር የስራ ቅጥር አገኙ።የጉግሳ ምኞት የመንግስት ሰራተኛ መሆን ነው።የልባቸው ሀሳብ ስለሞላ፣ የመጡበት ዕቅድ ስለተሳካ ደስ አላቸው። የቅጥሩን ሂደት አጠናቀው ስራ ሲጀምሩ በቢሮው የተላላኪነት መደብ ተሰጣቸው።

**አዲስ ሕይወት**

ጉግሳ በተቀጠሩበት ቦታ አቅማቸውን ሊያሳዩ መትጋት ያዙ።ያሉበት የስራ መደብ ቅልጥፍናን ይጠይቃል።ከስራው ቀድሞ መሮጥ፣ የታዘዙትን ፈጥኖ ማድረስ የግድ ይላል። ይህ እንዲሆን የወጣቱ ተቀጣሪ ጉልበት አልደከመም።‹‹አቤት ወዴት›› እያሉ ስራውን ለማቀላጠፍ ከልባቸው ባተሉ።

የጉግሳ ስራ ፍቅርና ቅልጥፍና በአለቆቻቸው ዓይን ከፍ ያለ ሞገስ አገኘ።ሥራ ወዳድነታቸው፣ ታዛዥነታቸው፣ ሰዓት አክባሪነታቸው ሚዛን ደፍቶ ታየ። ሁሌም ጠንካራ ሰራተኞች እንዲህ በሆኑ ጊዜ ለተሻለ መደብ ይታጫሉ።በስራው የሚከፍሉት ዋጋ በጎ ሆኖላቸው ዕድገትና ለውጥ ያገኛሉ።

ጉግሳ ይህ አይነቱን አጋጣሚ ለማግኘት ጊዜ አልፈጁም።የተላላኪነታቸው የስራ መደብ ወደ መዝገብ ቤት ሹም አሻግሮ የቦታና የደመወዝ ዕድገት አሰጣቸው።

አሁን ወጣቱ ጉግሳ ከተላላኪነት ስራ ወጥተው ቢሮ መቀመጥ ጀምረዋል።አዲሱ የስራ መስክ ከደንበኞች የሚያገናኝ፣ ከሰራተኞች የሚያቆራኝ ነው።ጉግሳ በዋሉበት የስራ መስክ ጥንካሬ አይለያቸውም።የተሰጣቸውን ሀላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ይጥራሉ።የሰራተኞችን የግል ማህደር በጥንቃቄ ይዘው ግዴታቸውን ይወጣሉ።

የመዝገብ ቤት ስራ ትኩረትና ሀላፊነት የሚያሻው ነው።ይህን የሚያውቁት ጉግሳ ስራቸውን በአግባቡ ይወጣሉ። የቀደመው ቅልጥፍናና ስራ ወዳድነት ከእሳቸው ጋር ነውና አሁንም ትኩረት አላጡም። ካሉበት ሙያ በተሻለ ደረጃ ሊያቆማቸው ምክንያት ሆነ።

ጉግሳ በአጭር ጊዜ ቆይታ ስራ ከጀመሩበት የተላላኪነት ሙያ ወደሌላ የስራ መደብ ለመሻገር አጋጣሚውን አገኙ።ከነበሩበት የመዝገብ ቤት ስራ ወደሌላ መደብ ተዛውረው እንዲሰሩ ከአለቆች ደብዳቤ ደረሳቸው።የተቀጠሩበት መስሪያ ቤት የስራ ባህርይ በቢሮ ብቻ አይወሰንም።በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የመዘዋወር አጋጣሚው ይበረክታል።



አቶ ጉግሳ ደሜ

አሁን ጉግሳ ያደጉበት የስራ መደብ በቢሮ የሚወሰናቸው አልሆነም።አዲሱ የስራ ዘርፍ በየመስኩ የሚያስወጣ፣ በየአገሩ የሚያዟዝር ሆኗል።እሳቸው በየአጋጣሚው ያላዩት፣ ያልሰሩበት ስፍራ የለም። ከቦታ ቦታ በመኪና እያቋረጡ ከስራው መስክ ተገኝተዋል።አጋዴንን በመሰሉ መኪና በማይገባባቸው ስፍራዎችም በአየር ትራንስፖርት ተጉዘዋል።

የዛኔ ቀብሪ ደሀር ፣ ቀላፎና ሌሎች የሱማሌ አካባቢዎች በእሳቸውና በአጋር የስራ ባልደረቦቻቸው የሚሸፈኑ ነበሩ።ጉግሳ ከመስክ ስራቸው በዘለለ በኑሮ በቆዩባቸው አካባቢዎች ዓመታትን ባስቆጠረ ቆይታ ዘልቀዋል።አብረዋቸው ከሚኖሩት ባለቤታቸው ያገኙት ፍሬ ባይኖርም ወለጋ በነበሩ ጊዜ አንድ ወንድ ልጅ ወልደዋል።ባለቤታቸውም ልጅ እንደራሳቸው ተቀብለዋል።

**ጉግሳና ዘንድሮ**

ጉግሳ ደሜ የዕድሜ ዘመናቸውን በመንግስት ስራ አሳልፈው ዕድሜያቸው በደረሰ ጊዜ በክብር በጡረታ ተሰናበቱ።ዓመታትን በጥንካሬና በድካም ያሳለፈው ጉልበታቸው እረፍት ባገኘ ጊዜ ከቤት ሊውሉ ግድ አለ።ጉግሳ ከጡረታ የሚቀበሉት ገንዘብ ወር የሚያደርስ የጓዳን ቀዳዳ የሚሸፍን አይደለም።

ዓመታትን አብረዋቸው የዘለቁት ባለቤታቸው ጤና ካጡ ቆይተዋል፤ ከእሳቸው የጋራ ፍሬ ባይኖራቸውም የዘመድ ልጆችን እንደራሳቸው አሳድገው ለቁም ነገር አድርሰዋል።ዛሬ ሁሉም በራሳቸው ዓለም የሚሮጡ፣ በግላቸው ሕይወት የሚባዝኑ ናቸው።ጉግሳ ወለጋ ሳሉ የወለዱት ልጃቸው ያቅሙን ይረዳቸዋል።በቅርብ ባይኖርም ወላጅ አባቱን አልዘነጋም።

ጉግሳ ወር ጠብቀው በእጃቸው የሚያስገቡት አንድ ሺ ብር የልብ ሞልቶ አያውቅም።እንዲህ መሆኑ ያለስራ ተቀምጦ በሀሳብ ለሚናውዝ አባወራ ኑሮን አክብዷል።በህመም ቤት የዋሉት ባለቤታቸው ወጥተው መስራት የሚችሉ አይደሉም።ይህን ልሞክር ቢሉ እንኳን ዕድሜና አቅም ማነስ የሚያራምዷቸው አልሆኑም።

አሁን ኑሮ እየከበደ ችግር እየጨመረ ነው።አንዳንዴ አዛውንቶቹ ባልና ሚስቶች የመኖር አማራጭ ይጠፋቸዋል።እንደ ቀድሞው ሮጦ የሚያድር ጉልበት ፣ ሰርቶ የሚገባ አቅም በሌለበት በሀሳብ ሲጨነቁ ይውላሉ።

ጉግሳና ሚስታቸው በደህና ጊዜ ያሳደጓቸው የዘመድ ልጆች ከቤት ብቅ እያሉ ቤት ያፈራውን ያበስሉላቸዋል። አውደ ዓመት በመጣ ጊዜም እንደወጉ ለመሆን ክብር አያሳጧቸውም።እንዲያም ሆኖ አሁን ላይ ኑሮን የሚያሸንፉት አልሆነም።ችግርን እንደሁኔታው ለመወጣት አቅም አንሷቸዋል ።

**ሳቂታው አዛውንት**

አብሯቸው የኖረው ፈገግታ ችግራቸውን የሸፈነ፣ ሕይወታቸውን የደበቀ ይመስላል። ቀርቦ ያዋየ ፣ የጠየቃቸው ቢኖር ግን ከሳቂታ ፊታቸው ጀርባ የተደበቀ እውነት መኖሩን ይረዳል። ፈገግታ የተሰጣቸው ልማድ መሆኑን ያውቃል። ችግሩ ማን ቀርቦ ያዋያቸው፣ ውስጣቸውን ማን ይወቅላቸው የሚለው ላይ ነው።

እኔ አጋጣሚውን አግኝቼ ከአባባ ጉግሳ ጋር ጥቂት አወጋሁ።ያገኘኋቸው ልደታ አካባቢ ስራ ከጀመረው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ውስጥ ነበር።ጉግሳ በስፍራው የመቆማቸው እውነት ከምገባ ማዕከሉ የሚያገኙትን ምሳ ለእሳቸውና ለህመምተኛዋ ባለቤታቸው ለመውሰድ ነው። ማዕከሉ እሳቸውን ለመሰሉ አቅመ ደካማ ወገኖች በቀን አንድ ጊዜ የምገባ መርሀ ግብር አለው።

ጉግሳ ሁሌም ሰዓቱን አክብረው በስፍራው ይደርሳሉ።እሳቸውን መሰል ችግረኞች ተቀምጠው በሚመገቡበት ዕልፍኝ የሚሰጣቸውን አመስግነው ይቀበላሉ። ከሚያገኙት በረከት ግን አንዲት ጉርሻ እንኳን ወደአፋቸው አይሉም።ከቤት ተኝተው የእሳቸውን እጅ የሚጠብቁ ሚስታቸውን ያስባሉ።

እሳቸው የዕድሜ መግፋት ከህመም ያንገላታቸው ወይዘሮ ናቸው።እንደቀድሞው አባወራቸውን ደፋ ቀና ብለው አይቀበሉም።ከጉግሳ እጅ የሚመጣውን በረከት ቀምሰው ለመዋል ደጁን ይናፍቃሉ።ልጃቸው በራሱ ሕይወት የሚኖር የቤተሰብ አሳዳሪ ነው። አንዳንዴ ሲታመሙ ብቅ ከማለት የዘለለ በቅርባቸው የለም።

ዛሬ አቶ ጉግሳና ባለቤታቸው የኑሮ ውድነት ያንገላታቸው ይዟል።ያላቸው አቅም በቀን አንድ ደረቅ እንጀራ የሚያስገዛ አልሆነም።ቀድሞ በሳንቲም የሚገዙት ዕቃ ዛሬ ብር ለውጦት ዋጋው በእጥፍ ጨምሯል።በየቀኑ ሽቅብ የሚንረው ኑሮ ውድነት በተለይ አባወራውን በእጅጉ ያሳስባቸዋል።

በጡረታ ዕድሜ የሚገኙት አዛውንት ያለፉበት የሕይወት ውጣ ውረድ ዛሬን በእፎይታ ሊያኖራቸው እንደሚገባ ያምኑ ነበር።ይህ እንዳይሆን ሕይወት በራሱ ፈተና ሆኖ እያንገላታቸው ነው።ሁሌም ደጋግመው ሲያስቡት የሚገርማቸው የዘንድሮ እህል ገበያ ነገር ነው።በእሳቸው ዕምነት መሬቱ ሰፊ እርሻው የሰጠ ነው። በየዓመቱ የሚገኘው በረከትም ዕልፎችን በወጉ መግቦ ያሳድራል።

ዛሬም የገጠሩ መሬት ብዙ የሚያበቅል፣ የሚያሳፍስ ነው።በከተማ ሲሆን ግን ታሪኩ ይቀየራል።የሚገኘው በረከት ገንዘብ አሸንፎት፣ ለጥቅም አዘንብሏል።የኑሮ ውድነቱ እሳቸውን ጨምሮ ሌሎችን እያንገዳገደ ነው።

**ችግር ያልፈታው ጎጆ**

አዛውንቶቹ ባልና ሚስቶች እንዳለፉት መልካም ዘመናት ሁሉ ዛሬም አልተለያዩም።ዕድሜ፣ ህመምና ችግር እየፈተናቸው በአንድ ተቆራኝተዋል።አንዳንዴ ሊጠይቋቸው ብቅ የሚሉ ዘመዶች ከእጃቸው ይረጥባሉ።ወይዘሮዋ የሚያገኟትን ይዘው እንደአቅም ለቤት፣ ለሆድ የሚውለውን ያስባሉ።ጥንዶቹ ተደማምጠው ማደራቸው መልካም ሆኗል።አባወራው ከሚያመጡት የሰሀን ምግብ የዕለቱን እየጎረሱ ስለነገው ፈጣሪን ተስፋ ያደርጋሉ።

ጉግሳ በቅርቡ ባጋጠማቸው የጤና እክል ከሆስፒታል ለሁለት ወራት ተኝተው የቀዶ ህክምና አድርገዋል። እሳቸው ለነገ የሚሉት ገንዘብ የላቸውም። ከቀበሌ ባገኙት የጤና መድህን የነጻ ታካሚ ናቸው።ዛሬን በጤና ቆመው ስለነገ ተስፋ ማድረጋቸው ከአግርሞትም በላይ ለምስጋና አብቅቷቸዋል።

አባወራው ዓውደ ዓመት በደረሰ ጊዜ እንደቀድሞው ቀንዱ የዞረ ሙክት፣ ለመግዛት ገበያ አይወጡም። ከመንደሩ ሰዎች ጋር ቅርጫ አይገቡም።ወይዘሯቸውም ቢሆኑ ለዶሮና ቅቤ፣ ለዳቦና ጠላው መቀነታቸውን አይፈቱም። ዛሬ የትናቱ ታሪክ ከእነሱ የለም።ለዓመት በዓሉ ወግ ደጁን የሚናፍቁ፣ የዘመድ እጅን የሚያዩ ሆነዋል።

ጉግሳ ዓመታትን በቆጠሩበት የመንግስት ስራ ደስተኛ ነበሩ።ጊዜና ጉልበታቸውን ሰጥተው ሀላፊነትን መወጣታቸው ዛሬ በእጅጉ ያኮራቸዋል።አሁን አቅማቸው ሲደክም ጉልበታቸው ሲዝል ያለፈውን ጊዜ ያስባሉ፣ ልጅነታቸውን ያስታውሳሉ። የከፈሉት ዋጋ በዕድሜ ዘመናቸው ለሀገራቸው ያበረከቱት ስጦታ ነውና ቆጭቷቸው አያውቅም።

በስራ ያሳለፈው ጉልበታቸው፣ በድካም የዛለው አካላቸው ዛሬ አቅም አጥቷል።‹‹ይሁነኝ›› ብለው ግን ሰዎችን ‹‹እርዱኝ ፣ አግዙኝ ›› ሲሉ አይጠይቁም። ትናንት ብር ሲቆጥር ደመወዝ ሲያስገባ የነበረ እጃቸው ዛሬ ፈጽሞ ለልመና አይዘረጋም።

አባባ ጉግሳ ኩሩ ናቸው።ችግር ከእሳቸው ባይርቅም የፊታቸው ፈገግታ ይህን አሳብቆ አያውቅም። ሁሌም በሳቂታው ፊታቸው ዛሬን ያደምቃሉ፣ ነገን ይሻገራሉ። ፈገግታቸው የውስጣቸው ሀቅ የሸፈነ ቢመስልም ቀርቦ ያወጋ፣ ያዋያቸው ከእውነቱ ጥግ ይደርሳል። የፈገግታው ቋጠሮ ሲፈታ ያለውን ሀቅ ይረዳል።

ጉግሳ ‹‹ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ›› በሆነው ኑሯቸው ከነገ ለመድረስ ትግል ላይ ናቸው።ዓመታትን የቆጠረው የትዳር ሕይወታቸው በዕድሜ ብዛት ታጅቦ ማግኘትን ከማጣት ቢያሳያቸውም ዛሬም ለመኖር ሲሉ ተስፋ አይቆርጡም።ፈገግ እንዳሉ ትናንትን አልፈዋል፣ ከዛሬ ደርሰዋል።ነገን አስበዋል። በሳቂታ ፊት፣ በማይፈዝ ፈገግታ።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከልጅነት እስከ ዕውቀት የዳበረ የንግድ ሥራ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ተወልደው ባደጉበት በምዕራብ ጉጂ ዞን ቀርጫ ወረዳ ጉራቼ ጀልዶ ቀበሌ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። በወቅቱ በትውልድ አካባቢያቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽ ባለመሆኑ ከትውልድ አካባቢያቸው 150 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ተጉዘው ዲላ ከተማ ነው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከተታሉት። ለትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸውና ንቁ ተማሪ እንደነበሩ የሚናገሩት አቶ ታደሰ ኤዴማ የዕለቱ የስኬት እንግዳችን ናቸው።

ጎበዝ ተማሪ እንደነበሩ የሚናገሩት አቶ ታደሰ፤ በ12ኛ ክፍል ያመጡት ከፍተኛ ውጤት ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም መግባት የሚያስችላቸው ቢሆንም፣ እርሳቸው ግን በወቅቱ ዩኒቨርሲቲ መግባትን አልመረጡም። ለዚህም ዋና ምክንያታቸው የ12ኛ ክፍል ፈተና ተፈትነው ውጤት እስኪመጣ በሚል የጀመሩት የጥሬ ወርቅ ንግድ ነው። ከግለሰቦች ገንዘብ በመበደር ውጤት እስኪመጣ በሚል የጀመሩት ይህ የንግድ ሥራ በወቅቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤታማ ሆኖ ፍሬውን ማጣጣም ጀምረዋልና ፊታቸውን ወደ ትምህርት ማዞር አልሆነላቸውም።

ገና በለጋ ዕድሜያቸው ገንዘብ የቆጠሩትና የንግድን ጣዕም ማጣጣም የጀመሩት አቶ ታደሰ፤ በወቅቱ በጥሬ የወርቅ ንግዱ 20 ሺ ብር ያተርፋሉ። ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባ ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው ደግሞ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ጓጉተዋል። ይሁንና የወርቅ ንግዱን እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸው በኋላ የሚገኘውን ውጤት ለማወዳደር ጊዜ አልፈጁም። እናም ዩኒቨርሲቲ ገብተው የዲግሪ ምሩቅ ቢሆኑ በወር ደምወዝ 420 ብር እንደሚያገኙ አወቁ። ሁለቱንም ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ሚዛኑ ወዳጋደለበት አዘነበሉ። እናም ተምረው በወር 420 ብር ከመጠበቅ ይልቅ የጀመሩትን የጥሬ ወርቅ ንግድ አጠናክረው ቢያስቀጥሉ ውጤታማ እንደሚሆኑ በማመን ሙሉ ጊዜያቸውን ለንግድ በመስጠት ትምህርትን ደህና ሰንብት አሉት።

እንደዋዛ የጀመሩት የጥሬ ወርቅ ንግድ ዛሬ ላይ ለደረሱበት ስኬት መሰረት የጣለላቸው መሆኑን የሚያስታውሱት አቶ ታደሰ፤ በአሁኑ ወቅት በስፔሻሊቲ ቡና ላኪነት፣ በሆቴልና በነዳጅ ማደያ ሥራ ተሳትፈው ለበርካቶች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል።

የአርሶ አደር ልጅ እንደመሆናቸው የቤተሰቦቻቸው ፍላጎት ከንግዱ ይልቅ በትምህርት እንዲገፉ ፍላጎታቸው ነበር። ወላጅ አባታቸውና አብዛኛው የቤተሰብ አባል ቡና አምራችና አቅራቢ እንደነበሩም ያስታውሳሉ።

ከትምህርት ባስበለጡት የወርቅ ንግድ አምስት ዓመታትን ካሳለፉ በኋላ ባገኙት ትርፍ መኪና በመግዛት የንግድ ሥራቸውን ለመቀየር ጉዞ አንድ ብለው ጀመሩ። አቶ ታደሰ፤ የንግድ ሥራቸውን ለመቀየር የወሰኑት በቀዳሚነት የወርቅ ንግዱ ህጋዊ ባለመሆኑና ህጋዊ የሆነ ሥራ መሥራት እንዳለባቸው በማመን ነው፤ ከወርቁ ሲወጡ የቡና ንግድን በቀዳሚነት መርጠው ወደ ሥራው ገቡ።

ወላጅ አባታቸውን ጨምሮ አጠቃላይ ቤተሰቦቻቸው በቡና ንግድ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ምክንያትም ዘርፉን ለመቀላቀል ማገዶ አልፈጁም። በወቅቱም አቅጣጫቸውን ወደ ቡናው በማድረግ ከአካባቢው አርሶ አደር ቡና አበጥረውና ለቅመው ወደ ማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ ጀመሩ። ወርቅ ሸጠው ባገኙት ትርፍ የገዙት መኪና ደግሞ ንግዱን ለማቀላጠፍ በብዙ መልኩ አገዛቸው።

የቡና ንግዱ ውጤታማ እየሆነ ሲመጣ ታዲያ፤ ‹‹ቡናውን ለምን ወደ ውጭ አገር አንልክም›› በማለት በ2000 ዓ.ም በዘመነ ሚሊኒየም ባርኩሜ ቡና ላኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅታቸውን አቋቋሙ። የድርጅቱ መጠሪያ ባርኩሜ መሆኑም ወቅቱ የኢትዮጵያውያን ሚሊኒየም በመሆኑና ባርኩሜ ማለት ደግሞ በኦሮሚኛ ፍቺው ሚሊኒየም እንደሆነም አጫውተውናል።

ከዘመኑ ጋር የተወዳጀው ባርኩሜ ቡና ላኪም ከኢትዮጵያውያን ሚሊኒየም ማለትም ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ለተለያዩ የዓለም አገራት ስፔሻሊቲ ቡናን በመላክ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ለአገሪቷ እያስገባ ይገኛል።

ቡናን ወደ ለውጭ ገበያ በመላክ ሂደት ውስጥም የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደገጠሟቸውም አቶ ታደሰ ይገልጻሉ። በተለይም ለኤክስፖርት ገበያው አዲስና ጀማሪ መሆን ከልምድ አንጻር ከባድ እንደነበር ያስታውሳሉ። ይሁን እንጂ፤ ኤክስፖርት ማናጀር በመቅጠር በትንሽ በትንሹ በመላክ የኤክስፖርት ገበያውን መለማመድ ችለዋል።


በአሁኑ ወቅትም ሰፊ ቁጥር ያላቸውን የውጭ አገር ደንበኞች ማፍራት የቻሉት አቶ ታደሰ፤ በተለያዩ የዓለም አገራት በሚዘጋጁ ኤግዚብሽኖች በመሳተፍም የገበያ ትስስር መፍጠር ችለዋል። ባርኩሜ ቡና ላኪ ድርጅትም ኤክስፖርት የሚያደርገው ቡና ስፔሻሊቲ ቡና ሲሆን፤ በዋናነት የገበያ መዳረሻዎቹም አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ ቻይና፣ ታይዋን፣ ኮሪያ፣ ጃፓንና ሌሎችም ይገኙበታል።

የዛሬ 15 ዓመት ቡናን ወደ ውጭ ገበያ መላክ የጀመረው ባርኩሜ ቡና ላኪ በአሁኑ ወቅት በርካታ ደንበኞችን በማፍራት ተደራሽነቱን እያሰፋ እንደሚገኝ ያጫወቱን አቶ ታደሰ፤ ድርጅቱ ከዚህ ቀደም ለውጭ ገበያ የሚያቀርበውን ቡና ከአርሶ አደሮች እየገዛ ፈልፍሎ፣ አበጥሮና ለቅሞ ለገበያ ያቀርብ እንደነበር ያስታውሳሉ።

አሁን ደግሞ በምስራቅ ጉጂ ዞን አናሶራ ወረዳና ሻኪሶ ወረዳ ላይ የራሳቸውን ቡና ልማት እያካሄዱ ይገኛሉ። አጠቃላይ የቡና እርሻ ቦታቸው ስፋትም 190 ሄክታር ሲሆን፣ ከዚህ የሚያገኙትን ቡና በጥራት በማምረት በጥንቃቄና በተገቢው መንገድ በማዘጋጀት ደረጃውን የጠበቀ ስፔሻሊቲ ቡና በተሻለ ዋጋ ለውጭ ገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ።

ባርኩሜ ቡና ላኪ፤ ስፔሻሊቲ ቡና ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ በመሆኑ ሥራው ከፍተኛ ካፒታል እንዲሁም ቡናውን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈለግ እንደሆነ አቶ ታደሰ አስረድተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ስፔሻሊቲ ቡናን በስፋት ለመላክ ትልቅ አቅም ይጠይቃል። ያም ቢሆን ታዲያ ድርጅቱ እጅግ ጥራት ያለውን ቡና በዓመት ከ40 እስከ 50 ኮንቴነር ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ያስገባል።



አቶ ታደሰ ኤዴማ

በ50 ኮንቴነር ስፔሻሊቲ ቡና የሚገኘው ገቢም ከ150 እስከ 200 ኮንቴነር ከሚገኘው ሌላ ቡና ጋር ሲወዳደር እኩል አልያም እንደሚበልጥ አቶ ታደሰ ይገልጻሉ። ወደ ውጭ በሚልኩት ቡና በዓመት እስከ ሶስት ሚሊዮን ዶላር የሚያገኙ ሲሆን፤ ዘንድሮም ከ80 እስከ 90 ኮንቴነር ስፔሻሊቲ ቡና ለመላክና አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት አቅደው እየሠሩ ናቸው።

አቶ ታደሰ፤ በ190 ሄክታር የቡና እርሻቸው ላይ ከሚያለሙት ቡና በተጨማሪ በጉጂ ዞን በተለያዩ ከአካባቢዎች ከሚገኙ አርሶ አደሮችም ቡና ይገዛሉ። በተለይም ቀይ ቀይ የሆነውን ቡና ብቻ በማሰባሰብ በአልጋ ላይ አድርቀው በጥራት ለማዘጋጀት በርካታ አርሶ አደሮችን ይዘው ይሠራሉ። ቡና አልምቶ ለሚያቀርብላቸው አርሶ አደርም በኪሎ ከሁለት ብር እስከ ሶስት ብር ተጨማሪ ክፍያ በመፈጸም እንዲሁም የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ አርሶ አደሩ የበለጠ አምራች እንዲሆን ያደርጋሉ። በአሁኑ ወቅትም ኦርጋኒክ ሰርቲፋይድ በመሆን የበለጠ ተጠቃሚ መሆን የቻሉ በርካታ አርሶ አደሮች ስለመኖራቸውም አቶ ታደሰ አጫውተውናል።

ድርጅቱ በጉጂ አካባቢ ብቻ አምስት የሚደርሱ የቡና መፈልፈያዎች እንዳሉት ተናግረው፣ በእያንዳንዱ መፈልፈያ ጣቢያ ከ400 እስከ 500 የሚደርሱ አርሶ አደሮች ስለመኖራቸውም ይገልጻሉ። በአንድ የቡና መፈልፈያ ጣቢያም ከ40 እስከ 50 መኪና ቡና ይፈለፈላል ይላሉ።

በስፋት ከተሰማሩበት የቡና ወጭ ንግድ በተጨማሪ ነዳጅ በማደል ሥራ የተሳተፉት አቶ ታደሰ፤ በክልል ከተሞች ማለትም በነገሌ ቦረና፣ ክብረ መንግሥት፣ አርሲ ነገሌና በሌሎችም ቦታዎች ኖክ የነዳጅ ማደያዎችን አቋቁመው ለየአካባቢዎቹ ማህበረሰብ ነዳጅ እያቀረቡ መሆናቸውን ያብራራሉ።

ትምህርታቸውን ገታ አድርገው ወደ ወርቅ ንግድ የገቡት አቶ ታደሰ፤ የንግድ ሥራቸው መሰረቱን እያጸና ውጤታማ በመሆኑ ወደ ቡና ንግድ ተብተዋል፤ ቀጥለውም ነዳጅ ማደያዎችን በተለያዩ የክልል ከተሞች ከፍተዋል። እንዲህ እንዲህ እያሉ የንግድ ሥራ ዘርፎችን ለማስፋፋት በሚያደርጉት ጥረት እግዚአብሔርም ተጨምሮበት በቅርቡም በመሀል አዲስ አበባ ቦሌ ደረጃውን የጠበቀ ባለ አራት ኮከብ ሆቴል ገንብተው አገልግሎት በመስጠት ለከተማዋ ድምቀት ጨምረዋል።

የሆቴሉን ስያሜም በትንሽ ልጃቸው ስም መሰየማቸውን የጠቀሱት አቶ ታደሰ፤ የሆቴል ኢንቨስትመንትን ሲቀላቀሉም ይህ የመጀመሪያቸው እንዳልሆነ አጫውተውናል።

ተወልደው ባደጉበት አካባቢ በምዕራብ ጉጂ ዞን በቀድሞ አጠራሩ አገረማርያም በአሁኑ ወቅት ደግሞ ቡሌ ሆራ በሚባለው ከተማ አገረማርያም ሆቴልን ገንብተዋል። ከሆቴሉ አገልግሎት በተጨማሪ በከተማው የመጀመሪያ የሆነውን ፎቅ በመገንባት ቀዳሚ ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት ከተማዋ ፎቅ በፎቅ እንደሆነችና የተለያዩ ተቋማትም መገንባታቸውን ይናገራሉ፤ ለዚህም እርሳቸው የገነቡት አገረማርያም ሆቴል መሰረት የጣለና በከተማዋ ፎቅ መስራት እንደሚቻል ማሳያ እንደሆነ ይገልጻሉ።

በሆቴል ሥራቸው የመጀመሪያ ከሆነው አገረማርያም ሆቴል ያገኙትን ልምድና ዕውቀት በማዋሃድ ሁለተኛውንና ትልቁን ኬና ሆቴል መገንባት የቻሉት አቶ ታደሰ፤ ሆቴል ብዙ ብር ባይገኝበትም ጥሩ ስም እንደሚገኝበት ነው የሚናገሩት።

በመሀል አዲስ አበባ ቦሌ ላይ ሆቴል የመገንባታቸው ምክንያትም ሆቴል ከኤርፖርት ሲርቅ ዋጋው ይቀንሳል፤ ለኤርፖርት ሲቀርብ ደግሞ የሆቴል ዋጋ ይጨምራል ነው። ይህም በቡና ንግድ ምክንያት በተዘዋወሩባቸው የዓለም አገራት ያገኙት ልምድ ነው። ይህን ልምድ መሰረት በማድረግም ዛሬ ላይ ለኤርፖርት ቅርብ ከሆነው መሀል ቦሌ ላይ ባለ አራት ኮከብ የሆነውን ኬና ኢንተርናሽናል ሆቴል ገንብተው ለአገልግሎት ክፍት አድርገዋል።

በሆቴሉ ብቻ ከ100 ለሚልቁ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን፤ በቡና ምርትና ዝግጅት ሂደት ውስጥም በቋሚነት 60 ለሚደርሱ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠራቸውን ከዚህ በተጨማሪም በቀን ከ200 እስከ 300 ለሚደርሱ የኮንትራት ሠራተኞች የሥራ ዕድል በየዕለቱ የሚፈጠር መሆኑን ይገልጻሉ። በቡና ለቀማ ጊዜ ደግሞ ቁጥሩ በእጥፍ የሚጨምር እንደሆነ ያስረዱን አቶ ታደሰ፤ የሥራ ዕድል ለፈጠሩላቸው ሠራተኞችም ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ በወር ደመወዝ እንደሚከፍሉ ይናገራሉ።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርጉት አቶ ታደሰ፤ በተለይም ቡና በሚያመርቱባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በየዓመቱ የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ያቀርባሉ። ትምህርት ቤት፣ መንገድና ድልድይ በመሥራትም ከፍተኛ አበርክቶ አድርገዋል። ከእነዚህም መካከል በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ አካባቢዎች ኡራጋ ጠቤ ቡርቃ ቀበሌና ጉራቼ ጀልዶ ላይ ያሰሯቸው ትምህርት ቤቶች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። በተጨማሪም በአካባቢው የሚገኙ ወረዳዎች በሚሠሯቸው ማንኛውም የልማት ሥራዎች የበኩላቸውን ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ።

‹‹በአሁኑ ወቅት ያለው የቡና ንግድ ስርዓት ዘርፉን ውጤታማ ማድረግ ያስቻለና ሥራውና የሥራው ባለቤት የተገናኙበት ነው›› የሚሉት አቶ ታደሰ፤ ለዚህም መንግሥት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል በማለት መንግሥት ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የወሰደውን እርምጃ አድንቀዋል።

ቡና ላይ ገና ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅም ጠቅሰው፣ መንግሥት በወሰደው አንድ እርምጃ ተዓምራዊ ለውጥ መምጣቱ አስደሳች መሆኑን ይናገራሉ። በቀጣይም በዘርፉ እየታየ ያለው ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው አርሶ አደሩ ላይ መሥራት አስፈላጊና የግድ መሆኑን ነው ያስገነዘቡት።

በመጨረሻም በሆቴሉ ዘርፍ በስፋት ለመምጣት ማሰባቸውን ያጫወቱን አቶ ታደሰ፤ መንግሥት በሊዝ በሚሰጣቸው ቦታ ላይ ባለ አምስት ኮከብ 30 ፎቅ ከፍታ ያለው ዘመናዊ ሆቴል ለመገንባት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል። በቡናው ዘርፍም እንዲሁ ቡናን አበጥሮ በጥሬው ብቻ ከመላክ ይልቅ እሴት በመጨመር ቆልቶና ፈጭቶ ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሰናዱ ይገኛሉ። ይህም ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ድርሻ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይሆንም።